# የይቅርታ ቅርስ

ጽሑፍ፡- በፓትሪሺያ ስንጀን
ሜሪ ሚልስ እንዳሻሻለችው
ትርጉም፡- በገበየሁ አየለ
አርትዖት፡- ዘነበ ገብረሐና

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ አይ ኤም ሥነ ጽሑፍ
የፖ.ሣ.ቁ. 127 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
1997 ዓ.ም (2004)

Titles by Patricia M.St. John

STAR OF LIGHT

TREASURES OF THE SNOW

THE TANGLEWOODS' SECRET

RAINBOW GARDEN

THE SECRET OF THE FOURTH CANDLE

THE MYSTERY OF PHEASANT COTTAGE

For older readers:

NOTHING ELSE MATTERS

THE VICTOR

I NEEDED A NEIGHBOUR

For younger readers:

THE OTHER KITTEN

FRISKA, MY FRIEND

©Patricia M. St. John 1950

First published 1950

The revised edition first published 1999

Reprinted 2001

Scripture Union, 207-209 Queensway, Bletchley, Milton Keynes MK2 2EB

ISBN 1 85999 266 8

All rights resereved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted, in any form, or by any means, electronic, mechanical, photocopying, recording or otherwise, without the prior permission of Scripture Union.

Printed and bound in Great Britain by

Creative Print and Design (Wales) Ebbw Vale.

## ማውጫ

1. ምዕራፍ አንድ፡- የገና ዋዜማ ....1
2. ምዕራፍ ሁለት፡- የአኔት ሴት አያት መጡ ....8
3. ምዕራፍ ሦስት፡- በጣም ልዩ የገና ስጦታ ....17
4. ምዕራፍ አራት፡- ጸቡ ተጀመረ ....24
5. ምዕራፍ አምስት፡- አደጋው ....30
6. ምዕራፍ ስድስት፡- ከአደጋ መዳን ....37
7. ምዕራፍ ሰባት፡- አኔት በቀል ዐቀደች ....45
8. ምዕራፍ ስምንት፡- የማምለጫ ዕለት .... 51
9. ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ወደ ሆስፒታል ጉዞ ....58
10. ምዕራፍ አሥር፡- ሉሲየን ጓደኛ አገኘ ....65
11. ምዕራፍ አሥራ አንድ፡- ወደ ለምለሙ ከፍታ ሥፍራ ጉዞ ....73
12. ምዕራፍ አሥራ ሁለት፡- የአኔት በቀል ....80
13. ምዕራፍ አሥራ ሦስት፡- የሽማግሌው ታሪክ ....86
14. ምዕራፍ አሥራ አራት፡- የእጅ ሥራው ውድድር ....96
15. ምዕራፍ አሥራ አምስት፡- ሌላ ገና እና ጣፋጭ ስኩቶች ....104
16. ምዕራፍ አሥራ ስድስት፡- ድመቲቱ ክላውስ ጠፋች ....110
17. ምዕራፍ አሥራ ሰባት፡- የተከፈተ በር ....116
18. ምዕራፍ አሥራ ስምንት፡- ነገሮች መስተካከል ጀመሩ ....121
19. ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ፡- አኔት አንድ ፍልሚያ ድል አደረገች ....126
20. ምዕራፍ ሃያ፡- ሉሲዩን አንድ አሳብ አለው ....134
21. ምዕራፍ ሃያ አንድ፡- የማይረሳ ሌሊት ....142
22. ምዕራፍ ሃያ ሁለት፡- ሉሲየን ዶክተሩን አገኛቸው ....150
23. ምዕራፍ ሃያ ሦስት፡- ዳኒ ከዶክተሩ ጋር ተገናኘ ....158
24. ምዕራፍ ሃያ አራት፡- የኢየሱስ ፍቅር ሰዎችን ይለውጣል ....167
25. ምዕራፍ ሃያ አምስት፡- ዳኒ ተሻለው ....172
26. ምዕራፍ ሃያ ስድስት፡- አዲስ ጅማሬ ....176

# ስለ አዲሱ እትም

ፓትሪሺያ ስንጆን የጻፈቻቸው መጻሕፍት የመጀመሪያዎቹ እትሞች ከወጡ ከ50 ዓመታት በላይ ቢሆናቸውም፣ ዛሬም ቢሆን ተወዳጅነታቸው እንዳለ ነው።

በዚህ አዲስ እትም፣ ሜሪ ሚልስ የፓትሪሺያ ስንጆንን አስደናቂ የታሪክ ጸሐፊነት ክህሎት በማያበላሽ መንገድ በጥንቃቄ ቋንቋውን ለአዲሱ ትውልድ አንባቢዎች እንደሚስማማ አድርጋ አስተካክላዋለች።

# የደራሲዋ ማስታወሻ

ኑሮዬን እዚያው ለማድረግ ስዊዘርላንድ ወደ ተባለው አገር የሄድሁት የሰባት ዓመት ልጅ ሳለሁ ነበር። ቤቴ እኔትና ዳኒ የተባሉ ልጆች ከሚኖሩበት አንድ መንደር በላይ ባለ ተራራ ላይ የሚገኝ ቤት ነበር።

እንደ እነ እኔት፥ እኔም መንደሪቱ ውስጥ ወደ አለው ትምህርት ቤት የምሄደው በበረዶ ላይ በሚንሸራተት ጋሪ ነበር። በበጋ ደግሞ የሣር ድርቆሽ ሰብስቤ እየከመርኩ ቤተሰቦቼን እረዳለሁ። ከብቶችን እጠብቅ፥ ሣር ድርቆሽ ውስጥ እተኛም ነበር። በገና በዓል ዋዜማ ምሽት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድኩ የብርትኳን ፍሬዎችና ድብ በሚባለው አውሬ ቅርጽ የተሠሩ ብስኩቶች የተንጠለጠሉበትን የገና ዛፍ ተመልክቻለሁ። አሞኝ ከሸለቆው ባሻገር ባለው መንደር ውስጥ ወደሚገኘው ዶክተር የተወሰድሁበት ጊዜም ነበር። አንድ ገበሬ የሰጠኝ ክላውስ የተባለ ነጭ ድመት ነበረኝ። ሕፃናት ወንድሞቼ ወተት በሚያመላልስ ጋሪ ላይ ሆነው ጋሪውን ከሚጎትተው ትልቅ ውሻ በስተኋላ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል።

ይህ ሁሉ የሆነው ግን ከብዙ ዓመት በፊት ነበር። ወደ ስፍራው የተመለስሁት ለጉብኝት ነበር። ስዊዘርላንድ አሁን ያኔ ከማውቃት በጣም ሳትለወጥ አትቀርም። ዛሬ በዚያ አገር አንድ ልጅ ትምህርቱን ለረጅም ጊዜ የሚያቋርጥበት ሁኔታ እንደማይኖርና የሕክምና አገልግሎቱም እንደ ተሻሻለ ርግጠኛ ነኝ። በአሁኑ ጊዜ እያንዳንዱ ትንሽ መንደር የራሱ ዶክተር ይኖረዋል ብዬ እገምታለሁ። በትክክል አላውቅም።

ስለ አንዳንድ ነገሮች ግን ርግጠኛ ነኝ፤ የያኔው ትምህርት ቤትና ቤተ ክርስቲያኒቱ አሁንም አሉ። በላሞች አንገት ላይ የሚታሠሩ ቃጭሎች ዛሬም ሸለቆው ውስጥ ያቃጭላሉ። አበቦችም በመብቀያቸው በግንቦት ወር ሜዳውን ሁሉ በመልካም መአዛቸው ያውዱታል። ሕፃናት በዓሉ በደረሰ ቁጥር ገና ዛፍ ሥር ሰብስብ እያሉ በዓሉን የሚያከብሩበትን መዝሙር ይዘምራሉ፤ እኔ አደርገው እንደነበረ ሁሉ፥ በድብ ቅርጽ የተሠራ ብስኩታቸውን ይወድዳሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ለታሪኩ ማማር ስል ያልነበሩ አንድ ወይም ሁለት ነገሮችን ስለጨመርሁ፥ መንደሪቱን በትክክለኛ ስሟ አልጠራኋትም። ለምሳሌ፥

በሸለቆ ማቋረጫ ብቻ የሚደረስበት ከተማ በመንደሪቱ አቅራቢያ አልነበረም። ከዚህ በቀር፥ ሌላውን ነገር የገለጥሁት እውነቱን እንዳለ ነው ። ወደ ስዊዘርላንድ የምትሄድበት አጋጣሚ ቢኖርና በኤሌክትሪክ ኃይል በሚሽከረከር መጓጓዣ ባቡር ተሳፍረህ ከሞንትራ ከተማ ሽቅብ ጉዞ ብትጀምር፥ ባቡሩ በሚቆምበት አካባቢ የሣር ድርቆሽ የተከመሩባቸውን ሜዳዎች ታገኛለህ። አልፎ አልፎ ቁጥ ቁጥ ካሉት ቤቶች ኋላም አረንጓዴ ተራራዎችን ታያለህ። ከባቡሩ ሃዲድ በስተቀኝ ወደ ታች እየተወረወረና አረፋ እየሠራ የሚፈስ ወንዝ አለ። ከወንዙ ባሻገር ሌሎች ተራራዎች ይታያሉ። በአንድ ረጅምና አረንጓዴ ተራራ፥ እንዲሁም እልፍ ብሎ በሚታይ ሌላ ቋጥኛማ ተራራ መካከል አንድ መተላለፊያ መንገድ አለ። ከባቡሩ ጣቢያ ብዙም ሳይርቅ አጠር ያለ ነጭ የትምህርት ቤት ህንፃ፥ ከአንድ ኮረብታ በስተኋላ ደግሞ ከእንጨት ተሠርቶ ጣራው ሽቅብ የወጣ ቤተ ክርስቲያን ስትመለከት በዚህ መጽሐፍ የሚቀርበው ታሪክ የተጀመረው እዚያች መንደር ውስጥ መሆኑን ትረዳለህ።

ፓትሪሺያ ስንጀን

1950

# ምዕራፍ አንድ
# የገና ዋዜማ



ዕለቱ የገና በዓል ዋዜማ የነበረበት ዕለት ነበር፤ በሁሉም ስፍራ ላይ «ስነው» ይታያል።

በኢትዮጵያ ውስጥ «ስነው» አይታይም፤ ይህ ታሪክ በተፈጸመበት በስዊዘርላንድ ግን ስነው መታየቱ የተለመደ ነው። «ስነው» የሚለው ቃል አየሩ ለተለመደው ዝናብ በጣም በሚቀዘቅዝበት ጊዜ እንደ ባዘቶ ጥጥ ከሰማይ ብን ብን እያለ የሚወርደውን ለስላሳ ነጭ ብናኝ የሚያመለክት ቃል ነው። ስነው በከፍተኛ ሁኔታ ሲወርድ፥ እይታን ይሸፍንና ለማየት አስቸጋሪ ይሆናል። ለስላሳው ነጭ ብናኝ መሬት ላይ ይከማችና ተራሮችን፥ ዛፎችንና ቤቶችን ሳይቀር ሁሉንም አካባቢ በለስላሳው ነጭ ብርድ ልብስ ይሸፍነዋል። ስነው በጣም ጥልቅ ሊሆን ይችላልና ገና በአዲስነቱ ሳለ ያማረ ሆኖ ይታያል። ሕፃናት ከእርሱ አሻንጉሊቶችን በመሥራትና የስነው ኳሶችን እርስ በርሳቸው በመወራወር በስነው ውስጥ መጫወት ደስ ያሰኛቸዋል። አየሩ ሲቀዘቅዝ፥ ስነው ግግር ሊሆን ይችላል፤ ከዚያም ጠጣር ይሆንና ስለሚያንሸራትት በእርሱ ላይ መራመድ አደገኛ ነው። አየሩ ሲሞቅና ስነው ሲሟሟ ወደ ውኃነት ይለወጣል። አልፎ አልፎ የአየሩ ሙቀት መለዋወጥ ብዛት ያለው ስነው ከተራራው ጎን ተደርምሶ እንዲወርድ

ያደርጋል። ይህ ናዳ ተብሎ ይጠራል። እየሟሟ ያለው ስነው በዚህ ዐይነት ኀይል ዛፎችን ሊነቃቅልና ቤቶችንም ሊያፈራርስ ይችላል፤ በዚህ ወቅት ተራሮች ላይ የሚወጣ ማንኛውም ሰው በስነው ውስጥ የመቀበር አደጋ አለበት።

ሦስት ሰዎች በቁልቁለታማውና «ስነው» በተሸፈነው ተራራ ወደ ታች በመውረድ ላይ ነበሩ። ከፊት ለፊታቸው የሚያበራው የጨረቃ ብርሃን ከኋላቸው ጥላ አጥልቷል። ከሦስቱ ሰዎች መካከለኛዋ ረጅም ቀሚስ ለብሳ ጥቁር ካፖርት ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋለች። አንድ ፀጉረ ጥቁር ልጅ እጅዋን ጥብቅ አድርጎ በመያዝ ሳያቋርጥ እያወራ አብሯት ይሄዳል። አንዲት የሰባት ዓመት ሴት ልጅ ከእነርሱ እልፍ ብላ ሰማይ ላይ የተበተኑትን ከዋክብት እየተመለከተች በመጓዝ ላይ ናት። ከብስኩት የተሠራና የድብ ቅርጽ ያለው አሻንጉሊት ደረቷ ላይ ባጠመረቻቸው እጆቿ ጥብቅ አድርጋ ይዛለች። አሻንጉሊቱ ወርቅማ መልክ ያለው ሲሆን፥ ዓይኖቹ በጣፋጭ ክሬም የተሠሩ ናቸው።

ወንዱ ልጅም የአሻንጉሊት ቅርጽ ያለው ብስኩት ነበረው። ስለበላው የተረፈው የአሻንጉሊቱ የኋላ ሁለት እግሮች ብቻ ነበሩ። ሴቷን ልጅ በንቀት እያየ፥ «የእኔ አሻንጉሊት ካንቺ የበለጠ ትልቅ ነበር» አለ።

ሴቷ ልጅ በልጁ ንግግር ሳትናደድና ወደ እርሱም ሳትመለከት፥ «ያንተ ትልቅ ቢሆንም በእኔ አሻንጉሊት አልለውጥህም ነበር» አለች። ከዚያም እቅፍዋ ውስጥ ያለውን ውብ አሻንጉሊት ጎንበስ ብላ በፍቅር ተመለከተችው። በጣም ያምራል። አቤት እንዴት ጠንካራ ነው! መአዛው እንዴት ያስጎመጃል! በጨረቃ ብርሃን ሲታይ እንዴት ደስ ይላል! እንደዚህ የሚያምር አሻንጉሊቱን በፍጹም አልበላውም ብላ ወሰነች!

ያን የመሰለ የአሻንጉሊት ብስኩት የተሰጣቸው የአንድ መንደር ሰማኒያ ትንንሽ ልጆች ቢሆኑም፥ የእርሷ ከሁሉም ይበልጥ ያምራል።

በመሆኑም፥ ለዚያ ምሽት መታሰቢያነት ለሁልጊዜ ታስቀምጠዋለች። በአየችው ቁጥር የገና በዓል ዋዜማን፥ ቀዝቃዛውን ሰማያዊ ሰማይ፥ በብርሃን የደመቀውን ቤተ ክርስቲያን፥ የከዋክብት ቅርጽ ባላቸው ብልጭልጭ አሻንጉሊቶች ያጌጠውን የገና ዛፍ፥ የገና መዝሙሮችን፥ ዛፍ ሥር ያለውን ትንሽ የሕፃን አልጋ ፈጽሞ አትረሳቸውም። በእንግዳ



ማረፊያው ምንም ቦታ አለመኖሩን ስታስብ አልቅሺ አልቂሺ የሚል አሳብ መጣባት። ያኔ እዚያ ብትሆን ኖሮ በሯን በሰፊው ከፍታ ማርያምንና ዮሴፍን በእንግድነት ትቀበላቸው ነበር።

ወንዱ ልጅ፥ ሉሲየን በሴቷ ልጅ ዝምታ ተናዱል። «የእኔን የብስኩት አሻንጉሊት ልጨርሰው ትንሽ ነው የቀረኝ። እስቲ ካንቺ አቅምሺኝ አኔት። ገና አልጀመርሽውም፥» አለ ኮስተር ብሎ። ነገር ግን አኔት በእምቢታ ራሷን ነቅንቃ አሻንጉሊቷን ይበልጥ እቅፍ እያደረገች፥ «በፍጹም አልበላውም፥ ለሁልጊዜ አስቀምጠዋለሁ» አለች።

እንዲህ እያወሩ ነጩ ኮረኮንቻማ መንገድ ለሁለት ከሚካፈልበት ስፍራ ደረሱ። ከዚያ ትንሽ እልፍ ብሎ ካለ መንታ መንገድ አቅራቢያ የውስጥ መብራት ብርሃናቸው በየመስኮታቸው የሚታዩ ቤቶች አሉ። ከኋላቸው በረቶች ይታያሉ። ያ አካባቢ የአኔት ቤት መዳረሻ ነበር።

ከልጆቹ ጋር የነበሩት ማዳም ሞሬል ቆም ብለው አኔትን ተመለከቷትና፥ «ብቻሽን ወደ ቤትሽ ትሄጃለሽ ወይስ እኛ እናድርስሽ?» አሏት።

«የለም፥ ብቻዬን ብሄድ ይሻለኛል። ከእናንተ ጋር እንድውል ስለፈቀዳችሁልኝ አመሰግናለሁ። ደህና ይደሩ ማዳም፤ ደህና እደር ሉሲየን፥» አለችና ወደ ቤቷ አቅጣጫ ሮጠች። ሴትዮይቱ አሳባቸውን ለውጠው እስከ ቤትሽ ካላደረስኩሽ እንዳይሏት የማሰቢያ ጊዜ ልትሰጣቸው አልፈለገችም።

ከሉሲየን ልፍለፋ ተገላግላ በሌሊቱ ጸጥታ ደስ ለመሰኘት ጓጓታለች። ለማዳም ሞሬልና ለሉሲየን የማያቋርጥ ጥያቄ ትሑት መልስ መስጠቱ እያለ እንዴት ለማሰላሰልና ከዋክብትን ለመመልከት ትችላለች?

ከዚያ ቀደም በምሽት ውጭ ቆይታ አታውቅም። የዚያ ዕለቱም በአጋጣሚ የሆነ ዓይነት ነው። በዚያን ምሽት በበረዶ ጋሪ ከወላጆቿ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ነበረባት። ይህን አሳብ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ለሳምንታት ሲያሰላስሉና ሲያቅዱ ነበር የቆዩት። ያን ዕለት ጠዋት ግን እናቷ ስለታመሙ አባቷ ሐኪም ፍለጋ ከሸለቆው ባሻገር ወደ አለ ከተማ ሄዱ። ሐኪሙ በሻይ ሰዓት አካባቢ መጥቶ ነበር፤ ነገር ግን አኔት ተስፋ እንዳደረገችው እናቷን በጊዜው

ሊያድኗቸውና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄዱ ሊያደርግ አልቻለም። አኔት በጣም እያዘነች ከእርሷ በላይ ከተራራው ከመጡት ማዳም ሞሬል ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን የሄደችው ለዚህ ነበር። እዚያ ስትደርስ ግን፥ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው የገና በዓል ሥርዓት ድምቀት ሌላውን ነገር ሁሉ አስረሳት።

የሥርዓቱ ድምቀት ከትዝታዋ አልጠፋም። አሁን በበረዶ በተሸፈነ መሬትና በከዋክብት መካከል ስትቆም ከዚህ ድምቀት ተለይታ ወደ ቤቷ መግባት ቅር ያሰኛል። ቤቷ ደርሳ ወደ ፎቁ መወጣጫ ደረጃዎች ስትቃረብ አመንታችና ዙሪያዋን ተመለከተች። ፊት ለፊቷ የላሞች በረት ታያት፤ ከብቶች ሲንቀሳቀሱና ሲመገቡ ተሰማት። ወዲያው አንድ አስደሳች አሳብ መጣባትና አሳቧን በፍጥነት ቆርጣ በበረዶው ውስጥ ባለው ፈለግ ላይ እየሮጠች የበሩን መወርወሪያ አነሣች። የከብቶቹ ትኩስ ትንፋሽ፥ እንዲሁም የወተትና የድርቆሽ ሣር ደስ የሚል ሽታ ተቀበላት። በአንዲት መልኳ ቡናማ በሆነ ላም እግር ሥር ሾልካ አለፈችና ላሚቱ ፊት ወደ አለው ግርግም እንደ ትል እጥፍጥፍ እያለች ሄደች። (ግርግም ከብቶች የሚመገቡበት ቦታ ነው)። ላሚቱ ግርግሙ ላይ ያለውን ሣር በመመገብ ላይ ናት። አኔት አንገቷን እቅፍ አደረገቻት፥ ከዚያም ልክ ማርያም የወለደችውን ሕፃን አቅፋ በረት ውስጥ ተቀምጣ ሳለች ላሞቹ ሣር ይበሉ እንደነበሩ፥ ላሚቱ ሣር መብላቷን ቀጠለች።

አኔት ላሞቹ ፊት የነበረውን ግርግም እየተመለከተች ሕፃኑ ኢየሱስ እንዲያ ባለ ግርግም ሣሩ ላይ የተኛበትን ሁኔታ አሰላሰለች። በረቱ ውስጥ የነበሩት ላሞች በፀጥታ ለሕፃኑ ሲሰግዱለት ታያት። በበረቱ ጣራ ቀዳዳ አንድ ደማቅ ኮከብ ይታያት ስለነበር፥ ኮከቡ በቤተ ልሔም ላይ ያበራበትንና ጠቢባኑን ሕፃኑ ኢየሱስ ተኝቶ ወደ ነበረበት ቤት የመራበትን ሁኔታ አስታወሰች። እነዚያ ለኢየሱስ ሊሰግዱ የመጡ ሰዎች ወደ ጎንና ጎን እየተወዛወዘ በሸለቆው ላይ በሚራመዱ ግመሎቻቸው ላይ ተቀምጠው፥ ሲጓዙ በአሳቧ ታያት። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፥ የበረቱ በር በቀስታ ይከፈትና የበግ ግልገሎችን ያቀፉ እረኞች በፀጥታ ገብተው ሕፃኑን ለማሞቅ ከበግ ፀጉር የተሠራ ልብስ እናልብሰው ይላሉ። አኔት ወደ ታች ጎንበስ ብላ፥ ሰው ሁሉ አላስገባም ብሎ በር ለዘጋበትና ቤት ለሌለው ሕፃን በጣም አዘነችለት።



«ቤታችን ውስጥ ሰፊ ቦታ ነበር። ብቻ ይህ ስፍራም (በረቱ) ከሁሉም ሳይሻል አይቀርም። የሣሩ ድርቆሽ ንጹሕ፥ ሉይዝ ተብላ የምትጠራዋ ላም ትንፋሽም ትኩስና ደስ የሚል ነው። ምናልባት እግዚአብሔር ለልጁ ይህን የተሻለ ስፍራ ሳይመርጥለት አልቀረም፥» አለች አኔት በሹክሹክታ።

በከፊል በተከፈተው የበረት በር በኩል የፋኖስ ብርሃን ባታይና ከውጭ የስነው ላይ የሰው እርምጃ ኮሽታ ባትሰማ ኖሮ ሌሊቱን በሙሉ ስታሰላስልና ስታልም ታድር ነበር።

ወዲያው የአባቷን አስቸኳይ ጥሪ ሰማች።

ከግርግሙ ላይ በመውረድ የላሚቱ ጅራት እንዳይነካት አደረገችና ከበረቱ ወጥታ አባቷን ለማቀፍ እጆቿን ዘርግታ ወደ እርሳቸው ሮጠች።

«ላሞቹን እንኳን ለገና በአል አደረሳችሁ ልላቸው ነው ወደ በረቱ የገባሁት። ልትፈልገኝ ነው የመጣኸው?» አለች እየሳቀች።

«አዎ፥ ልፈልግሽ ነው የመጣሁት» አሉ አባቷ። ነገር ግን እንደ እርሷ አልሳቁም። በጨረቃ ብርሃን ፊታቸው ነጥቶና ኮስተር ብሎ ታየ። እጇን ይዘው ወደ ፎቁ በሚያስወጡት ደረጃዎች ላይ ሊጎትቷት በመቃረብ፥ «እናትሽ በጣም ስትታመም ቶሎ መምጣት ነበረብሽ። ወዴት ሄደች እያለች ለግማሽ ሰዓት ያህል ስለ አንቺ ትጠይቅ ነበር» አሉ።

በጣም የሚወዷት እናቷ ታመውና ተኝተው ሲፈልጓት እርሷ ግን በገናው ዛፍ ውበት ተማርካ ስለረሳቻቸው አኔት በጣም አዘነች። ሐኪሙ ሕክምና አድርጎላቸው እንዲሻላቸው ያደርጋል ብላ አስባ ነበር። እጇን ከአባቷ እጅ አላቀቀችና ከእንጨት በተሠራው የፎቅ መወጣጫ ሽቅብ እየሮጠች ወደ እናቷ መኝታ ቤት አመራች።

አኔት ቀጭንና ትንሽ ልጅ ስለሆነች፥ ድምፅም ሳታሰማ ቀስ ብላ ስለሄደች፥ ወደ እናቷ አልጋ እስከምትጠጋ ድረስ፥ ዶክተሩም ሆነ የመንደሪቱ ነርስ አላዩዋትም። እናቷ ግን አዩዋትና እጆቻቸውን በከፊል ወደ እርሷ ዘረጉ። አኔት ሳትናገር እናቷ እቅፍ ውስጥ ገባችና ፊቷን በእናቷ ትከሻ ሸሸገችው። የእናቷ ፊት እንደ ትራሳቸው ነጭና አስፈሪ ሆኖ ስለአገኘችው አለቀሰች። ያን ያህል ጊዜ ከእናቷ ተለይታ በመቆየቷም ተጸጸተች።

«አታልቅሺ አኔት! አንድ ስጦታ አዘጋጅቼልሻለሁ» አሉ እናቷ በሹክሹክታ።

አኔት ለቅሶዋን በቅጽበት አቆመች። ስጦታ? እንዴታ፥ የገና በዓል እኮ ነው አኔት እናቷ ስጦታ እንደሚሰጧት ረስታ ነበር። እናቷ ስጦታ የሚሰጧት ቢሆንም ያን የሚያደርጉት አብዛኛውን ጊዜ የገና በዓል በዋለ በሳምንቱ በሚውለው የፈረንጆች አዲስ ዓመት በዓል ላይ ነበር። እናቷ ያዘጋጁላት ስጦታ ያለው የት ይሆን? አካባቢዋን በጉጉት ተመለከተች።

እናቷ ወደ ነርሷ ፊታቸውን መለስ አደረጉና፥ «ስጪት» አሉ ድክም ባለ ድምፅ። ነርሷ በጨርቅና በብርድ ልብስ የተጠቀለለ ነገር አነሣች። ከዚያም ወደ አኔት ቀርባ ሰጠቻትና፥ «ታናሽ ወንድምሽ ነው፤ የእሳቱ ምድጃ ወደ አለበት ክፍል እንሂድና ወንድምሽ የተኛበትን አልጋ ታወዛውዢለሽ። እናትሽ እንቅልፍ እንዲወስዳት እንውጣላት። ደህና እደሪ በይና ሳሚያት» አለቻት።

«ታናሽ ወንድምሽ፤ የአንቺ ነው አኔት። አሳድጊልኝ! ውደጂው! ተንከባከቢልኝ! ለአንቺ ሰጥቼዋለሁ፥» አሉ እናቷ በደካማ ድምጻቸው።

ወዲያው ድምጻቸው በድካም ተዋጠ፥ ዓይኖቻቸውን ከድን አደረጓቸው። አኔት መናገር እስኪያቅታት ፍዝዝ ብላ በነርሷ እየተመራች ከፎቅ ወረደች። የገና ስጦታዋ በሻሽና በብርድ ልብስ ትጠቅልሎ የተኛበትን ከእንጨት የተሠራ አልጋ ለማወዛወዝ በምድጃው አጠገብ በርጩማ ላይ ተቀመጠች።

አኔት በአልጋው ውስጥ ትንሽ ወንድሟ የተኛበትን ጉብታ እየተመለከተች ለረጅም ጊዜ በፀጥታ ተቀመጠች። ቤቱ ፀጥታ ሰፍኖበታል። የገና ኮኮብ ልክ ቤተልሔም በረት ውስጥ በተወለደው ሕፃን ላይ እንዳበራው ሁሉ፥ በዚያን ምሽትም አኔት በነበረችበት መስኮት ብርሃኑን ፈንጥቋል። ማርያም በረት ውስጥ ተቀምጣ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን ሕፃን ትመለከት እንደነበረ፥ አኔትም ምድጃው አጠገብ ተቀምጣ ሕፃን ወንድሟን ትጠብቅ ነበር።

ለስላሳ ጣቶቿን ሰደድ አድርጋ የወንድሟን ለስላሳ የራስ ፀጉር ዳሰሰችው። የሚታያት የሕፃኑ የአካል ክፍል እራሱ ብቻ ነበር። በድካም አተነፋፈስ ተነፈሰችና እራሷን ሕፃኑ ተወዛዋዥ አልጋ ላይ አስደግፋ በአሳብ ጭልጥ ብላ ሄደች። ከዋክብት፥ እረኞች፥ ገና የተወለዱ ሕፃናት፥ የተዘጉ በሮች፥ ጠቢባንና በድብ ቅርጽ የተሠሩ



ብስኩቶች. . . እነዚህ ሁሉ እየተደበላለቁ በአሳቧ ሲታይዋት ሳለ ነበር፥ እንቅልፍ ሸለብ አድርጓት ወደ ወለሉ ሸርተት ያለችው።

አባቷ ያገኟት በዚህ ሁኔታ እራሷን ተወዛዋገዡ አልጋ ላይ አስደግፋ ልክ እንደ ሕፃኑ ወንድሟ በፀጥታ ለአንድ ሰዓት ከአንቀላፋች በኋላ ነበር።

አኔትን ከተኛችበት እያነሷት፥ «እናት የሌላችሁ አሳዛኝ ሕፃናት፤ እንዴት አድርጌ ነው እነዚህን ሕፃናት ያለ እናት የማሳድጋቸው?» አሉ፤ የአኔት እናት የገና በአልን በሰማይ ለማሳለፍ ወደዚያው ሄደዋልና።

## ምዕራፍ ሁለት

# የአኔት ሴት አያት መጡ



ከተወለደ ሦስት ሰዓት ብቻ የሆነው ሕፃን ዳንኤል በርኔ፥ የሰባት ዓመቷ አኔት ልዩ ንብረት ሆነ።

ደን የመንደሩ ነርስ ሕፃኑን ለመመገብና ለማጣጠብ ለተወሰነ ጊዜ ከነአኔት ጋር ቆየች። እርሷ ከሄደች በኋላ የአኔት አባት ሕፃኑን የምታሳድግ ሴት ቀጠረ። ይሁን እንጂ ሕፃኑ ዳኒ የአኔት ሆነ። ሰው ሁሉ የሚያስበው እንደዚሁ ነበር።

አኔት በእናቷ ሞት ምክንያት በመጀመሪያ የተሰማት ኀዘንና ድንጋጤ ካለፈ በኋላ፥ በብቸኛና ትንሽ ልቧ ውስጥ የነበረውን ፍቅር ሙሉ በሙሉ በሕፃን ወንድሟ ላይ አፈሰሰች። ሕፃኑ ሲጠባ ጡጦውን ትይዝለታለች፤ ባንቀላፋ ጊዜ ሲነቃ እንዳያጣት አልጋው አጠገብ ተቀምጣ ትጠብቀዋለች። ሌሊት ሲነቃም ወይም ሲያለቅስ ፈጥና የምትደርስለት አኔት ናት። ወደ ፎቁ በረንዳ እያወጣች ፀሐይ እንዲሞቅ ታደርገዋለች። ከአኔት በሚያገኘው ከልብ የሆነ ፍቅርና በፀሐይ ሙቀት ሕፃኑ ጠንካራ ሆነ። በመንደሪቱ ከነበሩት ሕፃናት ሁሉ እንደ እርሱ ጤነኛና ቆንጆ ልጅ አልነበረም። ሲተኛ፥ ሲነቃ፥ ሲስቅ፥ ሲመገብና ሲጫወት እንደገናም ሲተኛ ደስታ ሳይለየው አደገ። ማንንም ያስቸገረበትና ያስጨነቀበት ጊዜ አልነበረም።



«በዕድለኛ ኮከብ ነው የተወለደው፥» አለች አሳዳጊው ሴትዮ ትኩር ብላ እያየችው።

«በገና ኮከብ ብርሃን ነው የተወለደው። ሁልጊዜ ጤነኛና ደስተኛ የሚሆን ይመስለኛል፥» አለች አኔት ረጋ ባለ አነጋገር።

አቤት ዳኒ እንዴት አደገ! ፀሐይ በረዶን በሚያቀልጥበትና የዐደይ አበባ መስኩን መሙላት በሚጀምርበት ጊዜ ለሕፃኑ ልኩ የሚሆን ሌላ አዲስ ልብስ እንደሚያስፈልገው እነ አኔት አሰቡ። ላሞች ወደ ተራሮች የሚሄዱበት ጊዜ ሲደርስ የመጀመሪያ ጥርስ አበቀለ። አኔት ስለ መጀመሪያ ጥርስ ምንም ስለማታውቅ፥ በጥርሱ መብቀል ምክንያት ችግር ይደርሳል ብላ አልገመተችም፤ ሕፃኑም ቢሆን ስለዚህ ነገር ልብ ያለው ነገር አልነበረም። በመሆኑም በመነጫነጭና በማልቀስ ፈንታ ይስቅና እጁን ይነክስ ነበር።

ብዙም ሳይቆይ ሕፃኑ ዳኒ ከአልጋው እየወረደ ራሱን ችሎ ይንቀሳቀስ ጀመር። በአልጋውም ሊወሰን አልቻለም። ቤቱ ውስጥ ያሉ ዕቃዎችን ሁሉ ለመነካካትና ለማወቅ ፈለገ። አኔት አደጋ እንዳይደርስበት እየተከተለችና እየተንቀጠቀጠች ለጥቂት ሳምንታት ጠበቀችው። በኋላ ግን አንድ እግሩን በለሰለሰ ጨርቅ ከጠረጴዛ ጋር ስላሰረችው ርቆ ሳይሄድ ዙሪያውን ይጫወት ስለነበር ሕይወቷ ሰላማዊ ሆነ።

በዚህ ጊዜ ነበር፥ አንድ ቀን አኔት ዳኒን አልጋው ላይ አስተኝታ ወደ ሳሎን ስትሄድ አባቷ ራሳቸውን በሁለት እጃቸው ይዘው በምድጃው አጠገብ ቁጭ በማለት ሲተክዙ ያገኘቻቸው። አባቷ በጣም የሸበቱ፥ የአረጁና የደከሙ መስለዋል። ሚስታቸው ከሞቱ ወዲህ እንዲህ ያለ ሁኔታ ቢታይባቸውም፥ ዛሬ ብሶባቸዋል። አይዞህ በማለትና በማበረታታት እናቷን ለመተካት የምትጥረው አኔት ጉልበታቸው ላይ ቁጭ ብላ ለስላሳ ፊቷን በከሳና በገረጣው ፊታቸው ላይ ካስደገፈች በኋላ፥

«ምን ነው አባዬ? በጣም ደከመህ? ቡና ላፍላልህ?» አለቻቸው።

ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃዎች ያህል ዝም ብለው በፍቅርና በአድናቆት ስሜት ተመለከቷት። በተረት ዓለም እንዳሉ ቆንጃጅት ትንሽና ውብ ሆና ሳለች እንደ አስተዋይ ሴት ታየቻቸው! አባቷ ባለፈው አንድ ዓመት ጊዜ ችግራቸውን ለእርሷ የመንገርና ምክሯን

የማዳመጥ ልምድ አዳብረዋል። በዚሁ መሠረት አሁንም ራሷን ወደ ትከሻቸው ሳብ በማድረግ አቀፉአትና ስለ ችግሩ ሁሉንም ነገሯት፣ «ልጄ ሆይ፥ ከላሞቻችን የተወሰኑትን መሸጥ አለብን። ትንሽ ገንዘብ ያስፈልገናል፣ ያለዚያ ለክረምት የሚሆንሽ ጫማ መግዣ አይኖረንም፥» በማለት በኀዘን ገለጡላት።

አኔት ቀና አለችና በድንጋጤ ተመለከተቻቸው። ያሏቸው አሥር ላሞች ሲሆኑ፥ እያንዳንዳቸው እንደ ጓደኛ የሚፈቀሩ ነበሩ። ማንኛቸውም ቢሸጡ በጣም የሚናፍቋቸው ይሆናሉ። በመሆኑም ላሞች ሳይሸጡ ገንዘብ የሚገኝበትን ሌላ የተሻለ ዘዴ መፈለግ ነበረባት።

«አየሽ ልጄ፥» ቀጠሉ አባቷ ንግግራቸውን፣ «ሌሎች ወንዶች ሕፃናት ልጆቻቸውን የሚንከባከቡላቸው ሚስቶች አሏቸው። እኔ ግን ዳኒን ለምታሳድግልኝ ሴት ገንዘብ መክፈል አለብኝ። ይህ ደግሞ ብዙ ገንዘብ ያስወጣል። ያም ቢሆን አንድ ሰው ይህን ምስኪን ሕፃን ሊያሳድገው ያስፈልጋል።»

አኔት ቀጥ ብላ በወፍራሙ የተጎነጎነ ፀጉሯን ወደ ኋላዋ ወረወረች። ምን እንደሚደረግ በትክክል ዐወቀች። ማድረግ ያለባት ከአሳቧ ጋር እንዲስማሙ አባቷን ማሳመን ብቻ ነበር።

«አባዬ፥» አለች በቀስታ ተለይቶ በሚሰማ ድምፅ፣ «የዳኒ ሞግዚት ከእንግዲህ አያስፈልጉትም። እኔ አሁን ስምንት ዓመት ከስድስት ወር ሆኖኛል፣ ማንኛውም ሌላ ሰው እንደሚያደርገው ላሳድገው እችላለሁ። ለዚህ አገልግሎቴ ደግሞ ምንም እንድትከፍለኝ አያስፈልግም። ስለዚህ ላሞቹ መሸጥ የለባቸውም። ከእኛ ሲለዩ ምን ያህል እንደሚያዝኑ አስብ እስቲ አባዬ! ርግጠኛ ነኝ፥ በተለይ ቡሬ የምትባለው ላማችን እንደ ሰው ታለቅሳለች!»

«መማር እኮ አለብሽ። ትምህርት ቤት በመሄድ ፋንታ ቤት መቀመጥሽ ተገቢ አይደለም። በሕግም የተከለከለ ነው። የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ለምን እንደዚህ አደረጋችሁ ብለው ለከንቲባው ይነግሩብንና ችግር ይገጥመናል» አሉ አባቷ።

«ግንባሯን ቋጥር በማድረግ ዳኒን ማሳደግ እኮ ከትምህርት የበለጠ አስፈላጊ ሥራ ነው» ስትል መለሰችላቸው። ይህን ብትነግራቸው የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ችግራችን ይገባቸዋል። ደግ ሰው ናቸው፣ ጓደኛህም ናቸው። በዚህ መንገድ እንሞክርና የሚሆነውን ነገር



እንመልከት። ትምህርቴን እዚሁ ወጥ ቤት ውስጥ ሆኜ ጧት ጧት ለማጥናት እችላለሁ። ዳኒም ወለሉ ላይ ቁጭ ብሎ ይጫወታል። ይህ ደግሞ ለአራት ዓመታት ብቻ ነው የሚቆየው። ዳኒ አምስት ዓመት ሲሆነው ሕፃናት ትምህርት ቤት ይገባል። እኔም በዚያን ጊዜ እርሱን ትምህርት ቤቱ አደርሰውና ወደ ትምህርት ቤቴ እሄዳለሁ» አለች።

አባቷ እንደገና ትኩር ብለው ተመለከቷት። አኔት ትንሽ ልጅ ብትሆንም፥ ሕፃኑን የምትጠብቀው ልክ እንደ ትልልቅ ሴቶች ነበር። በቤት አያያዝ ሙያም ልምድ ነበራት። ነገር ግን እንደ ወጥና ረጅም የእግር ሹራብ መሥራት የመሳሰሉትን ሥራዎች የማከናወን አቅም አልነበራትም። ትምህርቷን ደግሞ መማር ነበረባት። አባቷ ለአምስት ደቂቃዎች ሲያሰላስሉ ቆዩና አንድ አሳብ መጣላቸው።

«ሴት አያትሽ ይመጡ ይሆን?» አሏት በድንገት። «አርጅተዋል፣ የቁርጥማት ሕመምም አለባቸው፣ ዓይኖቻቸውም በደንብ አያዩላቸውም። ቢሆንም ወጥ መሥራትና አንዳንድ ነገሮችን መጠጋገን አያቅታቸውም። ማታ ማታም ትምህርትሽን ያስጠኑሻል። እኔ ወደ ተራራው በምወጣበትና በማልኖርበት ጊዜም እርሳቸው ስላሉ ብቸኝነት አይሰማሽም። ትንሽ ልጅ ስለሆንሽ ቀኑን ሙሉ ብቻሽን ልትሆኚ አይገባም። ሴት አያትሽ የሚያስጠኑሽ መሆኑን ገልጬ ለትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ደብዳቤ ብጽፍላቸው ምናልባት ጉዳዩን በዝምታ ያልፉት ይሆናል» አሉ።

አኔት ከአባቷ ጉልበት ላይ በመውረድ ከመሳቢያ ውስጥ ሁለት ገጽ ወረቀትና አንድ እስክሪብቶ በማምጣት፥

«ለሴት አያቴና ለትምህርት ቤቱ ዲሬክተር አሁኑኑ ጻፍላቸው። ዳቦ ላመጣ ስሄድ ለሁለቱም በፖስታ ቤት በኩል እልክላቸዋለሁ። እንዲህ ካደረግን ከሁለቱም ቶሎ መልስ እናገኛለን» አለች።

በዚያው ሳምንት ውስጥ ለሁለቱም ደብዳቤዎች መልስ መጣ። ቀድሞ የመጣው መልስ በገመድ በደንብ የታሠረ የእንጨት ሳጥናቸውን ይዘው በባቡር የመጡት የአኔት አያት ራሳቸው ነበሩ። አያቷ ጎብጠዋል፣ መራመድ እስኪያቅታቸው ድረስም ድክምክም ብለዋል። አኔት ልትቀበላቸው ወደ ባቡር ጣቢያው ቀደም ብላ ሄዳለች፣ ባቡሩ በሣር የተሸፈነውን ሜዳ አቋርጦ በሸለቆው ውስጥ እንደ ትል ጥምዝምዝ እያለ ያልፍ ነበር። አንዲት ላም ባቡሩ ሀዲድ ውስጥ

በመግባቷ ባቡሩ ሊዘገይ እንደ ቻለ የባቡሩ ሹፌር በቁጣ ለሰዎች ተናገረ። ሾፌሩ ስለ ቸኮለ የአኔት አያት ከባቡሩ ለመውረድ ተቸግረው ነበር። ሳጥናቸውም ወደ ውጭ የተወረወረላቸው ባቡሩ ከተንቀሳቀሰ በኋላ ነበር።

የአኔት አያት በጊዜው በተፈጠረው ሁኔታ የተጨነቁ አይመስሉም። ምርኩዛቸውን ደገፍ እንዳሉ፥ ከባቡር ጣቢያው የእነ አኔት ቤት እስካለበት ተራራ ድረስ እንዴት ለመሄድ እንደሚቻል ጠየቁ። ስለ ቁርጥማት በሽታ ምንም የማታውቀው አኔት፥ «በእግራችን እንሂድ» አለች። አያቷ ይህን ሲሰሙ «ጅል» አሏት። በመጨረሻ፥ ተራራው ላይ ካለችው መንደር ወደ ባቡር ጣቢያው አይብ አድርሶ የሚመለስ የዕቃ ማጓጓዣ ጋሪ አገኙና ለምነው ተሣፈሩ። መንገዱ ድንጋያማ፥ የጋሪው መሽከርከሪያ እግር ከእንጨት የተሠራ ለበቅሎ የሚያንሸራትት ነበር። እንዲያ ባለ መንገድ ላይ በጋሪ መጓዙ ከአያቷ ይልቅ አኔትን አስደሰታት። አያቷም ቢሆኑ ጥርሳቸውን ነክሰው ዝም አሉ፤ ቅሬታቸውንም አልገለጡም። ቤት ደርሰው አያቷ ምድጃ ዳር ባለው ሶፋ ወንበር ላይ አረፍ ብለው ሕመምተኛ ጀርባቸውን ትራስ ላይ አስደግፈው በነበረበትና አኔትም ሻይ ልታፈላላቸው ጉድጉድ ማለት ስትጀምር የድካም እፎይታ አሰሙ።

ሕፃኑ ዳኒ እየተንፏቀቀ ከጠረጴዛ ሥር ብቅ አለ። አያቱን ሲያይ የእጆቹን ሦስት ጣቶች አፉ ውስጥ ከተተና ሳቀ። እርሳቸውም በደንብ ሊያዩት መነጽራቸውን አደረጉ። ለጥቂት ጊዜ እርስ በርሳቸው ፊት ለፊት ተያዩ። ዕድሜ ያፈዘዛቸው ዓይኖቻቸው ብሩህ ሰማያዊ በሆኑት በዳኒ ዓይኖች ላይ አረፉ። ከዚያም ዳኒ ራሱን ወደ ኋላ እያስተኛ እንደገና ሳቀ።

«ይህ ልጅ በእንፉቅቁ እየሄደ ሱሪውን ይጨርሳል። በመዳህ መሄድን መማር አለበት» አሉ አያቱ፥ የቀረበላቸውን ዳቦ ቆረስ አድርገው እየተመገቡ።

የቀረበላቸውን ዳቦና ሻይ እስኪጨርሱ ድረስ ከዚህ ሌላ ቃል አልተናገሩም። ከዚያ በኋላ ጥቁር ቀሚሳቸው ላይ የወዳደቀውን የዳቦ ፍርፋሪ አራገፉና ምርኩዛቸውን ተደግፈው በቀስታ ተነሡ።

«እንግዲህ መጥቻለሁ። የምችለውን እሠራለሁ፤ የማልችለውን አንቺ ትሠሪልኛለሽ» ብለው ተናገሩ። አኔት፥ «ልጁን ቀና



አድርጊውና ውኃ ቤቱን አስጎብኚኝ» አሉ። ከዚያን ዕለት ጀምሮ የእነ አኔት አያት የሚችሉትን ሲሠሩ ሌላውን አኔት እየሠራች ቤተሰቡ በጥሩ ሁኔታ ይኖር ጀመር። ሴት አያቱ ደስ ባይላቸውም እንኳ ጠረጴዛው እግር ዙሪያ በእንፉቅቁ መሄድን ያልተወ ዳኒ ብቻ ነው ። አኔት ወደ መንደሩ መደብር ...ካ ከሱፍ የተሠራ ጥቁር ልብስ የገዛችው በዚህ ምክንያት ነበር። አያታቸው ያን የሱፍ ጨርቅ እየቆራረጡ በዳኒ ሱሪዎች ሁሉ ላይ ከኋላ ሰፉት። በዚህ መንገድ የጥቁር ጨርቅ እራፊዎች የተጣፉባቸውን ሱሪዎች መታጠቅ የተለመደ ባይሆንም፥ ጨርቆቹ የተጣፉበትን ዓላማ የተሳካ አድርገዋል። ሆኖም ዳኒ ስለሚቀመጥበት ጨርቁ ብዙ ጊዜ አይታይም ነበር።

የአኔት አባት ለጻፉት ሁለተኛ ደብዳቤም መልሱ መጣ። የመጣው መልስ ራሳቸው የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ነበሩ። ዲሬክተሩ አንድ ቀን፥ ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ድከም ባለ አካሄድ ከሸለቆው ወደ ተራራው በመውጣት ወደ እነ አኔት ቤት መጡ። የአኔትን አባት አቶ በርኔን ሊያነጋግሩ ፈልገዋል። አቶ በርኔ ግን ላም ያልቡ ነበርና ዲሬክተሩ ሲመጡ በላሞች በረት መስኮት በኩል አዩአቸው። በክርክሩ እንዳይሸነፉ ስለ ፈሩ፤ ከትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ጋር ለመከራከር አልፈለጉም። ስለዚህ በጓሮ በር ሮጠው በመሄድ ቆጥ ላይ ተደበቁ። መኖሪያ ቤቱ ሳሎን ውስጥ ተቀምጣ ወደ ውጭ ትመለከት የነበረችው አኔት፥ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር በቤቱ ዙሪያ እንደ ደረሱ የአባቷን እግሮች መሰላሉን መውጣት ጨርሰው ወደ ቆጡ ሲወጡ አየች፤ ከዚያም አባቷ ከእርሷ የሚጠብቁትን በትክክል ተረዳች።

በሩን ከፈተችና ዲሬክተሩ ወደ ቤት እንዲገቡ ጋበዘቻቸው። ሲገቡም ቤቱ ውስጥ ካሉት ሁሉ እጅግ የሚያምረውን ቀይ ወንበር በታላቅ ትሕትና አቀረበችላቸው። አኔትን በጣም ይወዷታል፤ እርሷም በጣም ትወዳቸዋለች። ዛሬ ግን ትንሽ ተፈራርተዋል። የአኔት አያት እጆቻቸውን ጭናቸው ላይ በማጣመር ወደ ጦርነት እንደሚሄድ ፈረስ ቀጥ ብለው ተቀምጠዋል።

ዲሬክተሩ የፍርሃት ሳል እየሳሉ፥ «አባትሽን ላነጋግረው ነው የመጣሁት» አሉ። «የማነጋግረው የአንቺን ትምህርት ማቋረጥ አስመልክቶ ስለ ጻፈልኝ ደብዳቤ ነው። እንዳንቺ ያለች ትንሽ ልጅ ትምህርት ማቋረጧ ተገቢ ነው ብዬ አላስብም። ከዚህም ሌላ ድርጊቱ የመንግሥትን ሕግ ይጻረራል።»

«እርስዎ ካልገለጡ በቀር መንግሥት ስለ እርሷ ምንም አያውቅም። ደግሞም ልጅቱን እኔ ራሴ አስተምራታለሁ። እንደ ዳኒ ያለን ሕፃን ልጅ ጠባቂ እኅቱን ወስዶ ብቻውን ማስቀረት ተገቢ አይመስለኝም፥» አሉ የአኔት አያት።

«እርስዎ ሊጠብቁት አይችሉም?» አሉ በርጋታ ዲሬክተሩ።

«ፈጽሞ አልችልም። ዐይኖቼ አጥርተው ስለማይመለከቱ የሕፃኑን እንቅስቃሴ ማየቱ ለእኔ ችግር ነው። እጆቼ በቁርጥማት ሕመም ስለሚጠቁ፥ ቢወድቅ እንኳ ላነሣው አልችልም። ሕፃኑ እንደሆነ እንደ ፈጣን ባቡር ነው የሚሽከረከረው። የሰማኒያ ዓመቷ አሮጊት እንዴት እችለዋለሁ? የሚናገሩትን አያውቁም፥» አሉ አያቲቱ ቆጣ ብለው።

ዲሬክተሩ ዳኒን ትኩር ብለው አዩት። ሕፃኑ ለማገዶነት የተዘጋጀውን የእንጨት ፍቅፋቂ አጎንብሶ ይበላል። ከሰውነቱ የሚታየው፥ ሱሪው ላይ በመቀመጫው አቅጣጫ የተሰፋለት ጥቁር ጨርቅና የፋፋ እግሮቹ ብቻ ነበሩ። ዲሬክተሩ ይህን ሲመለከቱ በርግጥ ሴትዮይቱ ሕፃኑን ሊይዙት እንደማይችሉ ተገነዘቡ።

ዲሬክተሩ ምን ማድረግ እንደሚችሉ አላወቁም። ጓደኛቸው የሆኑት የአኔት አባት ምናልባት የተሻለ አሳብ ይኖራቸው ይሆናል ብለው አሰቡና ወደ አኔት ዘወር ብለው፥ «መቼ ነው አባትሽ የሚመጣው፥ አኔት?» አሉ።

«አላውቅም። ወደ ውጭ ወጥቷል! ትንሽ ይቆይ ይሆናል። መጠበቁ ምንም አይጠቅምዎትም፥» አለች አኔት ሳትጠራጠር ዲሬክተሩ በሸለቆው ወደ ታች እንደ ሄዱ አባቷ ወዲያው የሚመጡ መሆኑን በማወቅ።

የትምህርቱ ቤቱ ዲሬክተር ዝም ብለው ማሰላሰል ጀመሩ። ጥሩ ሰው በመሆናቸው አኔት ላለባት ኃላፊነት ያስቡ ነበር። ነገር ግን የአኔት አባት የብዙ ጊዜ ጓደኛቸው ስለሆኑ ለሕግ አሳልፈው ሊሰጧቸው አልፈለጉም! በተለይም አኔት ሕፃኑን ለመንከባከብ ቤት ውስጥ እንድትሆን ማስፈለጉ ግልጽ ስለነበረ በመጨረሻ አንድ አሳብ መጣላቸው። አሳቡ በጣም ጥሩ ባይሆንም፥ ምንም ካለማሰብ ይሻላል።

«ነገሩ በአንድ ቅድመ ሁኔታ ብቻ እንዲፈታ አደርጋለሁ፤ ይኸውም አኔት በየሳምንቱ ቅዳሜ ጠዋት ዳቦ ለመውሰድ ወደ መንደራችን ስትመጣ እንድትጎበኘኝ በማድረግ እፈትናታለሁ።



በትምህርቷ መሻሻል ከታየባት ምንም አልናገርም። የማትማር መሆኗን ከተረዳሁ ግን፥ እንደ ማንኛውም ልጅ መማር አለባት ብዬ የማስገደድ ኃላፊነት አለብኝ» አሉ።

ዲሬክተሩ ሲናገሩ ኮስተር ለማለት ሞከሩ፤ አኔት ግን ብሩህ ፈገግታ ታሳያቸው ነበር። ሕፃኑ ዳኒ ደግሞ ለቤተሰቡ ድል እንደ ሆነለት ተሰምቶት ከአጎንበሰበት ድንገት ቀና ብሎ ከተስተካከለ በኋላ እንደ ዶሮ ጮኸ። ዲሬክተሩ ፈገግ ብለው እናት የሌላቸውን የሚያማምሩ ልጆች በፍቅር ዐይን በማየት ተሰናብተዋቸው ሄዱ። አኔት፥ ዲሬክተሩ ርቀው መሄዳቸውን ካረጋገጠች በኋላ አባቷ ወደ ተደበቁበት ሄዳ ካሉበት ቆጥ እንዲወርዱ አደረገች። ከዚያም ከዲሬክተሩ የሰማችውን መልካም ዜና ነገረቻቸው።

በዚሁ መሠረት አኔት ሁልጊዜ ቅዳሜ ጠዋት ዲሬክተሩ ወደሚኖሩበት ነጭና ረጅም ቤት ትሄዳለች። የዳቦ ቅርጫቷን እንዳዘለችና የተቦጫጨቀ ደብተሯን እንደ ያዘች የፊት ለፊቱን በር ታንኳኳለች። ዲሬክተሩ በደስታ ወደ ቤት እንድትገባ ይጋብዟታል። በክረምት ምድጃ ዙሪያ ተቀምጠው ቅመም የበዛበት ኬክ ይመገባሉ፤ ትኩስ ወተት ይጠጣሉ። በበጋ ደግሞ በረንዳቸው ላይ ቁጭ በማለት ፍራፍሬዎችና ጭማቂ ይመገባሉ። ፈተናው የሚጀምረው ከዚያ በኋላ ነበር።

ፈተናው ሁልጊዜ የሚጀምረው በሂሳብ ትምህርት ነበር። አኔት ግን በሂሳብ ትምህርት ጎበዝ አልነበረችም። ዲሬክተሩ ለጥቂት ደቂቃዎች ይጠይቋትና አኔት መመለስ ሲያቅታት በዚያ ሁኔታ መቀጠሉ ጊዜ ማጥፋት እንደ ሆነ በመገመት ወደ ታሪክ ትምህርት ጥያቄዎች ይሸጋገራሉ። እዚህ ላይ ለአኔት ምንም ዐይነት ጥያቄ አያስፈልግም ነበር። ቁጭ እንዳለች ጉልበቷን ገጥማ ወደፊት በማዘንበል የስዊዘርላንድን ታሪክ ትተርካለች። ዊልያም ቴል የተባለው ታዋቂ አርበኛ ላገሩ ነጻነት ያደረገውን ተጋድሎና ትንሹ ልጁ በራሱ ላይ የነበረው ፍሬ በሚምዘገዘግ ቃላት እስኪቆራረጥ ድረስ በድፍረት በጀግንነት እንዴት እንደ ቆመ ትናገራለች። እነዚህን ስለ መሳሰሉ የስዊዘርላንድ አርበኞች አኔት በሚገባ ታውቃለች። አኔትና ዲሬክተሩ በፈገግታ ይተያዩ ነበር። ሁለቱም ጀግንነትን ስለሚወዱ ደስ ብሏቸዋል። ከዚህ በኋላ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይገባሉ። በየምሽቱ ድምጽዋን ከፍ አድርጋ ለሴት አያቷ ስለምታነብላቸው፥

አኔት መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ እያወቀች ሄደች። በዚህ ጊዜ ዲሬክተሩ የሂሳብ ትምህርት ስለ ከበዳት አኔትን መውቀሱን ዘንግተውታል። በዚህ ፈንታ የሚነበቡ አዳዲስ መጻሕፍትን ይሰጧታል። በዳቦ ቅርጫቷ ባዶ ቦታ ደግሞ ብስኩቶችንና በብርማ ወረቀት የተጠቀለለ ቸኮላት ይሞሉላታል። ከዚያም የደህና እንገናኝ ሰላምታ ይለዋወጡና ይለያያሉ። ዲሬክተሩ በራፍ ላይ ቆመው አኔት በጥዱ ጫካ ጠርዝ እስከትደርስ ድረስ ይመለከቷታል። ምክንያቱም ሁልጊዜ ፊቷን አዙራ እጇን ታውለበልብላቸዋለች።

ዲሬክተሩ ከዓመታት በፊት ተራራማው አካባቢ የምትኖርና ወርቅማ ፀጉር ያላት አንዲት ልጅ አፍቅረው ነበር። አሁን የሚኖሩበትን ቤት ገዝተው በጥሩ ሁኔታ ያሳደሱትም ለእርሷ ነበር። ክፉ አጋጣሚ ሆነና አንድ ቀን አበባ ለመልቀም ወደ ውጭ እንደ ወጣች በድንገት የወረደ በረዶ ገደላት። በዚህ ምክንያት ዲሬክተሩ ብቻቸውን ኖሩ። በሕልማቸው ግን ሁልጊዜ ትታያቸዋለች። እርሷን ብቻ ሳይሆን በሕልማቸው የተጎነጎነ ወርቃማ ፀጉር ያላትን፣ የዓይን ብሌኗ ሰማያዊ የሆነ ትንሽ ሴት ልጅን እግራቸው ሥር በበርጩማ ላይ ተቀምጣም ይመለከቱ ነበር። አኔት ወደ ቤታቸው ስለ መጣች የዲሬክተሩ ሁለተኛ የሕልም ክፍል በየቅዳሜው ጠዋት ጠዋት እውን ሆነ።



## ምዕራፍ ሦስት

## በጣም ልዩ የገና ስጦታ



ዕለቱ ይህ ታሪክ ከተጀመረ ከአምስት ዓመት በኋላ የሚከበር የገና በዓል ዋዜማ ነበር። የያኔው ሕፃን ዳኒ አሁን የአምስት ዓመት ልጅ ሆኗል። ለዳኒ ይህ ልዩ ቀን ነበር። ምክንያቱም በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በገናው በዓል ላይ ለመገኘት የሚችል ትልቅ ልጅ እንደሆነ ተቆጥሮ ከአኔት ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሄድና የገናውን ዛፍ እንዲመለከት ተፈቅዶለታል።

ቀና ብሎ አልጋው ላይ በመቀመጥ በኩባያ የተሰጠውን የድንች ሾርባ ይጠጣ ጀመር። ወደ ንጣቱ የሚያደላው ነጭ ፀጉሩ በጣም ወፍራምና ፀጉራም ከሆነው የአልጋ ልብስ በመጠኑ ነው ብቅ ብሎ የሚታየው። አኔት የድብ ቅርጽ ያለውን የሚያምር ብስኩት ይዛ አጠገቡ ተቀምጣለች።

«አዝናለሁ ዳኒ። ይዘሽው ልትተኛ አትችልም። እንዲያ ካደረግክ ጠዋት ስትነሣ ተሰባብሮ ነው የምታገኘው። ተመልከት፣ እዚህ ቁም ሳጥኑ ውስጥ አስቀምጠዋለሁ። በምሽት የጨረቃይቱ ብርሃን ስለሚያበራበት ይታይሃል» አለች፣ የድብ ቅርጽ ያለውን ብስኩት እየተመለከተች። አነጋገሯ ጠንከር ያለ ነበር።

ዳኒ ከአኔት ጋር ለመጨቃጨቅ አፉን ከከፈተ በኋላ አሳቡን ለወጠና አፉን በሾርባው ሞልቶ ዝም አለ። የብስኩት ድቡን አቅፎ እንዳያድር አለመፍቀዷ ትክክል አልመሰለውም። ቢሆንም የሚያስደስቱ ሌሎች ነገሮች ነበሩ። ዳኒ ማለዳ ከእንቅልፉ ከነቃበት መሽቶ እስከሚተኛ

ድረስ ሁልጊዜ ደስተኛ ነበር። በተለይ በዛሬው ምሽት የደውል ድምፅና አንጸባራቂውን የገና ዛፍ ስለ አየ፥ በከዋክብት ብርሃን እየተመራም ውጭ ባለው የበረዶ ክምር ላይ ስለ ተንሸራሸረ እጅግ ደስ ብሎታል። ሾርባውን ከጨለጠ በኋላ ኩባያውን ለአኔት ሰጣት። ከዚያም ፀጉራሙን የአልጋ ልብስ እንደ ማቀፍ አደረገና!

«ነጠላ ጫማዬን መስኮቱ ደፍ ላይ ባስቀምጠው የገና አባት የሚመጣ ይመስልሻል?» ብሎ ጠየቃት። አኔት ከዳኒ በሰማችው ጥያቄ ተገረመች። ልጁ እንዲህ ያለ ነገር ከየት ሰማ ብላም አሰበች። ምክንያቱም የገና አባት እንግሊዝ ውስጥ የሚታወቀውን ያህል ስዊዘርላንድ ውስጥ አይታወቅም ነበር። የስዊስ ሕፃናት የጣፋጭ ምግብ ስጦታዎችን ከገና ዛፍ ሥር ያገኛሉ። ከወላጆቻቸው የሚቀርቡላቸውን ስጦታዎች የሚቀበሉት ደግሞ በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ነው። በገና ዕለት ልጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ቢጋበዙም፥ ሽልማት የሚያገኙት ግን ጥቂቶች ናቸው።

የጀመረውን ጥያቄ ቀጠለ ዳንኤል፥ «የገና አባት የሚመጣው በአጋዘን በሚጎተትና በረዶ ላይ በሚንሸራተት ጋሪ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ። እንደዚያ ይመጣና በጥሩ ልጆች ነጠላ ጫማ ውስጥ ስጦታዎችን ያስቀምጣል። እኔ ጥሩ ልጅ ነኝ፥ አኔት?»

«አዎ፥ በጣም ጥሩ ልጅ ነህ» አለች አኔት ሳም አድርጋው፥ «አንተ ግን ከገና አባት ስጦታ አታገኝም። እርሱ የሚሄደው ሀብታም ወደ ሆኑ ትንንሽ ልጆች ነው።»

«እኔ ሀብታም ልጅ አይደለሁም?» አለ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ከሕይወት ያገኘ የሚመስለው ዳኒ።

«አይደለህም! ሀብታም ልጅ አይደለህም። እኛ ድሃዎች ነን! እኛን ለማስተዳደር አባታችን ተግቶ ለመሥራት ይገደዳል። እኔና ሴት አያቴ ደግሞ በየጊዜው የሚቀዳደዱ ልብሶችህን ስንሰፋ ነው የምንኖረው። አዳዲስ ልብሶችን እንዳንገዛልህ ገንዘብ የለንም» አለች አኔት።

ዳኒ ሳቅ አለና፥ «ድሃ ብሆን ግድ የለኝም! ድህነትን እወደዋለሁ። ይልቅስ እስቲ ስለ ገና በዓል፥ ስለ ሕፃኑ፥ ስለ ላሞቹ እና ስለ ትልቁ አንጸባራቂ ኮከብ ታሪክ ንገሪኝ» አለ።

በጥያቄው መሠረት አኔት ታሪኩን ለዳኒ ዘርዝራ ነገረችው። መተኛት የነበረበት ዳኒ ዓይኖቹን አፍጥጦ ታሪኩን በጉጉት አዳመጠ።



«ከምቹ ስፍራ ይልቅ በታሪኩ ውስጥ እንደ ነገርሽኝ ባለ በረት ውስጥ ድርቆሽ ሣር ላይ ብተኛ እወዳለሁ። ሕፃኑን በትንፋሿ ባሞቀችው ላም አጠገብ መተኛትም ደስ የሚል ነገር ይመስለኛል» አለ ዳኒ አኔት የነገረችውን ታሪክ ከሰማ በኋላ።

«በረት ውስጥ፥ ሣር ላይ መተኛትንማ መመኘት የለብህም። በክረምት አልጋ በሌለበት ቦታ እንደዚያ ባለ ቦታ ብትተኛ በጣም ስለሚበርድህና ስለማይመችህ የሚሞቅ አልጋ ትመኝ ነበር። በታሪኩ እንደ ሰማኸው ያንጊዜ ለተወለደው ሕፃን የሚሞቅ ስፍራ የከለከሉትና በረት ውስጥ እንዲያድር ያደረጉ ሰዎች ጨካኞች መሆን አለባቸው። የሚሞቅና የሚመች ስፍራ ሊያዘጋጁለት ይችሉ ነበር።»

እንዲህ ሲነጋገሩ ሳለ፥ ግድግዳው ላይ ያለው ሰዓት ከምሽቱ ሦስት ሰዓት መሆኑን ደወለ። አኔት ብድግ አለችና፦

«ተኛ ዳኒ፥ ለአባዬ እራቱን ማዘጋጀት አለብኝ» አለች።

እቅፍ አድርጋ በመሳም ካስተኛችው በኋላ፥ የመኝታ ቤቱን መብራት አጠፋችና ወጣች። ዳኒ ግን እንቅልፍ አልወሰደውም። በመስኮቱ በኩል ውጭ ወዳለው ጨለማ አፍጥጦ ያስብ ጀመረ።

ዳኒ ስግብግብ ልጅ ባይሆንም፥ የገና አባት ምናልባት ወደ ቤታቸው ቢመጣና ካለመዘጋጀታቸው የተነሣ ስጦታውን ሳያገኙ ቢቀሩ ሁኔታው የሚያሳዝን እንደሚሆን ማሰላሰሉ አልቀረም። ዳኒ ድሃ ልጅ በመሆኑ፥ የገና አባት ወደ እነርሱ ቤት አይመጣ ይሆናል። ቢሆንም ይመጣ ይሆናል ብሎ ማሰብ ይገባል። ጠዋት ምንም ባይገኝበትም ነጠላ ጫማውን ውጭ ማሳደሩ ምንም ጉዳት የለበትም። ጥያቄው ነጠላ ጫማው የት ይቀመጥ? የሚለው ነበር። መስኮቱ ደፍ ላይ እንዳያስቀምጠው፥ የመስኮቱን ተጣጣፊ የብረት መጋረጃ ሊከፍተው አይችልም። ከቤቱ ፊት ለፊት እንዳያስቀምጠው፥ ቤተሰቡ ሁሉ ሳሎን ውስጥ ስለሆኑ ያዩታል። ብቸኛው ምቹ ስፍራ ጓሮ፥ በወጥ ቤቱና በከብቶች ሣር ማከማቻ መካከል ያለው ነበር። የገና አባት እዚያ ድረስ ሄዶ ነጠላ ጫማውን አያየው ይሆናል። ቢሆንም ጫማውን ማስቀመጥና መሞከሩ ምንም አይጎዳም።

ዳኒ ሲያሰላስል ቆየና በመጨረሻ ወሰነ። በዚሁ መሠረት ከአልጋው ወረደና በቀስታ በመራመድ ከመኝታ ቤቱ ወጥቶ በሮቹ ደረጃዎቹ ወደ ታች ወረደ። እንቅስቃሴው እንዲሰማበት ስለአልፈለገ ያለጫማ

ነበር የሚራመደው። አንድ ደማቅ ቀይ ነጠላ ጫማ ይዟል። ነጠላ ጫማው ከጥንቸል ቆዳ ጭምር የተሠራ ሲሆን፥ አኔት ነበረች የሠራችለት። ጫማው ያልተለመደ ዓይነት ደማቅ ቀለም ያለው በመሆኑ፥ የገና አባት በሩቁም ቢሆን ያየው ይሆናል ብሎ ዳኒ አሰበ። ወጥ ቤቱ መዝጊያ ላይ ያለውን የእንጨት መቀርቀሪያ መነተቱ አስቸጋሪ ስለሆነ፥ በሩን ለመክፈት ዳንኤል ወንበር ላይ መቆም ነበረበት። በሩን እንደ ከፈተ መሬት ላይ የረጋው በረዶና የከዋክብት ብርሃን ታየው። ትንፋሹ መቆም እስኪቃጣው ድረስ የውጭው ቀዝቃዛ ንፋስ እንደ ስለት ወጋው። ነጠላ ጫማውን ወደ ደረጃው ዝቅ አደረገና በሩን በፍጥነት ዘጋው።

ይህን ካደረገ በኋላ ደስ እያለው ወደ መኝታው ተመለሰ። መኝታው ውስጥ ገባና አፍንጫውን ትራሱ ውስጥ በመቅበር ጥቅልል ብሎ ተኛ። ቀደም ሲል ከመተኛቱ በፊት ከአኔት ጋር የጸለየ ቢሆንም፥ እንዲህ በማለት ጥቂት ጨመረበት፦

«ውድ እግዚአብሔር ሆይ፥ እባክህ የገና አባት ከአጋዘኑ ጋር በዚህ በኩል እንዲያልፍ አድርገው። እኔ ምንም ድሃ ልጅ ብሆን፥ የገና አባት ቀይ ነጠላ ጫማዬን አይቶ በላዩ ትንሽ ስጦታ እንዲያስቀምጥልኝ አድርገው።»

ዳኒ መኝታው ውስጥ ጥቂት እንደ ቆየ እንቅልፍ ሸለብ አደረገውና ወደ ሕልም ዓለም ገባ። በዓለም ላይ እንዳሉት ሌሎች ሕፃናት እርሱም የገና አባት ቀይ ልብስ ለብሶ በበረዶ ላይ ሲራመድ ታየው።

ከእንቅልፉ የነቃው በጠዋት ነበር። በገና ዕለት፥ ሕፃናት በጠዋት ነው የሚነቁት። እንደ ነቃ ያስታወሰው ውጭ ያስቀመጠውን ቀይ ነጠላ ጫማ ነበር። ልቡ በፍርሃት ይመታ ጀመር። አልጋው ላይ እንደሆነ ቀና አለና አኔት መንቃት አለመንቃቷን ተመለከተ።

አልነቃችም፤ ከባድ እንቅልፍ ወስዷታል። ረጅም ፀጉሯ ትራሷ ላይ ተበትኗል። ገና እኩለ ሌሊት ሳይሆን አይቀርም ብሎ ገመተ ዳኒ። አባቱ ወጥ ቤት ውስጥ የወተት ማለቢያ ዕቃዎችን ሲያንኳኳ ባይሰማ ኖሮ በዚሁ ግምቱ ይጸና ነበር።

ስለዚህ የገና ማለዳ ሆኗል። ዳኒ ቶሎ ካልተነሣ፥ አባቱ በሩን ከፍቶ ሲወጣ የገና አባት ያመጣለትን ስጦታ ቀድሞ ያገኘዋል። መቼም የገና



ስጦታ እንደሚመጣለት ዳኒ እርግጠኛ ነበር። ማታ የነበረበት ጥርጣሬ በእንቅልፉ ጊዜ ጠፍቷል።

አኔትን እንዳይቀሰቅሳት እየተጠነቀቀ ከመኝታ ክፍሉ ወጣና አባቱ የወተት ዕቃዎችን ወደሚያጣጥቡበት ወጥ ቤት ሄደ። ሁለት እጆች እግራቸውን ጥርቅም አድርገው እስኪይዟቸው ድረስ የዳኒ አባት ምንም አላዩም ነበር። ጎንበስ ብለው ሲመለከቱ፥ ብሩህ ዓይኖችና በወጉ ያልተያዘ ፀጉር ያለውን ልጃቸውን ነበር ያዩት።

«የገና አባት መጥቶ ነበር?» አለ ዳኒ አባቱን ወደ ላይ እየተመለከተ። ዘግይቶ የተኛውና በማለዳ የተነሣው አባቱ የቃጭልና በበረዶ ላይ የሚሄድ የእርምጃ ድምፅ ከውጭ ሳይሰማ እንዳልቀረ ዳኒ እርግጠኛ ሆነ።

«የገና አባት?» አሉ የዳኒ አባት ግራ በተጋባ ድምፅ፥ «አልመጣም ኧረ! ወደዚህ አልመጣም። እኛ የምንኖረው በተራራማው አካባቢ ስለሆነ ወደዚህ መምጣቱ ያስቸግረዋል።»

«ለገና አባት በሚያስቸግር ስፍራ አይደለም ያለነው። ቢሆንም በአጋዘን የሚሳብ ጋሪው የትም ሊወስደው ይችላል። ስለ ተኛህ መምጣቱን አልሰማህ ይሆናል። በሩን ክፈትልኝ እስቲ አባዬ፥ ምናልባት የገና አባት ስጦታ አምጥቶልኝ ይሆናል» አለ ዳኒ እየጓጓ።

የዳኒ አባት የልጃቸውን ለገና ስጦታ ያለውን ጉጉት ቀደም ብለው ቢረዱ ኖሮ አንድ ጣፋጭ ነገር ጫማው ላይ ያስቀምጡለት እንደ ነበር አሰቡ። ልጁ ስጦታ አጥቶ ቅር ሲለው ማየቱን አልፈለጉትም። ቢሆንም የወተት ማለቢያ ዕቃዎችን ወደ ከብቶች በረት ለማስገባት የጓሮውን በር መክፈት ነበረባቸው። ስለሆነም በሩን ለመክፈት መወርወሪያውን ሳብ አደረጉ። በዚህ ጊዜ ዳኒ በአባቱ እግሮች መሀል እንደ ተራበች ጥንቸል በፍጥነት ሾልኮ ወጣና ነጠላ ጫማው በነበረበት ስፍራ ተንበረከከ።

ወዲያው ከፍ ያለ የደስታ ድምፅ አሰማና ጫማውን በሁለት እጆቹ ይዞ በሩጫ ወደ ወጥ ቤቱ ተመለሰ።

ተአምር ነው! የገና አባት ለዳኒ ስጦታ አምጥቶለታል። ዳኒ በደስተኞቹ አምስት ዓመታት ዕድሜው እንዲያ ያለ ቆንጆ ስጦታ አግኝቶ አያውቅም።

ቀይ ነጠላ ጫማው ውስጥ ያገኛት አንዲት ትንሽ የድመት ግልገል ነበረች። የዓይኖቿ ቀለሞች ሰማያዊ ሲሆኑ፥ አፍንጫዋ ላይ ጥቁር ነገር አለባት። ከሲታና ቀጭን ግልገል ናት። ከርሃብና ከብርድ የተነሣ ልትሞት ትንሽ ነው የቀራት። ዳኒ ጫማ ላይ ካለው የጥንቸል ፀጉር ትንሽ ሙቀት ባታገኝ ኖሮ ትሞት ነበር። አሁን ግን ትንሽ ትንሽ ትተነፍሳለች። የዳኒ አባት የወተት ማለቢያ ዕቃዎቹን ሁሉ ረስተው፥ ወጥ ቤቱ ወለል ላይ ልጃቸው አጠገብ ተንበረከኩና የግልገሏን ሕይወት ለማትረፍ የቻሉትን ሁሉ ያደርጉ ጀመር።

በመጀመሪያ በሚሞቅ ለስላሳ ጨርቅ ጠቀለሉና ሞቃቱ ምድጃ አጠገብ አስቀመጧት። ከዚያም ሁለቱ ተጋግዘው ወተት አሞቁና መጥባት ስለማትችል በማንኪያ ይመግቧት ጀመር። በመጀመሪያ ወተቱን መዋጥ ስለ አስቸገራት ወደ ውጭ ተፋችው። በኋላ ግን ምላሷን ወደ ውጭ እያወጣች ወተቱን ትውጠው ጀመር። ይህን ስታደርግ ዓይኖቿ ይከፈቱ፥ ወተቱንም ትወደው ጀመር። ለአምስት ደቂቃዎች ያህል እንደ ቆየች ጅራቷን እያወዛወዘች ተንጠራራች። የሚበቃትን ያህል ከጠጣች በኋላ፥ እንደ ኳስ ጥቅልል ብላ በመተኛት የኩርር ኩርርታ ድምፅ ታሰማ ጀመር።

ይህ ሁሉ ሲሆን፥ ዳኒና አባቱ አሳባቸው በሚያደርጉት ነገር ተይዞ ስለ ነበር አንድም ቃል አልተለዋወጡም። በኋላ ግን ሥራቸው ለጊዜውም ቢሆን በጥሩ ሁኔታ ስለ ተከናወነ ቁጭ አሉና ተያዩ። የዳኒ ጉንጮች ቀላ ብለው ዓይኖቹ እንደ ከዋክብት ያበሩሉ።

«የገና አባት እንደሚመጣ አውቅ ነበር» አለ ዳንኤል በሹክሹክታ፥ «እንዲህ ያለች ውብ ስጦታ እንደሚያመጣልኝ ግን በፍጹም አልገመትኩም። በሕይወቴ ሁሉ አግኝቼው የማላውቀው ውብ ስጦታ ናት። ስሟን ምን ልበለው አባዬ?»

«በገና በዓል መልአክ ስም ክላውስ ብለህ ብትጠራት ጥሩ ነው። በእውነቱ በተአምር የተገኘች ያህል ነው አመጣጧ» አሉ አባቱ።

ይህን ከተናገሩ በኋላ ግልገሊቱን ለዳኒ ትተዋት ወደ ከብቶቹ በረት ሄዱ። ደብዛዛ ብርሃን ባለው በረት ውስጥ እራሳቸውን ላሞቹ ጎን ላይ አስደግፈው ወተቱ ባልዲ ውስጥ አረፋ ሲፈጥር እየተመለከቱ፥ ስለ ግልገሊቱ ለዳኒ ሊገልጡለት ስለሚገባው ነገር አሰላሰሉ። ግልገሊቱ ከከብቶች በረት የመጣች መሆኗ ይታወቃል። ዳኒ ነጠላ ጫማ ላይ




ተቀምጣ መገኘቷና የእርሱ መሆኗ ይደንቃል። ምናልባትም ነገሩ አያስደንቅ ይሆናል ብለው አሰቡ የዳኒ አባት ከጥቂት ጊዜ በኋላ። በገና በዓል ዋዜማ ሌሊት በሰማይ የሚገኝ የሁሉ አባት፥ እግዚአብሔር ስለ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስብ፥ እናት የሌለው ምድራዊ ልጅ ቅር እንዲለው አይፈልግም። ቤተልሔም ውስጥ ስለ ተወለደው ሕፃን ሲል ነጭዋ ግልገል ወደዚያ እንድትመጣ ያደረገ እርሱ ይሆናል። የዳኒ አባት ይህን ሁሉ ሲያሰላስሉ ቆዩና አሳባቸውን ሰብሰብ አድርገው በትንሽ ልጁ ስም እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

አኔት ቁርስ ለማዘጋጀት ወደ ወጥ ቤት ስትመጣ ዳኒ የሌሊት ልብሱን እንደ ለበሰ አንዲት ነጭ ድመት ሲመለከት ስለ አገኘችው በመገረም ቆማ ቀረች። አንድ ጥያቄ ልትጠይቀው ስትል ጣቱን ከንፈሮቹ ላይ በማኖር ዝም እንድትል ምልክት አሳያት። ግልገሊቱ ከእንቅልፍዋ እንድትነቃ አልፈለገም። በቀስታ እየተራመደ ወደ አኔት ተጠጋ፥ ወንበር ላይ ቁጭ እንድትል አደረገና ጉልበቷ ላይ ቁጭ ብሎ የሆነውን ነገር ሁሉ በጆሮዋ ነገራት።

አኔት የሆነውን ነገር መረዳቱ አላስቸገራትም። እንዲያ ያለች ነጭና ንጹሕ የድመት ግልገል ከሰማይ ዱብ ያለች ናት ብላ አመነች። ወለሉ ላይ በመቀመጥ ዳኒና ግልገሊቱን ጉልበቷ ላይ አስቀመጠቻቸው። ሴት አያታቸው ያገኙዋቸው፥ ከግማሽ ሰዓት በኋላ የገና ጠዋት ትኩስ ቡና የተዘጋጀላቸው መሆኑን በማመን ወደ ወጥ ቤቱ በመጡ ጊዜ ነበር።

## ምዕራፍ አራት

## ጸቡ ተጀመረ



ሉሲየን አልጋው ላይ፥ ትልቅ ብርድ ልብሱን ተከናንቦ ተኝቷል። ከመኝታ የመነሻው ሰዓት መድረሱን አልወደደውም። መኝታው ይሞቃል! የውጩ አየር ግን በጣም ቀዝቃዛ ነበር። ቀና ብሎ አካባቢውን አየት ካደረገ በኋላ በረጅሙ ተነፈሰና እንደገና ሽፍንፍን አለ።

«ሉሲየን!» ብለው ተጣሩ በቁጣ ድምፅ። በፍጥነት ከመኝታው ላይ ዘልሎ ወረደ። እናቱ ሲጠሩት ይህ ለሦስተኛ ጊዜ መሆኑ ነው። ያለፉትን ሁለት ጥሪዎች ያልሰማ በመምሰል ዝም ብሎ ነበር። አሁንም ቢሆን ቶሎ ቢነሣ የከብቶቹን ወተት ለማለብ ባይችልም፥ ሳይረፍድበት ትምህርት ቤት ሊደርስ ይችላል። ጊዜ ባይበቃውም ወተቱን እናቱ ሊያልቡ ይችላሉ። እንዳውም ሰሞኑን እርሳቸው ነበሩ የሚያልቡት።

«ሌሎች ልጆች ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው በፊት ወተት እንዲያልቡ አይገደዱም» አለ ሉሲየን ጃኬቱን እየቀላለፈ፥ «አባት ስለሌለኝ ብቻ ከሌሎች ልጆች ይበልጥ የምሠራበት ምክንያት አይገባኝም።»

ከፎቅ የወረደው በኩርፊያና በእምቢተኛነት ስሜት ነበር። እንደዚያው እንደሆነ ቁርሱን ሊበላ ቁጭ አለ።



ቁርሱን እንዳጋመሰ እናቱ መጡና፦ «ስጠራህ ከመኝታህ ያልተነሣኸው ለምንድን ነው፥ ሉሲየን? ይህ ድርጊትህ ተደጋገመ! ጠዋት ጠዋት በፍጹም ሥራ አታግዘኝም። እኅትህ በጠዋት ተነሥታ ያለምንም ማጉረምረም ሥራ ትሠራለች። ሌሎች ልጆች የሚያሳድጉ አባቶች አሏቸው። እኛ ያሉን ሦስት ላሞች ብቻ ናቸው። ያለ እነርሱ ለመኖር አንችልም። አንተ ትልቅና ጠንካራ ልጅ ሆነህ ሳለ፥ የማለዳ ሥራዎችን ሁሉ ለእኔ በመተውህ ልታፍር ይገባል።»

«በየምሽቱ እሠራለሁ! ተጫውቼ አላውቅም። እንጨት ለመልቀም ከማንኛውም ልጅ ይልቅ ወደ ተራራ ወጥቼ ነው የምመጣው። ድርቆሽ አመጣልሻለሁ። ቅዳሜ ቅዳሜ ደግሞ የከብቶች በረት አፀዳለሁ።» አለ እየተነጫነጨ።

«ካልካቸው ሥራዎች ብዙዎቹን እኔው ነኝ አንተ ከትምህርት ቤት ከመመለስህ በፊት የምሠራቸው። እንደ ሌሎቹ ልጆች በክረምት ወራት በቂ የእረፍት ጊዜ እንደሌለህ አውቃለሁ። በመሆኑም የሚቻለኝን ሁሉ በማድረግ ላይ ነኝ። በማለዳ ተነሥቶ ወተት የማለቡ ሥራ ግን ሊገድለኝ ነው። አንተ አሁን በደንብ ስለ አደግክ ይህን መሥራቱ አያቅትህም። ለወደፊቱ ከእንቅልፍህ በጠዋት መንቃትና መነሣት አለብህ። አሁን እንዳይረፍድብህ ወደ ትምህርት ቤትህ ፍጠን» አሉት እናቱ።

ሉሲየን ኮቱን በፍጥነት ለበሰና እንዳኮረፈ እናቱን ተሰናብቶ ወጣ። ከዚያም በረዶ ላይ በሚንሸራተት ጋሪው ላይ በመውጣት በጫካው ውስጥ እየተሹለከለከ ወደ ትምህርት ቤቱ ሽው አለ። ሸርተቴው ጋሪ ከሚያሰማው ዝቅተኛ ድምፅ በቀር፥ ከቀኑ መምጣት በፊት ትንፋሹን እንደ ዋጠ ሁሉ፥ አካባቢው በጸጥታ ተውጧል። ሉሲየን ለወትሮው ጫካውንና ጸጥታውን ያደንቅ ነበር። ዛሬ ስለ ተበሳጨ ማድነቁን ረስቷል።

«ሰው ሁሉ እኔን መቃወሙ ትክክል አይደለም። ትምህርቴን በሚገባ ለማጥናት አለመቻሌ የእኔ ጥፋት አይደለም። ቤት ውስጥ ሁልጊዜ ለመሥራት እገደዳለሁ። ዛሬ ትምህርት ቤት የንባብ ፕሮግራም አለ! አሁንም ውጤቴ ከልጆች ሁሉ ያነሰ እንደሚሆንና ያቺ ጉረኛ አኔት ከሁላችንም የተሻለ ውጤት እንደምታመጣ እገምታለሁ። እንደ እኔ ትምህርት ቤት ከመሄዷ በፊት ወተት የማለብ ሥራ እንደሌለባት እርግጠኛ ነኝ! ኡፍ. . . !» አለ ለራሱ።

ብስጭቱ ስለ አልበረደለት የሚሄድበትን አቅጣጫ በጥንቃቄ አይመለከትም ነበር። በመሆኑም ሳያስበው አንድ ማቋረጫ መንገድ ላይ በመድረሱ ተንሸራታች ጋሪውን ለማቆም ሞክሮ ነበር።

አልቻለም፤ ከሌላ አቅጣጫ በመምጣት ላይ ከነበረችው አኔት ጋር ተጋጩና ከነተንሸራታች ጋሪዋ ቦይ ውስጥ ከተታት።

ግድየለሽ አካሄድ ነበር። ፊቱ በቁጣ የቀላው ሉሲየን አኔትን ከወደቀችበት ሊያነሣት ከጋሪው ውስጥ ዘሎ ወጣ። አኔት ግን ቀደመችው። አኔት ሉሲየንን አትወደውም፤ በገጠማት ሁኔታም ደንግጣለች። በረዶው እስከ ወገቧ እንደ ዋጣት ዓይኖቿ በቁጣ ቀልተው፤

«አንተ ከርፋፋ ወደል አህያ! የምትሄድበትን አቅጣጫ በትክክል ለመመልከት አትችልም? እስቲ ተመልከት መጽሐፌ እንዴት በውኃ እንደ ራሰና እንደ ተቀዳደደ? ጥፋትህን ለትምህርት ቤታችን ዲሬክተር እነግርልሃለሁ» አለች እንደ ማልቀስ እያለች።

ትዕግሥት የለሹ ሉሲየን ይበልጥ ተቆጣና፡— «እንዲህ ያለ ጭቅጭቅ አስፈላጊ አይደለም። አውቄ አይደለም እንድንጋጭ ያደረግኩት። የተፈጠረው ሁኔታ እንኳን የአሮጌ የደብተር መቀደድ የሞት አደጋ ሊያደርስብሽ ይችል ነበር። አደጋውን የሚመለከት ማንም ሰው ይህን ሊገምት ይችላል። የደብተሩ መቀደድ በትምህርት ፈተናሽ በምታመጪው ነጥብ ላይ የሚያስከትለው ችግር አይኖርም። መሄዴ ነው» አለ በቁጣ ድምፅ።

ይህን ተናግሮ ተንሸራታች ጋሪው ላይ ዘሎ ወጣና ጉዞውን በከፍተኛ ፍጥነት ቀጠለ። ትምህርት ቤት የደረሰው ልክ በሰዓቱ ነበር። ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ከጥቂት ጊዜ በፊት በተፈጠረው ሁኔታ ተጸጸተ። ነገር ግን ጥሩ ፀባይ ያለው ልጅ ስለአልሆነ ስለ አደረገው ጥፋት ለማሰብ አልፈለገም።

«ከወደቀችበት የተነሣቸው እራሷ ናት። ልርዳሽ ብላትም እሺ አትለኝም ነበር። እግዚአብሔር ይመስገን ትምህርት ቤቱ በጊዜ ደርሻለሁ። በዚህ ሳምንት ብቻ ሁለት ጊዜ ነው ዘግይቼ የደረስኩት» አለ።

ከበረዶ ክምር መውጣቱ ከመስጠሙ የሚለይ በመሆኑ አኔት ከባድ ችግር ገጥሟት ነበር። በብዙ ትግል ከበረዶው ማጥ ተላቅቃ የተበተኑ መጻሕፍቷን በምትሰበስብበት ጊዜ አምርራ ታለቅስ ነበር። ብርዱ፥ ድንጋጤው፥ ጉልበቷ ላይ የሚሰማት ህመም፥ ከሁሉም ይልቅ ንዴት አስለቀሷት። ሩብ ሰዓት ያህል ዘግይታ ትምህርት ቤቷ ስትደርስ ዓይኖቿ ቀልተው፥ አፍንጫዋ ደንዝዞ፥ እጆቿና ጉልበቶቿ ተጋግጠው ይደሙ ነበር። እንዲያ ሆናና የተቀዳደዱና የረጠቡ መጻሕፍቷን ይዛ ስትታይ ታሳዝን ነበር።



«ምን ሆነሻል አኔት ልጄ» አሉ የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር በድንጋጤ እያዩዋት።

አኔት ስለ ደረሰባት ነገር ሌላ ምክንያት ለመስጠትና የሉሲየንን ድርጊት ለመደበቅ አስባ ነበር። ሉሲየን ተመቻችቶና ግድየለሽ ሆኖ ክፍል ውስጥ መቀመጡን ስታይ ግን አልቻለችም።

«ሉሲየን ነው እንዲህ ያደረገኝ» አለች በቁጣ። «በተንሸራታች ጋሪው ገጭቶ ቦይ ውስጥ ጣለኝ። የወደቅኩበት የበረዶ ክምር አስምጦኝ፥ ከዚያ ለመውጣት እንኳን አልቻልኩም ነበር» ብላ ዓይኖቿን በእጆቿ እያሻሸች ታለቅስ ጀመር። መደንገጥ ብቻ ሳይሆን በጣም ተናድዳ ነበር!

ክፍሉ ውስጥ የነበሩት ልጆች ሁሉ አዘኑላት፤ በሉሲየን ግን ተናደዱበት። ይሄ ሁሉ ሲሆን ቀና ብሎ በመቀመጥ በቁጣ ይመለከት ነበር።

እንዲያ ያለ ጥፋት በመፈጸሙ ዲሬክተሩ ሉሲየንን ገረፉት። አኔት ደስ አላት። ይህ ሁሉ ካለፈ በኋላ የክፍሉ ልጆች በፈተና ያገኙት ውጤት ይነበብ ጀመር። አኔት ከሁሉ የሚበልጥ ነጥብ ስለ አገኘች ይበልጥ ደስ አላት። ሉሲየን ግን ከልጆቹ ሁሉ ያነሰ ነጥብ በማግኘቱ፥ ክፍለ ትምህርቱ አብቅቶ ሌሎች ወደ የቤታቸው ሲሄዱ እርሱ ክፍል ውስጥ ቆይቶ ተጨማሪ ሥራ እንዲሠራ ተደረገ። በዚሁ መሠረት ቀኑን ከሌሎች ጋር ሲማር ዋለና እነርሱ ወደ የቤታቸው ሲሄዱ ብቻውን ክፍል ውስጥ ቆየ። በውስጡ የነበረው ጥላቻ፥ ቁጣና ትዕግሥት የለሽነት በዚህ ምክንያት ሊፈነዳ የደረሰ እስኪመስለው ድረስ አደገ።

በመጨረሻ ወደ ቤቱ እንዲሄድ ተፈቀደለትና ተንሸራታች ጋሪውን እየጎተተ ወደ ተራራማው ሠፈሩ አመራ። ምን ዓይነት መጥፎ ቀን ነበር! ከእናቱ ጋር ተጣላ፥ አኔት ጥፋቱን ለዲሬክተሩ ነገረችበት፥ እርሱ ደግሞ ገረፈው፤ በፈተና ውጤቱም ከክፍሉ ልጆች ሁሉ የመጨረሻው ሆነ። እንዲህ ያለ መከራ የሚደርስበት ልጅ አለ? ይህን ነበር በጉዞ ላይ እያለ የሚያሰላስለው።

ያን ዕለት በየሜዳው ያሉት ጥላዎች ባልተለመደ ሁኔታ ሰማያዊ መስለዋል። ተራራዎች አናት ላይ የፀሐይ ብርሃን ይታያል፥ ስስ ደመናዎችም ያንዣብቡባቸዋል። የተራራዎች ጸጥታ ሉሲየንን ለመርዳት እጆቹን የሚዘረጋለት መሰለ። ሕፃናትና ተፈጥሮ በጣም ይቀራረቡ የለም? የተፈጥሮ ጸጥታ ከማንኛውም ሰብዓዊ የማጽናናት ድምፅ ይልቅ የተቆጣና ያዘነን ልጅ ለመፈወስ ይችላል። ዳገቱን

ለመውጣት በመታገል ላይ እያለ የሉሲየን ቁጣ ወደ ድካምና ብቸኝነት ተቀየረ። ብቸኝነቱ በጣም ስለ ተሰማው ዓይኖቹን እያሻሸ ትንሽ አለቀሰ።

ወዲያው ትዝ ሲለው፥ ለካ ብቻውን አይደለም። አሁንም መንታ መንገዱ ላይ ደርሷል። አንድ በመገረም የሚመለከተው ልጅ በረዶው ክምር ውስጥ ቆሟል። ጉንጮቹ የቀሉና ደስተኛ ልጅ ነበር። ሉጫ ፀጉሩ በኮፊያው ሥር ብቅ ብሎ ይታያል። ፊቱ በመልካም ጤንነትና በጫወታ ስሜት ፈገግ ብሏል።

ዳኒ ነበር ልጁ። በበረዶ ጥፍጥፍ የሰው ምስል ወይም አሻንጉሊት በመሥራት ላይ ነበር። ሥራውን ጨርሶ የምስሉን ዓይን በማስተካከል ላይ ነበር። እስከ ዛሬ ከሠራቸው የበረዶ የሰው ምስሎች ሁሉ ይበልጥ የሚያምር ስለሆነ አኔትን ፈልጎ ምስሉን ሊያሳያት ቸኩሏል።

«ለምንድን ነው የምታለቅሰው?» አለ ዳኒ ሉሲየንን እያየ።

«አላለቀስኩም!» አለ ሉሲየን በቁጣ።

«እአ፥ በማልቀስ ላይ ነህ! ለምን እንደምታለቅስም አውቄያለሁ። ዲሬክተሩ ስለ ገረፉህ ነው፤ አኔት ነግራናለች።» በማለት ዳኒ መለሰለት።

ዳኒ በጣም ጥሩ ትንሽ ልጅ ስለሆነ በሉሲየን መገረፍ ተደስቶ አይደለም እንደዚያ የተናገረው። ሉሲየን አኔትን እንደማይወዳት ግን ዳኒ ያውቃል። ይህ ደግሞ ለዳኒ ይቅርታ የማይደረግለት በደል ነበር። በዳኒ ንግግር ምክንያት ሉሲየን በጣም ተቆጣና የበረዶ ምስሉን በእርግጫ ሰበረበት። ዳኒ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸ። የሉሲየን ድርጊት በጣም አስቆጣው።

አኔት የዳኒን ጩኸት ስትሰማ ከነበረችበት በመውጣት የተፈጠረውን ነገር በሩቁ ተመለከተች። ወዲያው እንደ ነብር ግልገል እየፈጠነች ዳኒ ወደ አለበት ሮጠችና ሉሲየንን በጥፊ አጮለችው። ሉሲየን ሊመታት እጁን አንሥቶ ነበር! ነገር ግን የአኔት አባት ባልዲ ይዘው ከቤታቸው ብቅ ሲሉ ስለ አያቸው እጁን ሰበሰበ።

«ቦላካ– ወሬኛ– ፈሪ– እንደ ሕፃናት እያለቀሽ ወደ ትምህርት ቤት የምትመጪ!» አለ ሉሲየን ወደ አኔት በቁጣ አፍጥጦ።

«ትልቁ ባለጌ– ጉልበተኛው!» መልሳ ጮኸችበት አኔት፥ «እኔን ቦይ ውስጥ ጣልከኝ! አሁን ደግሞ የትንሹን የዳኒን የበረዶ ምስል ሰባበርክበት። ምንም ያደረገህ ነገር የለም! ለምን አትተወውም? በመገረፍህ በጣም ደስ ብሎኛል። ና ዳኒ፥ ወደ ቤታችን እንሂድ።»



ዳኒን አስከትላ በቁጣ ወደ ቤታቸው ሄደች። በርዋ ላይ ስትደርስ ዘወር ብላ በሩቅ ከሚታየው ተራራ ኋላ ያለውን ቀላ ያለ ሰማይ ተመለከተች። ሴት አያቷ አንድ ጊዜ፥ «በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አትግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት» የሚለውን ቃል አስተምረዋት ነበር። ያ ትዝ አላትና አሰላሰለችው። ገና ፀሐይ አልጠለቀችም፥ ሉሲየንም እዚያው እንደ ቆመ ነበር። እርሱ ያደረገውን መጥፎ ነገር መናገሯ ጥሩ አልነበረም።

ነገር ግን ከእርሷ ይበልጥ እርሱ ነበር ያጠፋው። ይቅርታ መጠየቅ የነበረበትም እርሱ ነበር። ይቅርታ ከጠየቀችው እንደ ጥፋተኛ ልትቆጠር ነው፤ ግን አይደለችም። የለም አይሆንም። እንዲህ ከራሷ ጋር ከተከራከረች በኋላ ወደ ቤት ገብታ በሩን ዘጋችው።

ሉሲየን አኔት በመታችው ጥፊ ምክንያት ፊቱን እየጠዘጠዘው በቀስታ ወደ ቤቱ ጉዞ ጀመረ። ከቀድሞው ይበልጥ ተናዷል። በጉዞ ላይ እንዳለ ቀና ብሎ የሚያስደንቅ ነገር ተመለከተ። ደመናው ከቤቱ ኋላ ያለውን ተራራ እየጋረደው ይጓዛል። አንዱ ቦታ ላይ ግን ቁልሉ ደመና ሁለት ላይ ተከፍሏል። በዚያ የደመና ክፋይ መሀል ወርቃማ የፀሐይ ብርሃን የሚንጸባረቅበት የበረዶ ቋጥኝ ታየው።

የክረምት ፀሐይ ስትጠልቅ በተራራማው አካባቢ የምትፈጥረውን ውበት ያውቀዋል። የዚያን ዕለቱ የፀሐይ ጥልቀት ማማር ግን እጅግ ስለ መሰጠው እንደገና ቀና ብሎ ተመለከተ። ጥርት ያለው ብሩህ ትዕይንት ቁጣውን የደካማነት ምልክት፥ በጣም ትንሽ ነገርና ሊያሰላስለው የማይገባ አደረገው። እንደገና ሰላማዊና ጥሩ ልጅ መሆን እንዴት ጥሩ ነው! ጊዜው ገና ስለሆነ፥ ቢሮጥ አኔት ላይ ይደርስባታል።

አይሆንም! አኔት ልታይ ባይ ስለሆነች፥ ከቁብ አትቆጥረውም ይሆናል። ደግሞስ ለምንድን ነው ሴት ልጅን ይቅርታ የሚጠይቃት?

ስለዚሁ ከሁለቱ አንዳቸው ቀድመው ይቅርታ ሊጠይቁ ባለመፈለጋቸው ጸቡ ቀጠለ፥ ለብዙ ጊዜ የሚቆይ፥ የሁለቱንም ሕይወት የሚጎዳ ጸብ።

ሉሲየን ቆሞ በማሰላሰል ላይ እንዳለ፥ በደመናው ክፋይ መሀል ንፋስ ነፈሰና ወርቃማ ነጸብራቅ የሚታይበት ተራራ በደመና ተጋረደ።

# ምዕራፍ አምስት
# አደጋው



የአኔት ልደት በመጋቢት ወር ነበር። ዳኒ ከሳምንታት ቀደም ብሎ ነበር ስለ አኔት የልደት በዓል ሲያቅድ የቆየው። ስጦታ እንደ መስጠት የሚያስደስተው ነገር የለም። ሰዎች ስጦታው ብዙ ዋጋ ያለው አይደለም ይሉ ይሆናል። እርሱ ግን ስጦታዎቹ ቆንጆዎች እንዲሆኑ ያስባል። ስጦታዎቹን በእንጨት ቁርጥራጭ ማከማቻ ስፍራ ደብቆ ነበር ያቆያቸው። አኔት ስጦታዎቹ ወደ ተደበቁበት ስፍራ መሄድ እንደሌለባት ስለ ተረዳች፥ ስፍራው በእንጨት ቁርጥራጮች የተጨናነቀ በማስመሰል ወደዚያ ሳትቀርብ ቆየች።

ከእንጨቱ ቁርጥራጭ ጋር የሚነድ የዛፍ ፍሬም ነበር። እዚያ መሀል ነበር ዳኒ ለአኔት ልደት ያዘጋጀው ስጦታ የተደበቀው። ስጦታው ነጣ ያለ ቡናማ መልክ ያላት ላም ሥዕል ነበር ። ላሚቱ በቁመቷ ልክ የሆነ ሰማያዊ አበባ በበዛበት ሜዳ ላይ ሣር ስትግጥ ትታያለች። ከላሚቱ ሥዕል ጋር የሚያማምሩ ነጫጭ ጠጠሮች፥ ከኮርማ በሬ ጭራ በተወሰደ ፀጉር የተሠራ የእጅ አምባር ነበሩ። ዳንኤል በስጦታዎቹ መካከል አንዳንዴ ቸኮላት የሚቀላቅል ቢሆንም፥ ብዙ አያቆየውም እራሱ በልቶ ይጨርሰዋል።

እንግዲህ ሲጠበቅ የነበረው ታላቅ በዓል ደረሰ። ነገ የአኔት የልደት በዓል ይሆናል። ዳኒ ያስብ የነበረው ስለ እርሱ ብቻ ነበር። አኔት ወደ ትምህርት ቤት ሄዳ በነበረ ጊዜ ስለ ስጦታው ለሴት አያቱ ነገራቸው። ዳኒ መጥቶ ክንዱን ጉልበታቸው ላይ ሲያደርግ፥ በረንዳው ላይ



ተቀምጠው ፀሐይ እየሞቁ ለእራት የሚሆን አትክልት ይቀነጣጥሱ ነበር።

«አያቴ፥ ለአኔት የልደት በዓል የሚሆን አበባ ለማምጣት በረዶው ወደ ቀለጠበት ተራራ አካባቢ መሄዴ ነው። ነገ ጠዋት ከስጦታዎቹ ጋር ቁርስ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠዋለሁ» አለ ዳኒ።

ከአጠገባቸው እየራቀ ያስቸገራቸው ሴት አያቱ በጥርጣሬ እያዩት፥

«ብቻህን ወደ ተራራማው አካባቢ መሄድ የማይገባህ ትንሽ ልጅ ነህ። ገደላማው ስፍራ ስለሚያንሸራትት የበረዶ ናዳ ይውጥሃል» አሉት።

«ድመቴ ክላውስ ከእኔ ጋር ትሄዳለች።» አለ ዳኒ በቅንነት።

ሴት አያቱ ሳቅ ብለው፥ «ድመትህ ብዙ መልካም ነገር ታደርግልህ ይሆናል» አሉት። ወዲያው የዳኒ ድመት ከመሬት ዘልላ ሴት አያቱ ጭን ላይ ቁጭ አለች። በዚህ ጊዜ የዳኒ ሴት አያት ትንሽ ደንገጥ አሉ። ድመቲቱ ግን እራሷን ከሴትዮይቱ እራስ ጋር በፍቅር እያሻሸች «ኩርርር» የሚል ድምፅ አሰማች።

«ስለ እርሷ እንደምንነጋገር ድመቴ አውቃለች። ሁሉን ነገር ታውቃለች። ወደ ተራራማው ስፍራ አብረን ብንሄድ እንደምትጠብቀኝ ነው አሁን በጆሮሽ የምትነግርሽ» አለ ዳኒ።

ከዚያም የድመት ግልገሉን ከሴት አያቱ ላይ አነሣ። አያቱን ሳመና አጭር የደስታ መዝሙር እየዘመረ በበረንዳው ደረጃዎች ወደ ታች ተንደረደረ። ኩርንችት ምስማሮች የተመቱበት ጫማው « ቋ፥ ቋ፥ ቋ» ይል፥ የሚዘምረው መዝሙርም ይበልጥ ጎልቶ ይሰማ ነበር። ሴት አያቱ ከእይታቸው እስኪሰወር ድረስ በደካማ ዓይናቸው ትኩር ብለው ተመለከቱትና በረጅሙ ተንፍሰው አትክልታቸውን መቀነጣጠሱን ቀጠሉ። ዳኒ ማደጉ፥ ብዙውን ነገርም እራሱ ማከናወን ስለ ጀመረ በአጭር ጊዜ ውስጥ አፀደ ሕፃናት ሊገባ ተቃርቦ ነበር። ከእንግዲህ ቤት መዋል ያለበት ሕፃን አልነበረም።

ዳኒ ወደ ተራራው በሚያወጣው ዳገት ወደ ላይ ይጓዛል። ድመቱ ክላውስም ትከተለዋለች። የገና አባት ያመጣት ቢሆንም፥ በበረዶ ላይ መጓዝ አትወድም። ቀኑ ደስ ይላል። ተራራው ላይ ያለው የበረዶ ክምር በመሟሟት ላይ ነበር። ሸለቆው ውስጥ ባለው ወንዝ አጠገብ ያሉት ሜዳዎች አረንጓዴ ሆነዋል። ከብቶችም ከበረታቸው እየወጡ ሣር

መጋጥ ጀምረዋል። የዳኒ ድመት ሜዳው ጫፍ ካለው አጭር የድንጋይ ግድግዳ ድረስ ጉዞዋን ቀጥላለች። ከግድግዳው በሌላ አቅጣጫ ከሥሩ የውኃ ፏፏቴ የሚወጣው ቋጥኝማ ገደል አለ። በበጋ ጊዜ ቋጥኞቹ በአበባ ይሸፈኑና ያምራሉ! አሁን ግን ራቁታቸውን ሆነው አፈር መስለዋል። ድመቲቱ ከላውስ ግድግዳው ላይ ደገፍ ብላ ለስላሳ ፀጉሯን ፀሐይ ታሞቅ ጀመር። እዚያው ሆና በምላሷ ሰውነቷን አጠበች። ነገር ግን ንፁሕና እንደ በረዶ የነጣች ስለሆነች እንደዚያ ማድረጉ አያስፈልጋትም ነበር።

ዳኒ እየተዘዋወረ አበቦችን ይቀነጣጥላል። ሜዳው የተለያየ ቅርጽና ቀለም ያላቸው አበቦች ሞልተውበት ነበር። ዳኒ ሁሉንም አበቦች በጣም ወደዳቸው። እነዚህ አበቦች በክረምት ወቅት የሚረጋባቸው አበባ እስኪረጋ እንኳን ሳይጠብቁ በረዶውን እየበሱ ቅጠሎቻቸውን ብቅ ያደርጋሉ። ትንሽ ይቆዩና ደግሞ አበባ ያወጣሉ።

ዳኒ የሚያምሩ ነገሮችን ስለሚወድ፥ በዚህ አበባ በበዛበት ሜዳ ላይ ባየው ነገር በጣም ደስተኛ ሆነ። ፀሐይዋ ትሞቃለች፥ አበቦቹ እርሱን እያዩ የሚስቁ ይመስላሉ። ዳኒ ከበረዶ ሥር በሚገኝ ዋሻ ውስጥ ስለሚኖሩ ትንንሽ አፈ ታሪካዊ ፍጥረታት የሰማውን ተረት አሰላሰለ። ፂማቸው ነጭ ሲሆን፥ ባርኔጣቸው ደግሞ ቀይ ነበር። ፍጥረቶቹ ተንኮለኞች ነበሩ። አንዳንዴ ሰው በሌለ ጊዜ ከዋሻቸው ይወጡና በየአበቦቹ ላይ እየተንጠላጠሉ ይጫወታሉ። ይህን ታሪክ ለዳኒ የነገረችው አኔት ነበረች። በዚህ ምክንያት በአበቦቹ መሀል ድምፅ ሳያሰማ በቀስታ እየተዘዋወረ እያንዳንዱን አበባ በጥንቃቄ ይመለከታል። ለዚህ ነበር አንድ ሰው ከኋላው መጥቶ አጠገቡ እስኪደርስ እርምጃውን ያልሰማው። በድንጋጤ ቀና ብሎ የሰውዬውን ማንነት ተመለከተ።

ሉሲየን በጣም ተጠግቶት ከኋላው ቆሟል። ደስ በማይል አመለካከት ዳኒ ላይ አፈጠጠበት። «አገኘሁህ!» የሚል ይመስላል አስተያየቱ። ዳኒ ባለቀሰ ጊዜ አኔት መጥታ በጥፊ እንደ መታቸው አልረሳም። እስከዚያን ዕለት ድረስ በቀሉን የመወጣት ዕቅድ ነበረው። ዳኒ እዚያ ለምለም ስፍራ ብቻውን ቆሞ ሲያየው በፍጥነት ወደ እርሱ ሄደ። ዳኒ! ትንሽ ልጅ ስለሆነ መቼም አይጎዳውም። ነገር ግን በዳኒ ላይ ማላገጥና ማናደድ፥ ለአኔት ስለተናገረበትም ብድሩን መመለስ ለሉሲየን አስደሳች ጨዋታ ይሆን ነበር። አበባውን ሊወስድበትም ይችላል።



«ለማን ነው አበባ የምትቀጥፈው?» አለ ሉሲየን።

«ለአኔት» አለ ዳኒ ኮስተር ብሎ። ይህን መልስ ሉሲየን የማይወደው መሆኑን ያውቃል። ቢሆንም ሁልጊዜ፥ በሚያስፈራ ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም እንኳን እውነትን መናገር ያለበት መሆኑን አኔት ስለ አስተማረችው በድፍረት ተናገረ።

ሉሲየን ደስ የማይል ሳቅ ሳቀና።

«አኔትን አልወዳትም። ልታይ ልታይ የምትልና ኩራተኛ ናት። በትምህርቷ ምንም ተስፋ የላትም! መዋለ ሕፃናት ያሉ ልጆች እንኳን በሂሳብ ትምህርት ውጤታቸው ከእርሷ ይሻላሉ። ላሞቿን ብቻ ነው እርሷ የምታውቀው። እነርሱን አበባዎች ለእኔ ስጠኝ! እርሷ አበባ ሊሰጣት አይገባም!» አለ።

ዳኒ ፊቱ እስኪቀላ ድረስ በሉሲየን ንግግር ደነገጠና የያዛቸውን አበቦች ወደ ኋላው አደረገ። ሰው እንዴት አኔትን ይጠላታል? ደግ፥ ብልህና ቆንጆ ናት። ዳኒ እንዲህ ያሰበው፥ የምቀኝነትን ምንነት ስለማያውቅ ነበር።

«አበቦቹ የእኔ ናቸው፥ አልሰጥህም» አለ ዳኒ አበቦቹን ጠበቅ አድርጎ በመያዝ።

«ትሰጠኛለህ፥ እወስዳቸዋለሁ፥ ትንሽ ልጅ ስለሆንክ በጣድ እቀማሃለሁ። ደግሞ የፈለግሁትን ነገር ላደርግብህ እችላለሁ። ለወሬኛነትህ የሚገባህን ዋጋ ነው የምሰጥህ» አለ ሉሲየን።

ከዚያም አበቦቹን ከዳኒ እጅ ቀምቶ መሬት ላይ በመጣል ረጋገጣቸው። ዳኒ ለአንድ አፍታ የተሰባበሩና የተጨፈለቁ አበቦቹን ተመለከተና ጨኸቱን ለቀቀው። ያን ዕለት አበቦቹን እየቀጠፈ ደስተኛ ሆኖ ነበር የዋለው! አሁን ግን አበቦቹ ተሰባብረዋል። ዘልሎ ሉሲየን ላይ በመንጠልጠል በትንንሽ እጆቹ እየመታው፥

«ለአባቴ ነው የምነግርልህ፥ አሁኑኑ ወደ ቤት ሄጄ እነግረዋለሁ። እስከ ቤትህ መጥቶ ነው የሚደበድብህ። ጨካኝና መጥፎ ልጅ ነህ» አለ።

ይህ እንዲሆን ሉሲየን አልፈለገም ነበር። ሉሲየን የዳኒን አባት ይፈራቸዋል። ምክንያቱም የዳኒ አባት ረጅምና ግዙፍ ነበሩ። ልጃቸው ዳኒ በሰው ጉዳት ሲደርስበት በጣም ነበር የሚናደዱት። ሉሲየን የዳኒን

ቦክስ ለማስቆም ሁለት እጆቹን ጥብቅ አድርጎ ያዛቸውና አካባቢውን እየተመለከተ ዳኒ ለአባቱ እንዳይነግር ለማድረግ የሚችልበትን መንገድ አሰበ።

ወዲያው ድመቲቱ ከላውስ ፀሐይ ስትሞቅ አያትና አንድ አሳብ መጣለት። ዳኒን ግፍትር አድርጎት ወደ ገደሉ ሮጠ። ዳኒ ደግሞ ጸበኛው የሄደለት መሰለውና እንባውን ጠራርጎ ቶሎ ቶሎ እያለ እንደገና አዳዲስ አበቦችን ይቀጥፍ ጀመር። ሉሲየን ኖረም አልኖረ የእኔት የልደት በዓል ብሩህና በአበቦች ያማረ መሆን አለበት።

እንዲህ እያሰበ በጥድፊያ አበቦችን በመቅጠፍ ላይ እንዳለ ነበር የሉሲየንን ድምፅ በሩቁ የሰማው። በፍጥነት ቀና አለና ድምፁ ወደ መጣበት አቅጣጫ ተመለከተ። ያየው ነገር ለጊዜው በጣም አበሳጨው። ሉሲየን ድመቲቱን ወደ ላይ አንጠልጥሎ በመያዝ ከገደሉ አጠገብ ቆሟል። አያያዙ በገደሉ ሥር ወደሚወርደው የወንዝ ውኃ ሊጥላት የተዘጋጀ ይመስላል።

«በአስቸኳይ ወደዚህ መጥተህ የሆነውን ነገር ለአባትህ እንደማትነግር ቃል ካልገባህልኝ፥ ድመትህን ገደሉ ውስጥ ነው የምጥላት» አለ ሉሲየን።

ዳኒ በበረዶው ላይ እየወደቀና እየተነሣ ይሮጥ ጀመር። እግሮቹ በድንጋጤ ስለ ተንቀጠቀጡበት በፍጥነት ለመሮጥ አልቻለም። ድመቱ ወደ ገደሉ ተጥላ በፍጥነት በሚወርደው ውኃ መወሰዷን ሲያስበው በድንጋጤ ሲቃ ጉሮሮው ስለ ደረቀ ለመጮህ እንኳን አልቻለም። ያም ቢሆን፥ እንደ ምንም ብሎ ሉሲየን ዘንድ በመድረስ ድመቱን ከዚያ መጥፎ ልጅ ማስጣልና እንደዚያ ያለ ሥራ ሁለተኛ እንዳይደገም ማድረግ አለበት።

ሊታወቅ የሚገባው ነገር ግን በዚህ ታሪክ መጀመሪያ ላይ እንደ ተባለው፥ ሉሲየን ድመቲቱን ገደሉ ውስጥ የመጣል አሳብ አልነበረውም። እርግጥ ሉሲየን ደግ ልጅ አልነበረም። እንደ ነፍሰ ገዳይ ጨካኝ ግን አልነበረም። ድመቲቱ ከላውስ አንገቷ ተይዞ ወደ ላይ ተንጠልጥላ ስለማታውቅ መንፈራገጥ ጀምራለች። ሉሲየን እንደማይለቃት ስትረዳ ይበልጥ ተንፈራገጠች። በመጨረሻም ስለ ተጨነቀች፥ ከዚያ ቀደም አድርጋው የማታውቀውን ነገር አደረገች። በፊት እግሮቿ ጥፍሮች ሉሲየንን ቧጠጠችው።



የዳኒን እየወደቀና እየተነሣ ወደ እርሱ መሮጥ ያየው ሉሲየን ተደነቀና ድመቲቱን ለቀቃት። ልክ እንደ ድንጋይ ወደ ገደሉ ወረደች። በድንጋጤ ፊቱ የገረጣውና እንባ የሚተናነቀው ዳኒ ያኔ ድመቲቱ ከነበረችበት የገደሉ ግድግዳ አጠገብ ደርሶ ነበር።

የድመቱን ወደ ገደል መጣል ሲመለከት፥ በወጥመድ የተያዘ ትንሽ አውሬ በሚያሰማው ዓይነት ድምፅ ጮኸና ወደ ገደሉ ሮጠ። በድርጊቱ በመደናገጥ እንደ ሽባ የሆነው ሉሲየን ዳኒን ይዞ ወደ ገደል ከመውረድ ሊያድነው አልቻለም።

ከዚያ በኋላ የሆነው ነገር ሁሉ የተከናወነው በጥቂት ሰኮንዶች ውስጥ ነበር። ድመቲቱ ክላውስ ውኃው ውስጥ አልወደቀችም። ከአስፈሪው ገደል ወጣ ባለ አንድ ገደል ላይ ጥብቅ ብላ በመንጠልጠል በሚያሳዝን ድምፅ ሚያው እያለች ትጮህ ጀመር። ትልቅ ልጅ ቢኖር ኖሮ ወደ ድመቲቱ ወርዶ ከገደሉ ያወጣት ነበር። ዳኒ ግን ገና የአምስት ዓመት ልጅ ነበር። እርሱም ቢሆን ድመቱን ካለችበት ለማውጣት ሞክሮ ነበር። ምን ያደርጋል ታዲያ! የረገጠው ድንጋይ አንሸራተተውና የጩኸት ድምፅ አሰምቶ ወደ ገደሉ ወደቀ። ያን ዕለት ያሰማው የጩኸት ድምፅ ለብዙ ዓመት ሉሲየንን ሲያስጨንቀው ኖሯል።

ሉሲየን የማይረባ ልጅ ባይሆንና ባይደነግጥ ኖሮ ዳኒ ሲወድቅ ትንሽ ተከትሎት ቁልቁል ወደ ገደሉ ሊመለከት ይችል ነበር። ዳኒ ሞቷል ብሎ ደመደመ። ውኃው የዳኒን በድን ተሸክሞ ወደ ፏፏቴው ሲወርድ መመልከቱ ግን ከአቅሙ በላይ ነበር። ከጠወለገ ትንሽ የሣር ክምር ላይ ቁጭ ብሎ ፊቱን በመዳፎቹ ከደነ። ያን ጊዜ እኔት ብታየው ኖሮ ሉሲየን በድርጊቱ መቀጣት ያለበት መሆኑን ትገነዘብ ነበር።

«ዳኒ ውኃ ውስጥ ሰመጠ። እኔ ነኝ የገደልኩት። ምን ላድርግ? ምን ይሻለኛል?» እያለ በመደጋገም ኀዘኑን ይገልጥ ጀመር።

ቀስ በቀስ ፍርሃት አእምሮውን ስለ አስጨነቀው ብድግ አለና ዙሪያውን ተመለከተ። ጊዜው ይፈጥናል። የዳኒ ቤተሰቦች ሊፈልጉት ቢመጡና ሉሲየንን ቢያገኙት ነፍሰ ገዳይ መሆኑን ይረዳሉ። ሉሲየን ከአደጋው ጋር ያለውን ግንኙነት እስከ አሁን የሚያውቅ ሰው የለም። ስለዚህ ቶሎ ወደ ቤቱ ቢሄድና ምንም ያላደረገ መስሎ ቢቀመጥ ማንም አያውቅበትም። አሁኑኑ ማምለጥ አለበት።

አዳኝ እንደሚያባርረው ጥንቸል እየሮጠ ወደ አንድ ዛፍ ሥር ሸሸ። ልቡ በኃይል መታ፤ ራስ ምታትም አስጨነቀው። ወደ ቤቱ ለመሄድ ግን ገና አልደፈረም። ከዚያ ይልቅ፥ ሌላ ሰው ቢያየው ከሌላ አቅጣጫ መጥቷል ብሎ እንዲገምት ለማድረግ በማሰብ ሰው በማይበዛበት መንገድ ጉዞውን ቀጠለ። ሰው የተከተለውና የእርምጃ ድምፅ የሰማ እየመሰለው በድንጋጤ ወደ ኋላ ይመለከት ነበር። ከኋላው የሚከተለው ሰው ግን አልነበረም።

በመጨረሻም ቤቱ ደረሰና ጓሮው በር ላይ ቆመ። ወደ ቤት ለመግባት አልቻለም። ያን አሳዛኝ ምሥጢር በልቡ ደብቆ በጣም የሚያምኑበት እናቱን ሊያያቸው አልደፈረም። ፊቱን አይተው ድርጊቱን ያውቁበታል። ምክንያቱም ፊቱ እንደ ቀድሞው አልነበረም። ነፍሰ ገዳይ ሆኖ ነበር።

ምናልባት ትንሽ ቆይቶ ሊያያቸው የሚያስችለው ድፍረት ያገኝ ይሆናል። ግን ገና ነው። ከመደንገጡ የተነሣ ጥርሶቹ ስለሚንገጫገጩ፥ ያን ሲያዩ እናቱ «ምን ሆነሃል?» ብለው ይጠይቁት ነበር። አሁኑኑ መደበቅ አለበት። ዙሪያውን እያየ ቦታ ፈለገ። የከብቶች በረት በሆነ ቤት ጣራ ላይ ወደ ተከማቸ የሣር ድርቆሽ የሚያወጣ መሰላል ተመለከተ። በመሰላሉ ሽቅብ በመውጣት ሣሩ ላይ በደረቱ ተኛና ልቡ የምትፈነዳ እስክትመስል ድረስ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ።



# ምዕራፍ ስድስት
# ከአደጋ መዳን



የዳኒ ሴት አያት ለምግብ የሚሆን አትክልት መቀንጣጠሱን ጨርሰው ምርኩዛቸውን በመደገፍ ወደ ቤት ገቡና ወንበራቸው ላይ አረፍ አሉ። በጣም ስለ ደከማቸው፥ ብዙም ሳይቆዩ እራሳቸውን ወደፊት ዘንበል እንዳደረጉ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰዳቸው።

ከቀድሞው ይልቅ ደካማ ሆነዋል። ዓይኖቻቸውም የመታወር ያህል ደክመዋል። ምንም ደካማ ቢሆኑም፥ የልጅ ልጆቻቸውን በጣም ስለሚወዱቸው ለእነርሱ ሲሉ የሚቻላቸውን ያህል ይሠራሉ። ከሽባነት ብዙም በማይሻሉት እጆቻቸው ምግብ ይሠራሉ፥ በደካማ ዓይኖቻቸው እያዩ የተቀደዱ ልብሶችን ይሰፋሉ። አኔት ገና የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ስለሆነች የአያቷን ችግር ባትረዳም፥ ሴት አያቷ በዚህ ቅር አልተሰኙም። የምንሠራው አንድን ሰው በማፍቀራችን ከሆነ፥ ሥራው አስቸጋሪ አይሆንም።

የአኔት ሴት አያት ከተለመደው በላይ ለረጅም ጊዜ አንቀላፉ። አኔት ወደ መንደሪቱ መደብር ሄዳለች። አባቷ ደግሞ ከቤታቸው በላይ ባለው ጫካ ውስጥ ዛፍ እየቆረጡ ግንድ ይከምራሉ። ሴት አያታቸው የዳኒን ከሱፍ የተሠራ ነጭ አሮጌ የእግር ሹራብና እጅጌው ላይ የተቀደደ ሰማያዊ ጃኬቱን ሊሰፉ ዐቅደው ነበር። ግን ደከሟቸዋል፤ በእርጅና የተጨማደዱ እጆቻቸውን ጉልበታቸው ላይ አጣመሩና እንቅልፋቸውን ቀጠሉ። የግድግዳው ሰዓት ሦስት ጊዜ ሲደውል እንኳን አልሰሙም።

ነቅተው ሰዓቱን ሲመለከቱ ለአሥር ሰዓት ትንሽ ነበር የቀረው። መደነቅንና ስጋትን የሚገልጥ ድምፅ አሰሙ። ዳኒ ከቤት የወጣው በስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን፥ ገና አልተመለሰም። ወዴት ሄዶ ይሆን?

«ዳኒ!» አሉ በቀጭን ድምፅ። ተደብቆ ይሆናል። በየጊዜው እንደሚያደርገው ከቁም ሳጥን ውስጥ እየቀለደ ብቅ ሊል ይችላል።

ነገር ግን ለጥሪው የወይታ ድምፅ አልተሰማም። ሴት አያታቸው እያዘገሙ ወደ በረንዳው ወጡና ዓይኖቻቸውን ከፀሐይ ጨረር በመዳፋቸው ከልለው በደካማ ዓይኖቻቸው ወደ ውጭ ይመለከቱ ጀመር። ወደ ቤቱ እየሮጠ ሲመጣ ያዩት ይሆናል። ዘግይቶ በመምጣቱ እንዴት ይገሥጹት ይሆን!

አንድ ሰው ከከብቶች በረት አቅጣጫ ብቅ አለ። ዳኒ አልነበረም። አኔት ነበረች። ከላይ አንድ ትልቅ ወርቅማ ዳቦ ብቅ ያለበት ቅርጫት አዝላለች። ከትምህርት ቤት ግማሽ የእረፍት ቀን ስለ አላት ወደ ገበያ ሄዳ ነበር። ከሩቁ እጆቿን እያወዛወዘችና እየሮጠች ወደ ሴት አያቷ መጣች።

«አኔት፥ ሸክምሽን አውርጂና ሄደሽ ትንሽ ወንድምሽን ፈልጊው። አበባ ሊቀጥፍ ከሄደ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ሆኖታል። እስከ አሁን አልተመለሰም» አሉ ሴት አያቷ።

አኔት ሸክሟን መሬት ላይ ጣል አደረገችው። ሴት አያቷ በዳኒ ጉዳይ እንዲሁ የሚጨነቁ መሰላት። ሰው ሁሉ ያውቀዋል፤ ታዲያ እየተዘዋወረ ከሜዳ ላይ አበባ ሲለቅም ምን ይነካዋል? ሰው ሁሉ ይወደዋል።

«ከአባታችን ጋር ወደ ጫካ ሄዶ ይሆናል። ቶሎ ወደዚያው ሄጄ እፈልገዋለሁ። በፊት ግን ትንሽ ዳቦ በማርማላት ልቀማምስ፥ እርቦኛል» አለች።

ሴት አያቷ መንገዱን እያዩ ለመጠበቅ ወደ በረንዳው ሲወጡ፥ አኔት ዳቦዋን በቅቤና ማርማላት ትበላ ጀመር። አኔት በመመገብ ላይ እያለች ነበር አባቷ የመጡት።

«ዳኒ የታለ?» አሉ ሴት አያት የአኔትን አባት እያዩ፥ «ከአንተ ጋር አልነበረም? ወደነበርክበት ጫካ አልመጣም?»



«ዳኒ?» አሉ የአኔት አባት በመደነቅ። «ወደ እኔ አልመጣም። መቼ ነው ከአንቺ የተለየው እማማ?»

የእነ አኔት ሴት አያት ያልተጨነቁ ለመምሰል የሚያደርጉትን ሙከራ ተዉትና፥ «ከአንድ ሰዓት ተኩል በፊት ነው ከእኔ የተለየው። ከድመቱ ጋር። በአካባቢው ካለው ሜዳ አበባ ሊቀጥፉ ነበር የሄዱት። አንድ ነገር ደርሶበታል ማለት ነው!»

አኔትና አባቷ ተያዩ፤ ሁለቱም ተጨነቁ። ከጫካ የመምጫው መንገድ ሜዳውን አቋርጦ የሚያልፍ ሲሆን፥ የዳኒ አባት በዚያ ሲመጡ ዳኒን አላዩትም። አኔት የአባቷን እጅ ያዝ አደረገችና፤

«ምናልባት አንተን ለመፈለግ በጫካው ውስጥ እየተቅበዘበዘ ይሆናል። እንሂድና እንፈልገው። ድመቲቱ ከላውስ ዳኒ የሄደበትን አቅጣጫ ልታሳየን ትጠብቀን ይሆናል። እርሷ ረጅም ጉዞ አትወድም።» አለች አኔት።

ተራራው ላይ ወደ አለው ጫካ አብረው ጉዞ ጀመሩ። አባቷ ያሰቡትን ሊነግሯት ስለአልፈለጉ ጉዟቸው ፀጥታ የሰፈነበት ነበር። በፀደይ ወራት በስዊዘርላንድ ተራራዎች ላይ አንዳንድ አደጋዎች ይፈጠራሉ። የበረዶ ክምር ሲቀልጥና ድንገተኛ ናዳ ሆኖ ሲወርድ ከባድ አደጋ ያደርሳል። ዳኒ ደግሞ በጣም ትንሽ ልጅ ነበር።

የእነ አኔት ሴት አያት ብቻቸውን ስለ ቀሩ ወደ ቤት ተመልሰው ይጸልዩ ጀመር። ሲጸልዩ ሳለ አንድ ራእይ አዩ። አያቶች በሥጋዊ ዓይናቸው ማየት እያቃታቸው በሄዱ ቁጥር በግልጥ በአእምሯቸው ያያሉ። በዚህ ጊዜ የአኔት አያት የተመለከቱት፥ አንድ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነበር። ጫካው ውስጥ በትልልቅ ቋጥኞች መሀል የሚፈስና በበረዶ ናዳ የተገደበ ወንዝ አለ። ዳኒ አበቦች ይዞ በወንዙ አቅራቢያ ባለ መተላለፊያ ይሮጣል። ነጫጭ ክንፎች ያሉት አንድ መልአክ አብሮት አለ። በክንፎቹ ጥላ ውስጥ መጠጊያ፥ ሙቀትና ደኅንነት ነበሩ።

«ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ» (ማቴ. 18፡10)፥ የሚለው ቃል ወደ አሳባቸው መጣና ሰላም እየተሰማቸው ከተንበረከኩበት ተነሥተው እራት ይሠሩ ጀመር።

ዳኒ ወይም ድመቲቱ ከላውስ ሜዳው ላይ ወይም የጥድ ዛፍ ባለበት አካባቢ አልነበሩም። አኔት እና አባቷ ዳኒን በስሙ እየጠሩ በአካባቢው ፈለጉት። ነገር ግን ከገደል ማሚቶና ከፏፏቴ ድምፅ በቀር የሚሰማ ነገር አልነበረም። ፀሐይዋ በተራራዎች አናት አልፋ ወደ ማደሪያዋ ማምራት ስለ ጀመረች ሜዳው ላይ የሚታየው ጥላ እየረዘመ ሄደ።

«አባዬ» አለች አኔት ፈጠን ባለ አነጋገር፥ «ዳኒ ወደ ሉሲየን ቤት ሄዶ ይሆን? ከዚህ ቀደም ሉሲየን ዳኒን ሲያነጋግረው ካንዴም ሁለቴ አይቻለሁ። ወደ እነ ሉሲየን ቤት ልሩጥና ጠይቄ ልምጣ።»

በበረዶ ወንዞች ላይ እየዘለለችና በሣሩ ላይ እየሮጠች እነሉሲየን ቤት ለመድረስ አምስት ደቂቃ እንኳን አልወሰደባትም። የጓሮው በራቸው ክፍት ነበር። አኔት ወደ ውስጥ አየት አደረገችና፥

«የሉሲየን እናት፥ ሉሲየን? ዳኒን አላያችሁትም?» አለች።

ቤቱ ፀጥ ያለና ባዶ ቢመስልም፥ ክፍት ስለሆነ፥ ሰዎቹ ከአካባቢው ርቀው የሄዱ አይመስልም። አኔት በከብቶች በረት በኩል አቋርጣ ልትሮጥ ስትል የሉሲየን እናት ወደ ቤታቸው ሲመጡ አየቻቸውና ወደ እርሳቸው ሮጠች።

«እማማ» አለች እጃቸውን እየያዘችና በጉጉት እያየቻቸው፥ «ትንሹን የእኛን ዳኒን አይተውታል? ጠፋብን፥ ካየነው ሁለት ሰዓት ሆኗል። ከሉሲየን ጋር ይሆን? ከሆነ፥ ሉሲየን እራሱ የታለ?»

«ይሆን ይሆናል። ሉሲየን ያለበትን ቦታ ትነግሩኝ እንደሆነ ብዬ ወደ ቤታችሁ ጎራ ብዬ ነበር። ሰነፉ የእኔ ልጅ ከዚህ ቀደም ብሎ ወደ ቤት መምጣት ነበረበት። ላሟ እንድትታለብ እምቧ በማለት ላይ ናት። እስካሁን ካልመጣ እንግዲህ እኔው አልባታለሁ። ከመጣ በቀጥታ ወደ በረት ነው መሄድ ያለበት። እስቲ እንሂድና እንየው» አሉ የሉሲየን እናት።

ሁለቱም ወደ ከብቶች በረት ሄዱና ከባዱን የእንጨት በር ከፈቱት። ቀይዋ ላም መሬቱን በእግሯ እየረገጠች ጅራቷን ታወዛውዛለች። ሉሲየን ግን በአቅራቢያው የለም። የሉሲየን እናት በቁጣ መለስ ብለው ለመውጣትና በሩን ለመዝጋት ሲዘጋጁ አኔት የቀሚሷን እጅጌ ሰብስብ አድርጋ ጣቷን አወጣችና፥

«ያዳምጡ፥ ቆጡ ላይ የሚሰማኝ ድምፅ የምንድን ነው?» አለች።

ሁለቱም ፀጥ ብለው ለጥቂት ጊዜ አዳመጡ። ከበላያቸው ባለው የሣር ማከማቻ ቆጥ ላይ የልጅ ለቅሶ ይሰማል።



አኔት እንደ ትንሽ የጫካ ድመት ፈጠን ብላ ድምፅ ወደ ተሰማበት ቆጥ በሚያስወጣው መሰላል ወደ ላይ ጉዞ ጀመረች። የሉሲየን እናትም እንደ ምንም እየታገሉ ተከተሏት። አንድ ያልተስተካከለ ነገር መኖሩን ሁለቱም ተገንዝበዋል። አኔት ስለ ዳኒ፥ ሴትዮይቱ ደግሞ ስለ ሉሲየን ብቻ ነበር የሚያስቡት።

«ሉሲየን ልጄ! ምንድን ነው ነገሩ? ምን ደረሰብህ?» አሉ የሉሲየን እናት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው።

«ዳኒስ? የት ነው ያለው? ምን አደረግከው? አምጣው!» አለች አኔት የሉሲየን እጅ ይዛ በሹክሹክታ።

ሉሲየን ሣሩ ውስጥ ውሽቅ እያለ እራሱን በኃይል ነቀነቀ። በጣም ፈርቷል።

«የት . . . እንዳለ. . . አላውቅም. . . የእኔ ጥፋት አልነበረም» የለቅሶ በሚመስል ድምፅ።

«ምንድን ነው ያንተ ጥፋት ያልሆነው?» አለች አኔት በኃይል እየነቀነቀችው፤ «የት ነው ያለው? ትዋሻለህ እንጂ ታውቃለህ! እባክዎ እማማ እውነቱን ተናገር ይበሉት!»

የሉሲየን እናት አኔትን በመጎተት ዘወር እንድትል አደረጉና ወደ ልጃቸው በርከክ አሉ። ዳኒ አንድ ክፉ ነገር እንደ ደረሰበትና ሉሲየንም ነገሩን እንደሚያውቅ በመገመት ፊታቸው በድንጋጤ ነጣ። ሉሲየንን ከተኛበት ሳብ በማድረግ ፊቱን ወደ ራሳቸው አዞሩት።

«ሉሲየን» አሉ የትእዛዝ በሚመስልና በተረጋጋ ድምፅ፥ «ቶሎ ንገረኝ፥ ዳኒ የት አለ?»

በቁጣ ትኩር ብሎ እየተመለከታቸው ምንም የማምለጫ መንገድ እንደሌለው ተረዳ።

በስቅታ ድምፅ «ሞቷል» አለና ፊቱን እንደገና ሣሩ ውስጥ በመቅበር ያለቅስ ጀመር።

አኔት ሉሲየን የተናገረውን ብትሰማም፥ ለጥቂት ጊዜ ሁለንተናዋ ስለ ደነዘዘ አልተንቀሳቀሰችም። የሉሲየን እናት ሕሊናዋን ትስታለች ብለው እስኪጠረጥሩ ድረስ ፊቷ ሕይወት የሌለው እስኪመስል ነጭ ሆነ። ሊያቅፉአት ቢሞክሩ ፈንጠር አለችና፤

«የሞተበትን ስፍራ ያሳዩን። አባቴ አስከሬኑን ወደ ቤት ይወስደዋል። ከዚያ በኋላ እኔ ሉሲየንን እገድለዋለሁ» አለች ሲቃ በሚተናነቀው ድምፅ።

የንግግሯን የመጨረሻ ክፍል የሉሲየን እናት ልብ አላሉትም። መጀመሪያ የተናገረችው ግን ቁም ነገር መሆኑን አመኑ። እጇን ይዘው በመጎተት ልጃቸው እንዲቆም ካደረጉት በኋላ የመሸከም ያህል ይዘውት በመሰላሉ ወረዱ።

«ዳኒ ያለበትን ልታሳየን ይገባል፤ ቶሎ። ያለዚያ የልጁ አባት ፖሊስ ይዞ በመምጣት ይወስድሃል» አሉ በጥድፊያ።

የእናቱ ማስፈራራት ስለ አስጨነቀው፥ ወደ ተራራማው ስፍራ ለመሄድ ባለው ፍጥነት ይጓዙ ጀመር። በጉዞው ወቅት አልፎ አልፎ ጥፋቱ የእርሱ አለመሆኑን እያለቀሰ ይናገራል። እናቱ እና አኔት ተከትለውታል። እናቱ እንደ እርሱ ያለቅሳሉ፤ አኔት ግን አንዲት እንባ ጠብታ አልወጣትም። ከቁጣና ከኀዘን የተነሣ እንባዋ የደረቀባት መሰለች።

ግድግዳው ወደ አለበት ስፍራ በፍጥነት ደረሱ። ሉሲየን ቆም ብሎ በመጨለም ላይ ወደ አለው ገደል አመለከታቸውና፥ «እዚያ ነው ያለው፤ ውኃው ውስጥ ሰጥሟል፥» አለ በሹክሹክታ ድምፅ። ከዚያም መሬቱ ላይ በመውደቅ ፊቱን ሣሩ ውስጥ ቀበረ። በዚህ ጊዜ የዳኒ አባት ከጫካው ዳር ወጥተው እነ እኔት ወደ አሉበት በፍጥነት መጡ።

ሉሲየንን ልብ አላሉትም። አኔትን አየት አድርገዋት ግዙፉን ቋጥኝ ተመለከቱ። ያኔ ነበር ሌሎቹ ልብ ያላሉትን አንድ ነገር ያዩት። ነጭ የድመት ግልገል ወጣ ባለው ቋጥኝ ላይ ተንጠላጥላ ትንቀጠቀጣለች። ይህን እንደ ተመለከቱ ለጊዜው ሌላ ቃል አላስፈለጋቸውም። «ገመድ ላምጣ፥» ብለው ከፉ የጫካ አውሬ እንዳባረረው ሰው በተራራው ቁልቁለት ተንደረደሩ።

የእነ አኔት ሴት አያት ቤታቸው በር ላይ ቆመው ነበር። የልጃቸውን ፊት ተመልከተው ለማወቅ የፈለጉትን ሁሉ በአንድ ጊዜ ተረዱ። የአኔት አባት ገመዱን ከተንጠለጠለበት ግድግዳ ላይ አውርደው ሲሮጡ በዝምታ ተመለከቷቸው። ወደ ኋላ ዘወር ብሎ፥

«ገደሉ ውስጥ፥» የሚል ድምፅ አሰሟቸውና በሩጫ ከእይታቸው ተሠወሩ።

የአኔት አያት ብቻቸውን ቢቀሩም፥ ለሚፈጠረው ነገር ዝግጁ ሆነው ለመጠበቅ ሲሉ፥ ውኃ ምድጃ ላይ ጣዱ፥ አሮጌ አንሶላዎችን ሰበሰቡ፥ ሌላም አስፈላጊ ናቸው ብለው ያሰቧቸውን ነገሮች አሰናዱ። ከዚያም



ቁጭ ብለው እጆቻቸውን አጣመሩ፤ ዓይኖቻቸውንም ከደኑ። እንደገና ዳኒ በአሳባቸው ታያቸው። ገደል ሥር ባለ ድፍርስ ውኃ ውስጥ ሰጥሟል። የመልአኩ ነጫጭ ክንፎች ግን ውኃውን ከመሄድ ገድበውታል። ዳኒ እጆቹ በመልአኩ ተይዘው በደህና ሁኔታ ላይ ነው።

«ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል» (ሉቃስ 4፡10) አሉ በሹክሹክታ። ከዚያም የዳኒን መኝታ ለማዘጋጀት ወደ መኝታ ክፍሉ አመሩ።

የዳኒ አባት ገመዱን ይዘው በሚያስደንቅ ፍጥነት ቢመለሱም፥ ለሚጠብቋቸው ሰዎች ግን ሰዓቱ ረዝሞባቸው ነበር። ገመዱን አንድ ትልቅ ግንድ ላይ አሥረው ቁልቁል ወደ ቋጥኛማው ገደል ሲለቁት፥ ዝም ብሎ ከመመልከት በስተቀር ማንም አላናገራቸውም። ገመዱን በእጆቻቸውና በእግሮቻቸው በመያዝ በቋጥኙ ላይ በማለፍ ወደ ገደሉ ወርደው ተሰወሩ። ገመዱን ይዘው አየር ላይ እንደ ተንጠለጠሉ በፍጥነት የሚወርደውን ወንዝ በድፍረት ተመለከቱ። ያ ወንዝ መሆን አለበት ልጃቸውን የወሰደባቸው። የተመለከቱት ነገር ትልቅ ተስፋን ወደ ልባቸው፥ ለቅሶን ደግሞ ወደ አፋቸው አመጣ።

የእነ አኔት ሴት አያት እንዳሉት፥ ዳኒ ወደ ገደሉ በወደቀ ጊዜ መላእክት ከጉዳት ጠብቀውት ውኃው ዘንድ አልደረሰም። ከገደሉ ወጣ ባለና ሜዳማ ወለል ባለው ስፍራ ላይ ነበር የወደቀው። እግሮቹ ወደ ኋላ ታጥፈዋል። መንቀሳቀስ ስለ አቃተው እያለቀሰ ከዚያ የሚያነሣው ሰው ይጠብቃል። ከወደቀ ወዲህ በነበረው የሁለት ሰዓት ጊዜ ስለሆነው ነገር ብዙም የሚያስታውሰው ነገር ባለመኖሩ እንቅልፍ እንደ ወሰደው ገመተ። ትዝ የሚለው ነገር አባቱ ከበላዩ እንደ ትልቅ አሞራ አንዣብበው ከወረዱ በኋላ አጠገቡ መንበርከካቸው ነበር።

«አባባ፥» አለ ዳኒ፥ ድክም ባለ ድምፅ፥ «ክላውስ የታለች?»

«ከበላይህ ባለው ቋጥኝ ላይ ናት። ስንመለስ ይዘናት እንሄዳለን» አሉ ትኩር ብለው እያዩት።

«አባዬ፥ እግሬን ያመኛል፥ ለመራመድ አልችልም። ወደ ቤት ተሸክመህ ትወስደኛለህ?» አለ ዳኒ።

«አዎ፥ እወስድሃለሁ፤ ልወስድህ ነው እኮ የመጣሁት። አሁኑኑ እወስድሃለሁ» አሉና የዳኒን እጅ ይዘው አነሡት።

«እኔንና ድመቴን ልትሸከመን ትችላለህ? እርሷን አትተዋትም አይደል? አሁን ወተቷን የምትጠጣበት ሰዓት ነው፥ በጣም ጠምቷታል» አለ ዳኒ ድክም ባለ ድምፅ።

«ድመትህን ኪሴ ውስጥ ከትቼ ነው የምወስዳት፥» አሉ አባቱ ዳኒን በቀስታ እያነሡ፥ ዳኒ ሲንቀሳቀስ እግሩን ስለ አመመው አቃሰተ። ነገር ግን አባቱን ትኩር ብሎ ይመለከት ስለነበር፥ የአምስት ዓመት ልጅ ሊኖረው የሚችለውን ጥንካሬ ያህል በረታ።

ዳኒና አባቱ ወደ ቤት ያደረጉት ጉዞ ረጅምና ቀስ ያለ ነበር። የዳኒ አባት ልጃቸውን በእጃቸው ይዘው በገመድ ወደ ላይ ለመውጣት አልቻሉም። ቀስ እያሉ ወደ ታች እስከ ወንዙ ወረዱና ዳር ዳሩን በመሄድ ምቹ ስፍራ ዘንድ ሲደርሱ ወደ ላይ ወደ ተራራው ወጡ። ይህ ሁሉ ሲሆን ዳኒ እንቅልፍ ወስዶት ነበር። የነቃው አባቱ አኔት አለችበት ቦታ ደርሰው ሣር ላይ ሲያጋድሙት ነበር።

«ድመቴ ኪስህ ውስጥ ናት?» አለ ሣሩ ላይ ተጋድሞ ዓኖቹን ገና እንደ ገለጠ።

አባቱ፥ «አሁን አመጣታለሁ» አሉና ቀደም ሲል ያሰሩትን ገመድ ይዘው እንደገና ወደ ገደሉ በመውረድ ድመቲቱን ይዘዋት መጡ። ዳኒ እጆቹን ዘርግቶ ከአባቱ ተቀበላት። ደረቱ ላይ ልጥፍ በማለት እንደ ትንሽ ሞተር «ኩርርር» ትል ጀመር። አኔት እንደ ህልም በሆነባት በዚያ ምሽት ለመጀመሪያ ጊዜ አለቀሰች።

አባቱና የሉሲየን እናት ዳኒን በአንድ ትልቅ ኮት ላይ አጋደሙትና በቀስታ ወደ ቤት ወሰዱት። አኔት ደግሞ ድመቲቱን ይዛ ተከተለቻቸው። ጉዞው ኀዘን የተቀላቀለበት ቢሆንም፥ ዳኒ ከሞት ስለ ተረፈና ለመናገር በመቻሉ የሰው ሁሉ ልብ በምስጋና ደስታ የተሞላ ነበር። ለጊዜው ይህ በቂ ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆን ማንም፥ እናቱ እንኳን ስለ ሉሲየን አላሰቡም። እርሱ ግን አሁንም እንደ ቀድሞው ፊቱን ድርቆሽ ሣር ውስጥ ቀብሮ ተኝቷል። ቀና ብሎ ሲመለከትና በዚያ ምሽት ብቻውን መቅረቱን ሲረዳ፥ የዓለም ሰው ሁሉ የጠላውና የረሳው መሰለው። ብድግ ብሎ በቀስታ ወደ ቤቱ ከሄደ በኋላ እየተንቀጠቀጠ አልጋው ላይ ወጣ። በዓለም ካሉት ልጆች ሁሉ እጅግ መከረኛውና ብቸኛው እርሱ የሆነ መሰለው።



# ምዕራፍ ሰባት
# አኔት በቀል ዐቀደች



ዳኒ ሞቃት ብርድ ልብሶች ደርቦ አልጋው ላይ ተኝቷል። በጣም ጠቃሚና የሚያስፈልገው ሁሉ ወዲያውኑ የሚቀርብለት ሰው መሆኑ ይሰማዋል። እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ ቀደም ሆኖ ስለማያውቅ፥ በአጋጣሚው በመጠቀም ላይ ነበር።

የዳኒ አባት አልጋው አጠገብ ቆመው ዳኒ በጣም የሚወዳቸውን አስቂኝ ተረቶች ይነግሩታል። አኔት ደግሞ ቸኮሌት ይዛ ዳኒ አልጋ ላይ ተቀምጣለች። ድመቲቱ ከላውስ ዳኒ ደረት ላይ ጥቅልል ብላ ተኝታለች። ሴት አያቱ ማርማላት እንደ ያዙ ከዳኒ መኝታ በሌላ አቅጣጫ ተቀምጠዋል። በፈለገ ጊዜ ሁሉ በማንኪያ እያደረጉ ይሰጡታል። የእግሩ ሕመም ባይጠዘጥዘው ኖሮ እንዲያ ደስ በሚል ሁኔታ ውስጥ መኖሩ ዳኒ መንግሥተ ሰማያት ውስጥ እንዳለ እንዲያስብ ያደርገው ነበር።

«አባዬ፥ ድመቴ በእርግጥ ጉዳት አልደረሰባትም?» አለ ዳኒ።

«በእርግጥ ጉዳት አልደረሰባትም። አንድ ሳህን ሙሉ ወተት ጠጥታ ጭራዋን ወደ ላይ በማቆም ነው አሁን ወደ ፎቅ የወጣችው። ጤነኛ የድመት ግልገሎች ብቻ ናቸው እንደዚያ የሚሆኑት» አሉ አባቱ።

«አባዬ፥ ሉሲየን እኮ ነው ድመቴን ወደ ገደሉ የጣላት። ሉሲየን በጣም ጨካኝ ነው፤ አይደል?» አለ ዳኒ። ሲናገር አንድ ማንኪያ የፍራፍሬ ጭማቂ ለመጉረስ አፉን እንደ ወፍ ጫጩት ከፍቶ ነበር።

«በጣም ጨካኝ ነው። ላደረገው ጥፋት ይቀጣል» አሉ አባቱ። እንዲህ ይበሉ እንጂ ልጃቸው በሕይወት በመኖሩና ደህና ሆኖ ስለ ሉሲየን ለማሰብ በመቻሉ በጣም ደስ ብሏቸዋል። አኔት ነበረች፥

ቸኮላት ይዛ በፀጥታ እንደ ተቀመጠች፥ ከማንም ይልቅ ስለ ሉሲየን የምታስበው።

«አልቻኩልም፥» አለች በአሳቧ፥ «ነገር ግን በሕይወት እስካለሁ ድረስ በፍጹም ይቅርታ አላደርግለትም። አንድ ቀን አንድ አሳዛኝ ነገር አደርግበታለሁ። በፍጹም ይቅርታ አላደርግለትም፤ በጭራሽ።»

«አኔት፥ ቸኮላቱን ስጪኝ፥ በልቼው ልተኛ። አንቺ ግን እግሬን ስለሚያመኝ እዚሁ ቆዪልኝ» አለ ዳኒ።

«እሺ ዳኒ፥ እንቅልፍ እስኪወስድህ ከአንተ ጋር እቆያለሁ» እያለች ቸኮላቱን ሰጠችው።

አባቱና ሴት አያቱ እየሳሙት ወጡ። አኔት እቅፍ አደረገችው።

«ዘምሪልኝ፤ የምወደውን መዝሙር ዘምሪልኝ» አለ እንደ ትእዛዝ ባለ ድምፅ።

መዝሙሩ እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር እንዲልና ትንንሽ ልጆችን ከአደጋ እንዲጠብቃቸው የሚጠይቅ ነበር። አኔት ልቧ በጥላቻና በበቀል ስለ ተሞላ ልትዘምረው አልፈለገችም ነበር። ዳኒ እንድትዘምር ስለ አስገደዳት እያዘነች ዘመረችው። መዝሙሩን ስትጨርስ፥ ዳኒ የቸኮላት ትርፍራፊውን ትራሱ ላይ እንዳንጠባጠበ አንቀላፍቷል። እርሷም አጠገቡ ጋደም አለች። በጣም ቢደክማትም ከሥጋት ስለ አረፈች አለቀሰች። እንባዋ የደስታ ብቻ ሊሆን አይችልም፤ ምክንያቱም ሌላውን ሰው የምንጠላ ከሆነ እውነተኛ ደስታ ሊኖረን አይችልም።

ከአልጋው ላይ ተነሣችና በረጅሙ ተንፍሳ ወደ ታችኛው ክፍል ለመሄድ የፎቁን ደረጃ ትወርድ ጀመር። አባቷ ከከብቶቻቸው ጋር ውጭ ነበሩ። ከብቶቹ እንደዚያን ዕለት ሳይታለቡ ቆይተው ስለማያውቁ፥ ትዕግሥታቸው አልቆ መሬቱን በእግራቸው እየደበደቡ ይጮሃሉ። የአኔት ሴት አያት ምግብ በመሥራት ላይ ናቸው። እርሳቸውም ሆኑ የአኔት አባት ከምሳ ወዲህ ምግብ አልቀመሱም። ምክንያቱም ሰው ሁሉ ከዳኒ መጥፋት በቀር ሌላ ነገር የማሰቢያ ጊዜ አልነበረውም።

አኔት አያቷ ወደ አሉበት ጓዳ ከሄደች በኋላ፥ «ተኝቷል» አለችና የደከመ ሰውነቷን ወንበር ላይ አሳርፋ ምድጃውን ትመለከት ጀመር።

«ሐኪሙ ቶሎ እዚህ ስለሚደርስ ያኔ እንቀሰቅሰዋለን። አሳዛኝ ነገር። ግድ የለም እንቅልፉ ከመጣ ይተኛ።»



አኔት ለጥቂት ጊዜ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ፥ «አያቴ፥ ሉሲየን መቀጣት አለበት። ቅጣቱ ምን ሊሆን ይገባል ትያለሽ? ዳኒ ላይ ካደረሰው ጥፋት ጋር የሚመጥን ከባድ ቅጣት አስቤ ላገኝ አልቻልኩም» አለች።

አያቷ ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ፥ «ክፉ ነገር ባደረግን ጊዜ፥ ማንም ጣልቃ ሳይገባ ክፉ ሥራችን ራሱ ቅጣት ሊያመጣብን እንደሚችል አስተውለሽ ታውቂያለሽ አኔት?» አሉ።

የለም፥ አኔት ስለዚህ ነገር አስባ አታውቅም።

«ዳኒ ሲወድቅ ባየው ጊዜ ሉሲየን ስለ ተሰማው ድንጋጤ እስቲ አስቢ። ዛሬ ማታ እንዴት ባለ አስፈሪና አስደንጋጭ ሁኔታ ውስጥ እንዳለ አስቢ፤ ሰዎች ድርጊቱን እንዳያውቁበት ምን ያህል እንደሚፈራ ገምቺ። ይህን ካሰብሽ በኋላ የሚገባውን ቅጣት አልተቀጣም ትያለሽ? ይቅርታ ልናደርግለትና እንደ ቀድሞው በሰላም እንዲኖር ልንረዳው አይገባም?» አሉ አያቷ።

አኔት ከአያቷ ንግግር ልብ ያለችው፥ «ሰዎች ድርጊቱን እንዳያውቁበት ምን ያህል እንደሚፈራ ገምቺ» የሚለውን ብቻ ነበር። ያ ግሩም አሳብ ነበር። የሉሲየንን ድርጊት ሰው ሁሉ እንዲያውቀው ታደርጋለች። በሄደችበት ሁሉ ድርጊቱን ሰው እንዲያውቀው ለማድረግ የተቻላትን ሁሉ ታደርጋለች። በድርጊቱ ምክንያት ሰው ሁሉ እስኪጠላው ድረስ በመንደሪቱ ላሉትና ትምህርት ቤት ለሚገኙ ልጆች ሳይቀር ትነግርበታለች።

አሳቧ የተቋረጠው በሩ በችኩላ አመታት ሲንኳኳ ነበር። የሉሲየን ታላቅ እኅት ነበረች የመጣቸው። ለሥራ ከሄደችበት ከተማ ስትመለስ እነ አኔት ዳኒን ይዘው ወደ ቤት ሲመጡ አግኝታቸው ነበር። የተፈጠረውን ነገር ከተረዳች በኋላ፥ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ወደሚገኘው ዶክተር ስልክ ለመደወል መንደሪቱ ውስጥ ወደሚገኘው ፖስታ ቤት ሮጠች።

«ዶክተር ፒሊያርድ ሊመጣ አይችልም። አንዲት ሕመምተኛ ሴት ለማከም ወደ ሌላ መንደር ሄዷል። እስከ እኩለ ሌሊት ወደ ቤቱ አይመለስም። አንዳንድ ሰዎች ‹ዳኒን በጋሪ ወደ ሆስፒታል ውሰዱትና ዶክተሩ እዚያው ያክመዋል› ይላሉ» አለች ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለ።

«አመሰግንሻለሁ ማሪዬ፥ ለእኛ ስትዪ ተቸገርሽ» አሉ የአኔት ሴት አያት ወደ ወጥ ቤት እየተመለሱ። ማሪዬ የሆነውን ነገር በትክክል ለማጣራት ቁጭ አለችና፥

«እስቲ ንገሪኝ አኔት፥ እንዴት ነው አደጋው የደረሰው? እናቴስ ለምንድን ነው ዝም የምትለውና የምትጨነቀው?» አለች ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ።

«እላይ ተራራው ላይ ነው አደጋው የተፈጠረው። ሉሲየን የዳኒን ድመት ገደል ውስጥ ጣላት ዳኒ ድመቲቱን ሊያድናት ሲሞክር ሉሲየን አልከለከለውም። ሆን ብሎ ወደ ገደሉ ገፍቶትም ሊሆን ይችላል። የዳኒ እግር ሳይሰበር አይቀርም። እወደቀበት ስፍራ ለብዙ ሰዓት ሲቆይ ሉሲየን ለማንም አልነገረም። ዳኒ ይሞት ነበር» አለች አኔት ቁርጥርጥ በሚል አነጋገር።

ማሪዬ በሰማችው ነገር ተሳቀቀች። ታናሽ ወንድሟን በጣም አታቀርበውም። ብትወደውና ብታቀርበው ኖሮ ሉሲየን ምናልባት ከአሁኑ የተሻለና ጥሩ ልጅ ይሆን ነበር። ፍቅር ያላገኙ ወይም ያልተወደዱ ልጆች ሌሎችን መውደድ ያቅታቸዋል።

«በከባድ ሁኔታ ሊቀጣ ይገባል። እኔ ነኝ ያን የማደርገው» አለች ማሪዬ በፍጥነት ከቤት እየወጣች። አኔት በደስታ ፈገግ አለች። በሉሲየን ላይ የገዛ ቤተሰቦቹ መነሣታቸው የምትፈልገው ነገር ነበር። ብቀላ የጀመረች መሰላት።

ከእንግዲህ በዚያ ምሽት የሚጠበቅ ነገር አልነበረም። ዝምታ በበዛበት ሁኔታ እራት ከተበላ በኋላ አኔት በድካምና በኀዘን ስሜት ወደ መኝታዋ ሄደች። ሻማ ለኮሰችና እንባ ባቀረሩ ዓይኖቿ ዳኒን ተመለከተችው። ወፍራም ፀጉሩ ወደ ኋላ ሆኖና እጆቹን ግራና ቀኝ ዘርግቶ ተኝቷል። የቀድሞ ሰላሙ ግን በገጽታው ላይ አይታይም። በእንቅልፍ ልቡ እንኳን ፊቱ የተከፋ ነው። በመወራጨት እራሱን ግራና ቀኝ እያወዛወዘ በጭንቀት ቃላት ያጉተመትማል።

አኔት መስኮቱ አጠገብ ካለው አልጋዋ ላይ ተኛች። ይሁን እንጂ፥ ምንም ቢደክማት እንቅልፍ አልወሰዳትም አላት። ብቻዋን ያለች መሰላት። ትንሽ ቆይታ በቀስታ የሚሄድ ሰው እርምጃ ተሰማትና ሴት አያቷ ወደ መኝታ ቤቱ ገቡ። ደስ አላት፥ አኔት። በፎቁ ደረጃዎች ወደ ላይ መውጣቱ ቁርጥማታቸውን እየቀሰቀሰ እግራቸውን



ስለሚያሳምማቸው ሴት አያቷ ብዙ ጊዜ ወደ አኔት መኝታ ቤት አይመጡም ነበር።

«አያቴ!» አለች አኔት እጆቿን እየዘረጋችላቸው።

ሴት አያቷ ምንም ሳይናገሩ አልጋው ላይ በመቀመጥ አኔት የጀመረችውን ለቅሶ እስከታቆም ድረስ እራሷን አሻሹላት።

ከዚያም፥ «ስሚ ልጄ፥ ዳኒ ገና ትንሽ ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደነው እንዲጠብቀው ኢየሱስን በእምነት ጠየቅነው። በየዕለቱ ጸሎታችንም በእጆቹ ይደግፈውና ይጠብቀው ዘንድ እግዚአብሔርን ለምነነዋል። እርሱም አልተወውም። ሁል ጊዜ የእግዚአብሔር እጆች ዳኒን ይጠብቁታል። ሞቶ ቢሆንም እንኳን በቀጥታ ወደ መንግሥተ ሰማያት ነበር የሚወስደው። ስለዚህ ማልቀሳችንን እንተውና እርሱ እንደሚጠብቀው፥ እንዲሁም ከሁሉ የሚበልጠውን መልካም ነገር እንደሚያደርግለት በእግዚአብሔር መታመናችንን እንቀጥል» አሉ።

«ለምንድን ነው ግን ሉሲየን ዳኒን እንዲጎዳው እግዚአብሔር የፈቀደው? አያቴ፥ ልገድለው እስከመኝ ድረስ ሉሲየንን በጣም እጠላዋለሁ» አለች አኔት።

«እንግዲያው ለዳኒ ልትጸልዪለት አትችይም። እግዚአብሔር ፍቅር ነው። በምንጸልይ ጊዜ ወደ ፍቅር ስለምንቀርብ፥ ጥላቻችን ሁሉ ፀሐይ ሲወጣበት እንደሚቀልጥ በረዶ ሊሟሟ ይገባል። ሉሲየንን ለእግዚአብሔር ተዪው፥ አኔት። እግዚአብሔር ለመልካምም ሆነ ለክፉ ሥራ የሚሰጠው ዋጋ አለ። እግዚአብሔር ልክ ዳኒን የሚወደውን ያህል ሉሲየንንም የሚወደው መሆኑን አትርሺ።»

ይህን ብለው አኔትን ሳሟትና ሄዱ። አኔትም አያቷ የተናገሯትን ቁምነገሮች ስታሰላስል ቆየች። በመጨረሻ የተናገሩትን ግን አላመነችበትም። እግዚአብሔር ጨካኙን፥ አስቀያሚውንና ደደቡን ሉሲየንን ከመልካሙና ከቆንጆው ዳኒ እኩል ይወደዋል መባሉ የሚታመን አልነበረም። አያቷ በንግግሯ የመጀመሪያ ክፍል የገለጡት ግን እውነት ነበር። ያ ነበር ያስጨነቃት። አያቷ እንዳሉት ሉሲየንን የመበቀል ቂም በልቧ ይዛ ለዳኒ ለመጸለይ አትችልም። ሁለቱ ነገሮች፥ ማለት ቂምና ጸሎት በአንድ ላይ ሊኖሩ አይችሉም። ለዳኒ ለመጸለይ ፈለገች። ያ የሚሆነው ግን ጥላቻዋን ካስወገደችና ሁለተኛ

እንዳይመለስ ካደረገች ነበር። ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት ግን በቀሉ መፈጸም አለበት።

እርሷ የበቀሏን ዕቅድ በማሰላሰሉ እየቀጠለች፥ ሴት አያቷን እንዲጸልዩ ልታደርጋቸው ትችላለች። ልክ ይህን በአሳቧ እንደ ወሰነች፥ ዳኒ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ በግማሽ እንቅልፍ ልቡ በሚያስፈራ ሁኔታ ያለቅስ ጀመር።

«ክላውስ!» አለ! «የታለች ክላውስ? ወንዙ ውስጥ ወደቀች እኮ።»

አኔት በሩጫ ወደ እርሱ ሄደችና፥ «አይደለም! አይደለም! እዚህ ነው ያለችው!» እያለች አባበለችው። ከዚያም ድመቲቱን ከአልጋው ግርጌ አመጣቻትና ለዳኒ አሳቀፈችው። ድመቲቱ ደረቱ ላይ በመንጠራራት ላይ እንዳለች፥ እርሱ ወደ ኋላው ጋደም አለና እንቅልፉን ቀጠለ።

አተነፋፈሱ የተረጋጋና ጤነኛ እስኪሆን ድረስ፥ አኔት አጠገቡ እንደ ተቀመጠች ከቆየች በኋላ፥ አልጋዋ ላይ ወጥታ እርሷም አንቀላፋች።



# ምዕራፍ ስምንት
# የማምለጫ ዕለት



ሉሲየን በጨለማ አልጋው ላይ ተጋድሟል። እራስ ምታትና ትኩሳት ይሰማዋል። ዓይኖቹ አልተከደኑም። ምክንያቱም በከደናቸው ቁጥር ዳኒ ገደል ውስጥ ሲወድቅ እየታየው ተቸግሯል። ገደሉ የዋዛ አልነበረም። ጭው ያለና ጨለማ ነበር! መጨረሻው አይታይም። ወደ ገደሉ የወደቀ ሰው ማረፊያ መሬት ሳያገኝ ለዘለዓለም ወደ ታች ይወርዳል።

ቶሎ ቶሎ ብንን ብንን ይላል። በነቃ ቁጥር ዝቅ ያለ የሲቃ ድምፅ ያሰማል። ከአሳቡ ይልቅ በሕልሙ የሚያየው ስለሚብስ ከፍርሃቱ የተነሣ ልቡ በጣም ይመታል። ያኔ አንድ ሰው በመጣለት እንዴት ጥሩ ነበር? ብቸኝነት በጣም ያስፈራል። እናቱ በአቅራቢያው እንዲኖሩለት ይፈልጋል። ምድር ቤት ባለው ወጥ ቤት ውስጥ እንቅስቃሴያቸው ስለሚሰማው መምጣታቸውን ተረዳ። ሊጠራቸው ግን አልደፈረም። ያደረገውን ነገር ስለ ሰሙ በጣም ተቆጥተዋል። ምናልባት በዚህ ምክንያት ወደ እርሱ ላለመምጣት ወስነው ይሆናል። ከዚህም ሌላ፥ እናቱን ሲጠራ ታላቅ እኅቱ ትመጣ ይሆናል። እርሷን ለማየት ደግሞ ፍጹም አይፈልግም። ብትመጣ ልትናገር የምትችለውን ለማሰብ እንኳ አልደፈረም።

ስለ ነገ ያስብ ጀመር። ወደ ትምህርት ቤት እንደሚሄድ፣ አኔት ድርጊቱን ለሰው ሁሉ እንደ ነገረችበት አሰበ። በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ማንም እንደማይወደው፣ አስቀያሚ፣ ግልፍተኛና ጅል አድርገው እንደሚያዩት ተሰማው። አሁን ደግሞ ይብሱኑ ሁሉም ይጠላዋል። ማንም ጓደኛ ሊሆነው ወይም ክፍል ውስጥ ጎኑ ሊቀመጥ አይፈልግም። ከትምህርት ቤት መልስ አብሮት ወደ ቤት የሚሄድ ልጅም አይኖርም።

ይህን ሁሉ ሲያሰላስል ሳለ፣ በፎቁ ደረጃዎች ላይ የሰው እርምጃ ሰማ። ትንሽ ቆይቶ እናቱ ወደ ክፍሉ ገቡ። ቁጭ ብሎ እያለቀሰ እጆቹን ወደ እርሳቸው ዘረጋ። እርሳቸው ግን ወደ እርሱ አልቀረቡም። አልጋው ላይ ቁጭ ብለው ጭንቀት ባጠላበት አመለካከት አዩት።

በልባቸው በጣም አዝነዋል፤ ሊያጽናኑትም ፈልገው ነበር፤ ግን ፈሩ። ዳኒ በጣም ተጎድቶ ከሆነ ቤተሰቦቹ ምን ያደርጉን ይሆን? የሚለው ፍርሃት ነበር ያስጨነቃቸው። በሕግ የሚመጣባቸው ቅጣትና ሊከፍሉት የማይችሉትን የዳኒ ሕክምና ዋጋ አስፈራቸው። ለልጃቸው ያደላሉ እንዳይባሉ መፍራታቸውን ሊገልጡለት አልደፈሩም። ከዚህም ሌላ፣ ሉሲየን ስለ አደረገው ነገር ሊቀጡት የሚገባቸው መሆኑ ተሰምቷቸዋል።

ነገሮቹን በጣም ልብ የሚሉ አስተዋይ ሴት ቢሆኑ ኖሮ ከእርሳቸው የሚፈለግ ቅጣት ያለመኖሩን ይረዱ ነበር። ሉሲየን ለብዙ ሳምንታት የሚገጥመውን ሥቃይ፣ ብቸኝነትና የበደለኛነት ሀፍረት ሊገምቱ ይችሉ ነበር። በዚህ ወቅት የእርሳቸው ድርሻ የተቻላቸውን ያህል ሉሲየንን ማጽናናትና መርዳት መሆኑን መገንዘብ ነበረባቸው። እርሳቸው ግን ይህን የሚረዱ ሴት አልነበሩም።

«በጣም መጥፎ ልጅ ነህ ሉሲየን። ካደረግኸው ነገር የተነሣ ምን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም። የዳኒ ጉዳት ከባድ ከሆነ ወየውልን። የሚታከምበትን ገንዘብ በሙሉ መክፈል ይኖርብናል። ያን ለማድረግ አቅም ወይም ሀብት የለንም። በዚህ ጉዳይ ፖሊስ ይመጣብናል ብዬ እጠብቃለሁ። እጅግ ከባድ ነገር ነው ያደረግከው። ድርጊትህ እጅግ አሳፍሮሃል ብዬም ተስፋ አደርጋለሁ» አሉ የሉሲየን እናት በጣም እያዘኑ።

ሉሲየን የሚናገረው ነገር እስኪጠፋው ድረስ በጣም አፈረ። ለወትሮው ጥያቄ ሲቀርብለት ፈጥኖ መልስ የሚሰጥና የሚከራከር



ልጅ ስለነበር የአሁኑ ዝምታው እናቱን ግራ አጋባቸው። የሉሲየን ዝምተኛነት በእርግጥ አዲስ ነገር ነበር።

«መልካም፣» አሉ እናቱ በተረጋጋ አነጋገር፣ «ነገሮች መልካም ይሆናሉ ብለን ተስፋ ማድረግ አለብን! ነገ ወደ ዳኒ ቤተሰቦች ሄደህ በድርጊትህ መጸጸትህን ንገራቸው፤ ይቅርታ ያደርጉልህ ይሆናል።»

ለተናገሩት አሳብ ከሉሲየን መልስ ቢጠብቁም ምንም አልናገር ስለ አላቸው ጭንቅ እያላቸው ከክፍሉ ወጡ። ዘግየት ብለው በጎድጓዳ ሳህን ሾርባ ይዘው መጡ። እንዲያ ያለ ጥፋት ያጠፋ ልጃቸውን ማጽናናቱ ተገቢ አይሆን ይሆናል! ቢያንስ ግን ሊመግቡት ይገባል።

ሉሲየን ሾርባውን ተቀበላቸው፤ ሊመገብ ግን አልቻለም። ሦስት ጊዜ ከተጎነጨ በኋላ ጉሮሮውን ስለ ተናነቀው መልሶ ለእናቱ ሰጣቸው። ከዚያም ትራሱ ላይ ድፍት ብሎ ፊቱን በመቅበር ስቅስቅ አለና አለቀሰ። እናቱ የሚሉት ነገር ስለ ጠፋቸው ምንም አልተናገሩም። እራሱን በቀስታ ሲዳስሱ ቆዩና ብቻውን ትተውት ከክፍሉ ወጡ።

በሚቀጥለው ማለዳ ከእንቅልፉ ሲነቃ የሆነውን ነገር ሁሉ ለማስታወስ አልቻለም። እራሱን የሚያመውና ዓይኖቹንም የሚከብደው ለምን እንደሆነ አልተረዳም። ቀስ እያለ ነበር ከአሳቡ የጠፋው ነገር ሁሉ ወደ ትዝታው የመጣለት። ሌላም ነገር አስታወሰ። ዛሬ ወደ ትምህርት ቤቱ መሄድና ስለ ድርጊቱ ከሰሙት ልጆች ጋር ፊት ለፊት መተያየት አለበት።

ዳኒ ሌሊቱን ሞቶ ይሆናል። ይህን የሰሙ ልጆች ደግሞ ለልጁ ሞት ዋነኛ ተጠያቂ እርሱ መሆኑን ያውቃሉ።

ይህን ሲያስብ ከቆየ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ላለመሄድና ለመደበቅ ወሰነ። ይህ በጣም አያስቸግርም። ከቤታቸው በላይ አለው ጫካ ውስጥ ተደብቆ በመዋል ማምሻው ላይ ወደ ቤቱ ሊመለስ ይችላል፤ ይህን ማንም ሊያውቅበት አይችልም። እናቱ ወደ ትምህርት ቤት ሄዷል ብለው ያስባሉ፤ ትምህርት ቤት ውስጥ ደግሞ ማንም ስለ እርሱ አይጠይቅም። የሚኖረው በጣም ሩቅ በሆነው ሸለቋማ አካባቢ ነበር፤ ምንስ ቢሆን ስለ እርሱ ማን ይገደዋል? እርግጥ ነው በመጨረሻ አንድ ሰው ድርጊቱን ማወቁ አይቀርም። ዛሬ ነገሩ መሰወሩ ግን ዋና ቁም ነገር ነው። ነገ ስሜቱ ሌላ ይሆን ይሆናል፣

ወይም ዳኒ ሕመሙ ይሻለዋል። ለዛሬ ይደበቅ፥ በኋላ ማንኛውም (ክፉም ሆነ መልካም) ነገር ሊሆን ይችላል።

ከአልጋው ላይ ተነሣና ከፎቁ ወረደ። ታላቅ እኅቱ ማርየ ወጥ ቤቱ ውስጥ ናት። ዳቦ ከበላችና ቡና ከጠጣች በኋላ ወደ ባቡር ጣቢያው ለመሄድ ተዘጋጅታለች። ሉሲየን ሲመጣ ቀና ብላ አየችውና ፊቷን ወደ ሌላ መለሰች። እርሱ ግን ወደ እርሷ አልተመለከተም። በዝምታ ወጥ ቤቱን አቋርጦ አለፈና የማለዳ ወተት የሚያልቡ እናቱን ለመርዳት ወደ ከብቶች በረት ሄደ።

ወደ በረቱ ሲገባ እናቱ በስጋት ተመለከቱት። እርሱ ግን ምንም አልተናገረም። ምድጃው አጠገብ ተቀምጦ በዝምታ ቁርሱን በሚመገብበት ጊዜም እንዲሁ ዝም እንዳለ ቆየ። መመገቡን እንዳበቃ ብድግ ብሎ ኮቱን ለበሰ፥ ከዚያም ምንም ሳይናገር የእናቱን ግንባር ሳመና ከቤት ወጣ።

በሩ ላይ ቆመው ከእይታቸው እስኪርቅ ድረስ ከተመለከቱት በኋላ ደህና ሁን በሚል አኳኋን እጃቸውን አወዛወዙለት። እርሱም እጁን ካወዛወዘላቸው በኋላ ከእይታቸው በመሰወር መንገዱ መታጠፊያ አቅራቢያ ተደበቀ። እዚያ ሆኖ እናቱ ከነበሩበት እስኪሄዱ ከጠበቀ በኋላ፥ ወደ ኋላ መልስ ብሎ ባለው ፍጥነት ሽቅብ ወደ ተራራው እሮጠ።

ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እስኪል በፍጥነት እየሮጠ ቀዝቃዛና ፀጥ ካለ ጫካ ውስጥ ደረሰ። እዚያ የሚያስፈራው ነገር የለም። ገና ጠዋት ነው። አንድ ዛፍ ሥር ቁጭ ብሎ ያሰላስል ጀመር።

ዛፉና አካባቢው ደስ ይላል። ስፍራው መልካም መዓዛና ፀጥታ ሰፍኖበታል። ሉሲየን መጠነኛ የእፎይታ ስሜት ተሰማው።

ቀኑን ሙሉ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት አላሰበም። ምግብ የለውም፤ ምሳውን የሚበላው ትምህርት ቤት ነበር። ነገር ግን እንግዲህ የተስፈኛነት ስሜት ባለፈው ሌሊት በደንብ ካለመተኛቱ ጋር ተዳምሮ እንቅልፉን ስለ አመጣበት እግሮቹን ዘረጋና ተኛ። እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደው። እኩለ ቀን እስኪሆንና ከተራራው ግርጌ ያሉት ተማሪዎች ለምሳቸው እስኪወጡ ድረስ ተኛ። ሲነቃ እርሱም እንደ ሌሎቹ ልጆች ምሳ መብላት አስፈለገው።



እዛው ጫካ ውስጥ ለምሳ የሚሆን ምንም ምግብ አልነበረም። ብድግ ብሎ በአካባቢው ካሉት ገበሬዎች አንዱ ምናልባት ወተት ይሰጠኝ ይሆናል በሚል ተስፋ ተራራው ላይ ወደ አሉት ጎጆዎች አመራ። በመራመድ ላይ እያለ ከኪሱ ውስጥ ሴንጢ አወጣና መሬት ላይ በተጋደመ አንድ ግንድ ላይ ተቀመጠ። ከዚያም አንድ የእንጨት ስባሪ አንሥቶ በሴንጢው ይፍቀው ጀመር። የተስተካከለ ነገር ባይሠራም ሁልጊዜ እንጨት ይፍቃል። አሁን ግን የሚያደርገው ሌላ ሥራ ስለሌለ በተራራው ከፍታ ስፍራ ከሚኖሩት ድኩላዎች የአንዱን ምስል ለመቅረጽ ወሰነ። እንጨቱን እንደ ዘበት ይፍቅ ጀመር።

የሚፍቀው እንጨት ቀስ በቀስ ቅርጽ ሲያወጣ ስለ ተመለከተ ያልተለመደ ደስታ ተሰማው። ይሰማው የነበረውን ሰቆቃ ለመጀመሪያ ጊዜ ረስቶ በሚሠራው ነገር ተመሰጠ። የሚሠራውን ፍጡር ምስል በአእምሮው ዓይን ይመለከት ጀመር፥ በሚታየው መሠረት ቅርጹን ሠራው።

በመሀሉ ቅርጹን ወደፊት ራቅ አድርጎ ያዘና መረመረው። ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ ባያውቅም፥ የድኩላ ምስል ነበር። የተጠናቀቀ ሥራ ግን አልነበረም። ዳኒ ላይ ካደረሰው አደጋ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ደስታ ተሰማው። ሊሠራ የሚችለው ነገር አገኘ። ደደብ ቢሆንም፥ ቅርጻ ቅርጽ ሊሠራ ይችል ነበር፤ ከእንግዲህ ብቸኛ ቢሆን ግድ የለውም። ሌሎች ልጆች ባያቀርቡት ፀጥ ወዳለው ጫካ መጥቶ ደስ የሚሉ ነገሮችን እየተመለከተ ቅርጻ ቅርጾችን ሊሠራ ይችላል። ሲሠራ ሌሎች ነገሮችን ይረሳል፤ ይህን ነበር ከምንም ይበልጥ የሚፈልገው። ማንኛውም ነገር ሲፈጠር፥ ብቻውን ወደዚያ በመምጣት ሁሉን ነገር ይረሳል።

ብድግ ብሎ ከበላዩ ወደ አለው ከፍታ ስፍራ በመውጣት ከበታቹ ባለው ሸለቆ ውስጥ የሚገኘውን ጫካ ቁልቁል ተመለከተ። ፀሐይዋ ወደ ምዕራቡ ተራራ አቅጣጫ በመጓዝ ላይ ናት። ከተራራው በታች በጣም ዝቅ ብሎ፥ ከትምህርት ቤት የሚወጡ ሕፃናት ሜዳው ላይ ሲራወጡ ጥቃቅን ነገሮች መስለው ይታያሉ። ሩብ ሰዓት ያህል ቆይቶ ሉሲየን ወደ ቤቱ ቢመለስ የሚያስፈራው ነገር የለም።

ጫካ ጫካውን እያደረገ በቀስታ መጓዝ ጀመረ። ሠፈሩ በጣም ቶሎ መድረስ የለበትም። አሁን የፀሐይዋ ብርሃን በሸለቆው ሌላ አቅጣጫ ላይ በመሆኑ፥ የጫካው ውስጥ በመቀዝቀዝና በመጨለም ላይ ነው።

ሉሲየን እጁን ኪሱ ውስጥ በመክተት የሠራውን የድኩላ ቅርጽ ጥብቅ አድርጎ ይዟል። እንደዚያ መያዙ የሚያረካ ስሜት አሳድሮበታል።

እቤቱ ሲደርስ ስለሚሰማው ነገር አሰላሰለ። ዳኒ ሞቶ ይሆናል። ይህን አሳብ ስለሚጠላው ከአእምሮው ሊያስወግደው ፈለገ። ዳኒ መሞት ሳይሆን ምናልባት በጣም ተጎድቶ ይሆናል። ዳኒ መሬት ወድቆ ትንሽ ፊቱ በድንጋጤ ነጭ ሆኖ ሽቅብ ሲመለከት በአሳቡ ታየው።

ላደረሰው በደል ማካካሻ የሚሆን ነገር ቢያስብም፥ ጠብ ያለለት ምንም አልነበረም።

ወደ ቤቱ የገባው እያፈረና እየተሸማቀቀ ነበር። እናቱ በጉጉት ትኩር ብለው ተመለከቱት። ለጥቂት ጊዜ ዝም ካሉ በኋላ፥ «ትምህርት እንዴት ነበር ዛሬ?» ብለው ጠየቁት፥

«ደህና ነበር። ስለጠየቅሽኝ አመሰግናለሁ፥» አለ።

«የዳኒን ቤተሰቦች ላናግራቸው ሄጄ ነበር። አኔትና አባቷ ዳኒን በጋሪ ወደ ሐኪም ቤት ወስደውታል። እስኪመሽ ይቆያሉ። የዳኒ ሴት አያት በትሕትና ነው ያናገሩኝ ሉሲየን። ጥሩ ቤተሰብ ናቸው። ይቅርታ የሚያደርጉልህና የሚገባህን መከራ ከማምጣት የሚቆጠቡ ይመስለኛል።»

ሉሲየን ዝም አለ። የዳኒ ሴት አያት ይቅርታ ያደርጉለት ይሆናል፤ አኔት ይቅር እንደማትለው ግን በሚገባ ያውቃል።

«የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ስለተፈጠረው ሁኔታ ሰምተዋል?» ብለው ጠየቁት እናቱ።

«አዎን።» ሲል መለሰ ሉሲየን።

«ምን አሉ?» ሲሉ ቀጠሉ እናቱ።

«ምንም።» ሲል መለሰ ሉሲየን።

እናቱ ግራ ገባቸው። ልጃቸው ትምህርት ቤት ስለሚገጥመው ሁኔታ እያሰቡ ሲጨነቁ ነበር የዋሉት። ከሉሲየን ሁኔታ እንደሚረዱት ግን ምንም የሆነ አይመስልም። እንዳውም ልጃቸው ከጠዋት ይልቅ ደስተኛ መስሏል።

«ወደ ላሞቹ ሄጄ ወተት አልባለሁ እማዬ፥» አለ ሉሲየን በእፎይታ ስሜት ወደ ከብቶች በረት እየሄደ። በረቱ ከእናቱ ጥያቄዎች መሸሺያና መሸሸጊያ ስፍራ ነበር። ላሞቹም ስለ እርሱ ክፉ ነገር የሚያስቡ ፍጡሮች አልነበሩም። ወተቱን ቶሎ ቶሎ አልቦ እዚያው እንዳለ የሚበቃውን ያህል ጠጣና ረሀቡ መለስ አለለት። ቁርሱን ከበላ ወዲህ ምንም አልቀመሰም ነበር።



ዛሬ ማታ ከእራቱ ትንሽ አስተርፎ በመያዝ ዛሬ ወደ ዋለበት ጫካ ነገም ሄዶ በመደበቅ ቀኑን በፀጥታ ሊያሳልፍ አሰበ። ድርጊቱ እስኪታወቅበት ድረስ ይህን በየዕለቱ ያደርገዋል። ምናልባት ብዙም ሳይቆይ ይታወቅበት ይሆናል።

የቻለውን ያህል ካለበ በኋላ ወተቱን ይዞ ወደ ቤት ተመለሰ። እቤቱ በር ላይ ሲደርስ ከታላቅ እኅቱ ጋር ተገናኙ። በጣም ስለ ተናደደች ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ ይላል።

«አንተ መጥፎ ልጅ!» ብላ ጮኸች እንዳየችው። «ከትምህርት ቤት ቀረህ! ምን ሲሠራ ነው የዋለው እማማ? ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄድ ማድረግ ነበረብሽ!»

እናቷ በንዴት ዘወር ብለው፥ «ምንድን ነው የምትይው ማሪዬ? ወደ ትምህርት ቤት ሄዷል። አሁን ገና ነው የተመለሰው። አትጨቅጭቂው፤ ወደ ሥራሽ ሂጂ» አሏት።

«እውነትሽን ነው! የመጣው አሁን ከሆነ፥ ከየት እንደ መጣ ለማወቅ እፈልጋለሁ። ከባቡር ጣቢያ ስመጣ የትምህርት ቤቱን ዳሬክተር አናግሬአቸዋለሁ። አትክልታቸውን ይኮተኩቱ ነበር። ሳልፍ አይተው ነው የጠሩኝ። ‹ሉስዬን ለምን ቀረ? ለምንድን ነው ወደ ትምህርት ቤት ያልመጣው? አሞታል እንዴ?› ብለው ጠየቁኝ። ‹ደህና ነው፥ አልታመመም፤ ነገ ይመጣል። ኅትቼም ቢሆን አመጣዋለሁ› ብዬ መለስኩላቸው። እንግዲህ ሉሲየን ዛሬ የዋልክበትን እግዚአብሔር ያውቃል። ነገ ግን እኔ እራሴ ነኝ ወደ ትምህርት ቤት የምወስድህ» አለች እኅቱ ቁጣ በተሞላበት ንግግር።

«ውሸት መናገርህ በጣም ይገርማል ሉሲየን» አሉ እናቱ በኀዘን፥ «መጥፎ ልጅ ነህ። ምን እንደማደርግህ አላውቅም። የትምህርት ቤትህ ዳሬክተር የፈለጉትን ያድርጉህ»። በጣም ከመጨነቃቸውም በላይ ልጃቸው ስለ ዋሻቸውና ስለ ተናደዱ፥ ፊታቸውን በአንገት ልብሳቸው ሸፍነው ያለቅሱ ጀመር።

ሉሲየን በቁጣና በኩርፊያ ስሜት ፀጥ ብሎ ምድጃው አጠገብ ተቀመጠ። ሰው ሁሉና ማንኛውም ነገር ጠላት የሆነበት መሰለው። የመደበቂያ ተስፋውም ተወሰደበት። ነገ ወደ ትምህርት ቤት ሊሄድ ነው፤ አኔትን እዚያ ያገኛታል። ዛሬ ቢሄድ ኖሮ ወንድሟን ይዛ ወደ ሐኪም ቤት ስለሄደች አያገኛትም ነበር።

አንድ ትልቅ የእንጨት ቁራጭ አንሥቶ በሴንጢው ይፍቀው ጀመር። እጁን ወደ ኪሱ ከቶም ቀደም ሲል የሠራውን የድኩላ ቅርጽ ዳሰሰው።

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ወደ ሆስፒታል ጉዞ



ዳኒ ከሣር በተሠራ ምንጣፍ ላይ ጋደም ብሎ በጋሪ በመጓዝ ላይ ነው። ዓይኖቹ ጥጥ የመሰሉ ደመናዎች የሚንሳፈፉበትን ሰማይ ይመለከታሉ። ዙሪያ ገባውንም ቢመለከት ይወድ ነበር። ቁጭ ለማለት ባለመቻሉ አልሆነለትም። በመሆኑም እርሱ ሰማዩን ሲመለከት፥ አኔት ጎኑ ቁጭ ብላ በአካባቢው ስለሚታዩና ስለሚከናወኑ ነገሮች ትነግረዋለች። የእግሩ ሕመም በጣም ስለሚሰማው ዳኒ ቁጡ ሆኗል። ጋሪው በተንገጫገጨ ቁጥር ሕመሙ እየተሰማው ይጮሃል። ያኔ አኔት «አይዞህ» እያለች በቀስታ ንግግር ታበረታታዋለች። የሚያበረታታ አፍቃሪ ማግኘት መልካም ነው።

«አሁን ወደ መንደሩ ተቃርበናል፥ ዳኒ። በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ በማለፍ ላይ ነን። ኤሚል የተባለው የጽዳት ሠራተኛ ልጅ ላሞችን ከቤተ ክርስቲያኑ በማስወጣት ላይ ነው። አንድ መጥፎ ሰው የቤተ ክርስቲያኑን አጥር በር ክፍት ስላደረገው ይሆናል ከብቶቹ የገቡት» አለች አኔት።

«ላሞቹ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ግቢ ለመግባት በመሞከር ላይ ናቸው?» አለና ጠየቀ ዳኒ።

«አይደለም። በጣም ረዘመባቸው እንጂ በአጥሩ ላይ ለመዝለል ነበር የሞከሩት። ያ አልሆንላቸው ሲል በመቃብሮች ላይ ለመዝለል ሞከሩ።



አሁን ደግሞ መዋዕለ ሕፃናቱ አጠገብ ደረስን፤ መምህርቲቱ የትምህርት ቤቱን ደረጃዎች በመጠራረግ ላይ ናት። ዛሬ የጽዳት ቀን ስለሆነ ሕፃናቱ ሁሉ ቤታቸው እንዲውሉ ፍቃድ የሰጠቻቸው ይመስለኛል። የትምህርት ቤታችን ዲሬክተርም የጽዳት ቀን እረፍት ቢሰጠን እንዴት ጥሩ ነበር። አሀ! መምህርቲቱ ወደ እኛ መጣች። አይታናለች፤ ስለ አንተ ጤና ልትጠይቀን ያሰበች ይመስለኛል። ሌሎች ሁለት የሚያውቁን ሴቶችም ወደ እኛ መጡ። ውኃው ምንጭ አጠገብ ልብሳቸውን ያጥቡ ነበር» አለች አኔት።

እውነቷን ነበር አኔት። ስለ ዳኒ ጉዳትና ጤንነት ለማወቅ ነበር ሰዎቹ የፈለጉት። ትንሽ መንደር ውስጥ አንዱን ወሬ ሰዎች ሁሉ ቶሎ ይሰሙታል። በዳኒ ላይ የደረሰው ዓይነት አደጋ ብዙ ጊዜ ስለማይደርስ ዜናው ይወራል፤ ለብዙ ጊዜም አይረሳም። የፖስታ ቤቱ ሠራተኛ ሚስት ዳኒ ላይ ስለ ደረሰው አደጋ የሰሙት የሉሲየን ታላቅ እኅት ለመንደሬቱ ሐኪም በምትደውልበት ጊዜ ነበር። ለባቡር ጣቢያው ኃላፊ ሚስትም ይህቺው የሉሲየን እኅት ናት የማለዳውን ባቡር በምትጠብቅበት ጊዜ ያወራችላቸው።

በአሁኑ ጊዜ ሰው ሁሉ ዳኒ ላይ ስለ ደረሰው አደጋ ነው የሚያወራው፤ ሁሉም ስለ አደጋው ይበልጥ ለማወቅ ይፈልጋል። ልብስ ያጥቡ የነበሩት ማዳም ፒሌትና ማዳም ሊኖይር የባሎቻቸውን ሸሚዝ ውኃው ውስጥ ትተው፥ ማዳም ዱሬዛ ደግሞ መደብራቸውን ክፍቱን በመተው ሁለት ደንበኞቻቸውን አስከትለው እየሮጡ ነው የመጡት። መምህርቷም ማጽዳቷን ትታ ነው የመጣችው። ሁሉም በሩጫ መጥተው ዳኒን ለማየት ይንጠራሩ ጀመር። ከሣር በተሠራ ምንጣፍ ላይ በጀርባው ተንጋሏል። ፊቱ ከመገርጣቱ በስተቀር ኀዘን አይታይበትም። ሰዎቹን በመመልከቱም ደስ ብሎታል።

«ውይ፥ ትንሹ ድንቡሼ» አለች መምህርቲቱ ዳኒን እያየች። ከዚያም ወደ አኔት ዘወር በማለት፥ «እስቲ ንገሪን አኔት፤ ምንድን ነው የሆነው?» አለች። ሴቶቹ ታሪኩን የሰሙና ለሌሎች እየደጋገሙ የነገሩ ቢሆኑም፥ እንደገና ለመስማት ሁሉም በጉጉት ጠብቁ። አኔትም የሆነውን ሁሉ ነገረቻቸው። ከንፈሮቻቸውን እየመጠጡና ራሶቻቸውን እያወዛወዙ አዳመጧት። ሁሉም በሉሲየን ድርጊት ተቆጡ።

«መጥፎ ልጅ ነው! ሕፃናቶች እንዳይጠጉት አስጠነቅቃቸዋለሁ» አለች የመዋዕለ ሕፃናቱ መምህርት።

«ልጄ ከእርሱ ጋር እንዲጫወት አልፈቅድለትም! ጨካኝ መሆኑ ከፊቱ ያስታውቃል። እንዲህ ያለ ክፉ ልጅ ለወለደች እናቱ አዝንላታለሁ» አሉ የፖስታ ቤቱ ኃላፊ ሚስት። ስለ ደስተኛውና ፊቱ ጠቃጠቆ ስለሆነው ልጃቸው ለአንድ አፍታ አሰቡ። በመንደሪቱ ነዋሪዎች በጣም ከሚወደዱት ልጆች አንዱ ነው።

የዳኒ አባት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ዶክተሩ ስለሚጠብቃቸው ቶሎ ይሄዱ ዘንድ ሰዎቹ መንገዱን እንዲለቁላቸው ጠየቋቸው። በዚሁ መሠረት ሴቶቹ ገለል ሲሉላቸው ጋሪውን እየነዱ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ሴቶቹ ደግሞ መንገዱ መሀል ስብስብ ብለውና በጣም ተቀራርበው ያወሩ ጀመር።

ጋሪው በቀስታ ይጓዛል፣ ማለዳው አልፎ ረፈደ። ጋሪውን የሚስበው ፈረስ ፍጥነቱን አልጨመረም። በመሆኑም አኔት በአካባቢው ስለምታየው ነገር ለዳኒ የመግለጫ በቂ ጊዜ አላት።

«ወንዙ ሞልቷል ዳኒ። ይህ የሆነበት ምክንያት በረዶውን የሚያሟሟ መልካም አየር በመኖሩ ነው። ውኃው በዛፎቹ ሥር ላይ ነው የሚፈስሰው። እዚህ ደግሞ አንድ ዛፍ ወንዙ ላይ ወድቆ እንደ ድልድይ ሆኗል። ውይ ዳኒ! አንዲት ነጣ ያለች ሽኮኮ ድልድዩ ላይ ቆማለች። ልሻገርበት ወይስ ይቅርብኝ እያለች የምታስብ ትመስላለች።»

«የታለች?» አለ ዳኒ የጤንነቱን ሁኔታ ረስቶ ቁጭ ለማለት እየሞከረ። አልቻለም! በሕመም ሲቃ አቃሰተና ወደ ነበረበት ተመለሰ።

«ልታያት አትችልም። እንዳውም ወደ ጫካው ሮጠች። አሁን ወደ ባቡር ጣቢያው በመቃረብ ላይ ነን። ባቡሩ ላይ ለመጫን የሚጠባበቁ ሦስት ላሞች ይታዩኛል» አለች አኔት።

ጉዞው ደስ በሚል ሁኔታ ተጠናቀቀ። ቤቶች ይታዩ ጀመር። ወደሚሄዱበት ከተማ በመቃረብ ላይ መሆናቸውን አኔት ለዳኒ ነገረችው።

«ስለ መደብሮቹ ንገሪኝ» አለ ዳኒ በጉጉት።

ወደዚያች ከተማ የመጣው ለሦስት ጊዜ ብቻ ነበር። በዓለም ላይ ካሉት ቦታዎች ሁሉ ይበልጥ ያምራል በማለት አስቧል።

እውነቱን ለመናገር ስፍራውን ከተማ የሚያሰኙት ብዙ ነገሮች አልነበሩም። መደዳ ሱቆች ያሉት አንድ ጠባብ መንገድ ብቻ ነበር



ያለው። ቢሆንም ሱቆቹ በጣም ያምራሉ። ኬክና ልዩ ልዩ የፍራፍሬ ጭማቂ የሚሸጥበት ቤት አለ። ጌጠኛ የአገር ልብሶች የሚሸጡበት መደብርም አለ። ከሁሉም የሚያምረው ግን ከእንጨት የተሠሩ ቅርጻ ቅርጾች የሚሸጡበት መደብር ነበር። የወፍ ቅርጽ ያለበት ሰዓትና አፋቸውን በሰፊው ከፍተው ፍራፍሬ የሚበሉ ከእንጨት የተቀረጹ የሽማግሌዎች ምስል ተደርድረውባቸዋል። እነ አኔት መደብሮቹን እየተመለከቱ ሆስፒታሉ ፊት ለፊት ደረሱ።

ትንሽ ሆስፒታል ቢሆንም፣ ለአኔትና ለዳኒ ግዙፍ ሆኖ ታያቸው። በሽተኞቹ ሁሉ ደረጃዎች ላይ ተቀምጠው ፀሐይ ይሞቃሉ። የሆስፒታሉ በር በሰፊው ተከፍቷል። የዳኒ አባት ከጋሪው ላይ ወርደው የፈረሱን ልጓም አጥሩ ላይ በማሠር ወደ ውስጥ ገቡ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ የበሽተኛ መሸከሚያ ቃሬዛ ከያዙ ሁለት ሰዎች ጋር ተመለሱ።

ሆስፒታሉ ውስጥ ከገቡ በኋላ ዳኒ ተመላላሽ ታካሚዎች ክፍል ከቃሬዛው ላይ እንዳለ አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ተኛ። አባቱ ከራስጌው፣ አኔት ደግሞ ከግርጌው ተቀመጡ። የቦታው ፀጥ ማለትና ለየት ያለ ሽታው ሁሉንም ዝም አሰኛቸው። ዳኒ ነርሶቹን ትኩር ብሎ ያያቸዋል። ረጃጅም ነጭ ልብሶች ለብሰው ያንኑ የመሰሉ የራስ ቆቦች አድርገዋል። ነርሶቹ ሴት አያቱ ሥዕላዊ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያያቸውን መላእክት ይመስላሉ ብሎ አሰበ።

በነበሩበት ሆነው ለብዙ ጊዜ ጠበቁ። አኔትና አባቷ እንቅልፍ ደፋ ቀና ያደርጋቸው ጀመር። ዳኒ ደግሞ እጆቹን በራሱ ላይ እንዳደረገ ጥልቅ እንቅልፍ ወሰደው።

ዳኒ ከእንቅልፉ የነቃው ድንገት በመጡትና የሚቸኩሉ በሚመስሉት በሐኪሙ ተቀስቅሶ ነው። እርሳቸው ሽማግሌ ሲሆኑ፣ ትልቅ ጥቁር ፂምና ጎርናና ድምፅ ያላቸው ናቸው። አኔት ፈርታቸዋለች።

ከዚያ በኋላ በነበረው ጊዜ ግን ሁሉም ነገር በፍጥነት የሚከናወን መሰለ። ዳኒ የእግሮቹ አጥንቶች ራጅ ይነሡለት ዘንድ በባለ ጎማ የሆስፒታል አልጋ ተወሰደ። በአልጋው መጓዙ ዳኒን አስደሰተው። የአጥንቱን ፎቶ ግራፍ ወደፊት እቤቱ ግድግዳ ላይ ለመስቀል ይፈቀድለት እንደሆነ ለማወቅ ፈለገ። ከተወሰደበት እንደ ተመለሰ ዶክተሩ የዳኒን በሽተኛ እግር ያዙና ሳቡት። ከሕመሙ ሥቃይ የተነሣ

ዳኒ በጣም ጮኸ። ትንሽ ቆይቶ የእግሩ ፎቶ ግራፍ መጣ። ምንም የዳኒን እግር አይመስልም።

ዶክተሩ ግን ፎቶ ግራፎቹን ተመልክተው የደስታ ምልክት አሳዩ። ፎቶግራፎቹን በትኩረት እየመረመሩ ራሳቸውን ሲነቀንቁ ቆዩና ወደ ዳኒ አባት ዘወር ብለው፥

«ልጁ ሆስፒታል ውስጥ መቆየት አለበት። እግሩ ከባድ ስብራት ደርሶበታል» አሉ።

የዳኒ አባት ግን የዶክተሩን አሳብ አልተቀበሉም። ትንሽ ልጃቸውን ጥቁር ጺምና ጠንካራ እጆች ላሏቸው ሰውዬ ሰጥተው ለመመለስ አልፈለጉም።

«ቤት እናስታምመዋለን። ያን ማድረግ አያቅተንም» አሉ ጠንከር ባለ አነጋገር።

ዶክተሩ በምንቸገረኝ አኳኋን ትከሻቸውን ወደ ላይና ወደ ታች ነቅንቀው፥ «ይቻላል! እኔ ግን እዚህ ቢቆይ ይሻለዋል እላለሁ። ወደ ቤታችሁ ልመጣ ግን አልችልም፥ እንዲያ ከሆነ ወዲህ ልታመላልሱት ነው» አሉ።

«ግድ የለም፥ እኔ አመላልሰዋለሁ» አሉ የዳኒ አባት በአሳብ ግትርነት። እኔት በትንሽ እጁ እጃቸውን ያዝ አደረገችው! እርሷም ዳኒ ቤት እንዲሆን ፈልጋለች።

ዶክተሩ እንደገና ትከሻቸውን ነቅንቀው እንደ ፈለጋችሁ በሚል አኳኋን እጆቻቸውን ግራና ቀኝ ዘረጓቸው። ዳኒ በአንዲት ነርስ አማካይነት እንደገና ወደ ሆስፒታሉ ውስጠኛ ክፍል ተወስዶ ከግማሽ ሰዓት በላይ እዚያው ቆየ።

በመጨረሻ ሐኪሞቹ ሲያመጡት፥ እንቅልፍ የወሰደውና ሁኔታው የተለዋወጠ መስሏል። ለየት ያለ የሆስፒታል ጠረን አለው። ምንም አያስታውስም። ከወገቡ በታች እግሩ በነጭ ፋሻ መጠቅለሉን በቅድሚያ ያየችው እኔት ናት። ለራሱ ለዳኒ በጣቷ አመለከተችው። ጎንበስ ብሎ የገዛ እግሩን በመደነቅ ተመለከተው።

«ለምንድን ነው ይህን ነጭና ወፍራም ሱሪ ያለበሱኝ?» አለ። መልስ ሳይጠብቅ ቀጠል አደረገና የዶክተሩን ትልቅና ጥቁር ጺም ስለማይወደው ወደ ቤቱ እንዲወስዱት ጠየቀ።



እኔትም የዶክተሩን ጺም አልወደደችውም! ሁሉም ወደ ቤታቸው መመለስን መረጡ! እኔት ስለ ራባት፥ ዳኒ ስለ ደከመው፥ አባታቸው ደግሞ ስለ ላሞቻቸው በማሰባቸው። ዶክተሩ ለሁለተኛ ጊዜ የተነሣውን የዳኒ እግር ራጅ ወይም ፎቶ ግራፍ ይዘው ሲመጡ ሦስቱም በስፍራው አልነበሩም። አንድ ፈረስ ሦስት ሰዎች ያሉበትን ጋሪ እየሳበ በፍጥነት ሲራመድ በሩቁ ይታያል። እነ እኔት ነበሩ። ዳኒን ወደ ሆስፒታሉ መቼ መመለስ እንደሚገባቸው ወይም እግሩ ላይ የታሠረው ፋሻ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበት መጠየቅ የሚገባቸው መሆኑን ዘንግተው ነበር።

ከቀኑ በአሥራ አንድ ሰዓት ቤታቸው ደረሱ። ብቸኝነት እንዳይሰማው በማሰብ ዳኒን ሳሎን ውስጥ ሰፋ ወንበር ላይ ነው ያስተኙት። ሌሊት ነቅቶ ቢፈልግ በቅርብ እንዲያገኛት እኔትም አቅራቢያው ምንጣፍ ላይ ተኛች። በሽተኛ እግሩን ትራስ ላይ እንዳደረገ ለሳምንታት እዚያው ተኛ። የሚያስፈልገው ነገር ሁሉ እዚያው ተዘጋጅቶለት ነበር።

እኔት ለጊዜውም ቢሆን ትምህርቷን አቋርጣ የዳኒ አገልጋይ ሆነች። የምታውቃቸውን ተረቶች ሁሉ ትነግረውና ልዩ ልዩ ጫወታዎችንም ታጫውተው ነበር! ሴት አያታቸው ደግሞ ለመብላት የሚያጓጓ ምግብ እየሠሩ ያቀርቡለታል። ዳኒ እንደ በሽተኛ ልዩ ምግብ እንዲቀርብለት አልፈለገም። የሚቀርብለትን ምግብ ሁሉ ይመገባል! ደስተኛና ተጫዋችም ነበር። እኔት ሥራ በዝቶባት ብትርቀው በረንዳው ላይ በጀርባው ይጋደምና በደስታ ይዘምራል።

ደስ የሚያሰኙ ነገሮች ሁሉ ነበሩት። የመንደሪቱ ሰዎችም የሚቻላቸውን ሁሉ ያደርጉለት ነበር። እናቱ መንደሪቱ ውስጥ ያደገችና ሰዎች ሁሉ የሚወዱት ሴት ነበረች። በመሆኗም በሞተች ጊዜ ልጆቿን ሊወዷቸውና ሊንከባከቧቸው ተዘጋጁ። በተለይም ተለማማጭ ሰማያዊ ዓይኖች፥ እንደ ዘማሪ ወፍ ደስ የሚል ድምፅ ያለውን ዳኒን ወደዱት! አንድ የአምስት ዓመት ሕፃን የሚያስፈልገውን እንክብካቤም አልነፈጉትም።

ሁልጊዜ ፍቅር የሚለገሰው ዳኒ ደስተኛ ሆነ። በሚጠይቁት ሰዎችና በሚመጡለት ቆንጆ ቆንጆ ስጦታዎች ተደነቀ።

የመንደሪቱ ልጆች ወደ ተራራዎች እየወጡ የሚያምሩ አበባዎችን ያመጡለታል። ከአበባዎች ብዛት የተነሣ አልጋው አጠገብ የነበረ አንድ ጠረጴዛ አበቦች የሚበዙበት የአትክልት ስፍራ መሰለ። ዳኒ አበቦቹን እንደ ወደዳቸው የተመለከቱት ሴት አያቱ ጠያቂዎቹ ልጆች የሚፈጥሩትን ጫጫታና ትርምስ ታገሡ። በቦት ጫማቸው በሚያመጡት ጭቃ በረንዳውን ቢያጨመላልቁትም አልተቆጡም።


የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር የሥዕል መጽሐፍ በስጦታ ላኩለት። የሻይ ቤቱ ባለቤት ጠቃጠቆ ያለባቸውና ቡናማ የሆኑ እንቁላሎችን፥ ዳቦ ጋጋሪው ደግሞ በልዩ ልዩ ቅርጽ የተጋገሩ ዳቦዎችን ይልኩለታል። በተለይ ዳቦ ጋጋሪው አኔትን ባገኛት ቁጥር ሳቅ እያለ ቅርጫቷ ውስጥ ዳቦ በነፃ ይከትላት ነበር። ለዚህ ነበር ዳኒ አኔት ወደ መደብር ሄዳ በምትመለስበት ጊዜ ሁሉ የዕቃ መያዣ ሳጠራዋን ተሽቀዳድሞ መክፈት የሚወደው። ያን ሲያደርግ ሳጠራው ውስጥ የሚያገኘው ነገር ሁሉ ከሰዎች ለእርሱ የተላከ ስጦታ ይመስለው ነበር።

ፖስታ አመላላሹ ሰውዬ የሚያመጣው ስጦታ ግን ለየት ያለና ከሁሉ የሚበልጥ ነበር። የአኔት ቤተሰቦች ደብዳቤ የሚመጣላቸው ሰዎች አልነበሩም። ስለዚህ እርሱ ራሱ በባለ ሥዕል ካርዶች ላይ እየጻፈ ለዳኒ ያመጣለት ጀመር። የሚመጣው በተለያዩ ቀኖች ስለሆነ፥ ዳኒ ሁል ቀን በጉጉት ይጠብቀዋል።

ፖስተኛው ሲመጣ አይጣደፍም። ከረጢቱ ውስጥ ያሉ ደብዳቤዎችና ካርዶችን እያወጣ ለዳኒ የተላከለትን ለማግኘት በቀስታ ይመርጣል። ያን ጊዜ ዳኒ ደብዳቤውን ለመቀበል በጉጉት ሲቁነጠነጥ መመልከቱ ፖስተኛውን ያስደስተዋል። ለዳኒ ሲል ፖስተኛው በሚያደርገው ነገር ፖስታቸው የተሻሸባቸው ሰዎች ቢኖሩ እንኳን አይከፋቸውም።



## ምዕራፍ አሥር
## ሉሲየን ጓደኛ አገኘ



የመንደሪቱ ሰዎች ባላቸው አቅም ሁሉ ዳኒን ሲንከባከቡት፥ ሉሲየንን ግን አራቁት። በጣም የናቁት መሆናቸውንም በተለያዩ መንገዶች ይገልጡ ነበር።

በመንደሪቱ ሰዎች ሁኔታ ለጥቂት ቀናት ተሠቃየ። የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ሉሲየን መጥፎና የማይረባ ልጅ መሆኑን እየገለጠ ትምህርት ቤቱ ውስጥ ንግግር አደረገ። ልጆች በመጀመሪያ ጭቃ እየወረወሩ ከጫወታ ሜዳቸው አባረሩት። በኋላ ደግሞ ያን ተዉና አኮረፉት። ትምህርት ቤቱ ውስጥ አንድ ቡድን በተመረጠ ቁጥር እርሱ የመጨረሻው ልጅ ይሆናል። ክፍል ውስጥ ልጆች ሁለት ሁለት እየሆኑ ሲቀመጡ እርሱ ብቻውን ይቀመጣል።

ትንንሽ ሕፃናት እንኳን ወላጆቻቸው ስለ ሉሲየን መጥፎነት ስለ ነገሯቸውና ከእርሱ ጋር እንዳይገጥሙ ስለ አስጠነቀቋቸው አይጠጉትም። «መጥፎና ጨካኝ ልጅ ነው፤ ዳኒን እንዳደረገው እናንተንም ይጎዳችኋል» እያሉ ነበር የሚነግሯቸው። ለዚህ ነበር ትንንሽ ልጆች እንደ አውሬ የሚያዩትና ሲቀርባቸው በሩጫ የሚሹሹት።

ወደ መንደሪቱ መደብሮች ሲሄድ ዕቃ ሻጮቹ የሚፈልገውን ይሰጡታል እንጂ ምንም አያናግሩትም። ወተት ሻጩ ከእርሱ ጋር ቃል አይለዋወጥም፤ የምግብ መደብሩ ባለቤት ሚስት ሉሲየን ዕቃ

በሚገዛበት ጊዜ ለሌሎች እንደምታደርገው በእጁ አትሰጠውም። ክፉ ነገር አይናገሩትም፤ ብቻ እንደማያውቁት ሰው ዝም ይሉታል።

ሉሲየን ሰዎች እንዲወዱት ለማድረግ የሚያስችሉ ነገሮችን ለማከናወን ድፍረት ስለ አጣ ወደ ራሱ የብቸኝነት ዓለም ገባ። ወደ ትምህርት ቤት የሚሄደውና የሚመጣው ብቻውን፥ ወደ መደብር ሲሄድ ብቻውን፥ ሲጫወት ብቻውን ነው። ልጆች ስለ አላቀረቡት አይደለም። ምክንያቱም እነርሱ ቶሎ ይቅርታ የሚያደርጉና በደልን የሚረሱ ፍጡራን ናቸው። የራሱ የሀፍረት ስሜት ነው እንዲርቃቸው ያደረገው። በልጆቹ ፊት ላይ ሁልጊዜ የሚታየው ጥላቻቸው ነው። የሚያስቡት ሁሉ ስለ ዳኒ ስለሚመስለው ከባለ ወተቱ ሰውዬ ጀምሮ ትምህርት ቤት እስከ አሉት ሕፃናት ሁሉን ይፈራቸው ጀመር።

ሉሲየን ራሱም ቢሆን ሁልጊዜ ስለ ዳኒ ያስባል። አሳቡ አእምሮውን ስለ አስጨነቀው ሐኪሙ ያለውን ነገር ከአኔት ለመጠየቅ ይመኛል። ነገር ግን ከአደጋው ዕለት ወዲህ አኔት ልታየውም ሆነ ልታናግረው ስለማትፈልግ ፈራት።

እቤት ውስጥ እናቱ እስኪገርማቸው ድረስ ዝምተኛ፥ ግን ደግሞ በጣም ሠራተኛ ልጅ ሆነ። ብቸኛነቱን የሚረሣው ጊዜውን በሥራ ሲያሳልፍ መሆኑን ስለተረዳ ነው ያለ እረፍት የሚሠራው። ቀድሞ ሰነፍ ነበር፤ አሁን ግን በእርሻ ቦታ እንኳን በጣም የሚሠራ ልጅ ሆኗል። እናቱ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያመሰግኑት ጀመር፤ እኅቱም አቀረበችው። እርሷ ኅበዝ ሠራተኛ በመሆኗ ለቀድሞው የሉሲየን ስንፍና በጣም ያናድዳት ነበር።

ለሉሲየን የተስማማውና ደስተኛ የሚሆንበት ስፍራ ግን አንድ ብቻ ነበር፥ ያውም ጫካ ውስጥ። እዚያ ደጋጎቹ ዛፎች ይሸሽጉታል። የሚጠላው ዓለም ደግሞ ወደዚያ አይመጣም። ሉሲየን ትርፍ ጊዜ ሲኖረው የሚሸሽበት ስፍራ ያ ነው። አንድ ግንድ ወይም ቋጥኝ ላይ ደገፍ ብሎ ከእንጨት ቁርጥራጭ በሰንጢው ትንንሽ ቅርጻ ቅርጾችን እየሠራ ከዚያ በሚያገኘው ደስታ ሌላውን ነገር ሁሉ ይረሳል። ዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጦ ሲሠራ የበጋው የጫካ ውስጥ ሰላምና ውበት ያጽናናዋል፥ ይመቸዋል።

ተራራው ከፍታ ላይ፥ ጫካው ዳር አንድ ሽማግሌ ብቻቸውን የሚኖሩባት አንድ ትንሽ ጎጆ አለች። ሰውየው ወደዚያ የሄዱት ከብዙ ጊዜ በፊት ሲሆን፥ ከአንዱ ፍየላቸው፥ ከዶሮዎቻቸውና ከድመታቸው ጋር ይኖራሉ። ለየት ያለ ባሕርይ ያላቸው ሽማግሌ ስለሆኑ የመንደሪቱ ሰዎች ይፈሯቸዋል። የሚፈልጉትን ነገር ለመግዛት ወደ መንደሪቱ የሚመጡት አልፎ አልፎ ነው። ሲመጡ ልጆች ይሸሿቸዋል።



«የተራራው ላይ ሽማግሌ» እያሉ ነው የሚጠሯቸው። አንዳንዶች ንፉግ ሐብታም ናቸው ሲሏቸው፥ ሌሎቹ ከፖሊሶች የተደበቁ ናቸው፥ የቀሩት ደግሞ እብድና መጥፎ ሰው ናቸው ይሏቸዋል። እውነተኛው ምክንያት ምንም ይሁን ምን እቤታቸው የገባ ወይም ከመሸ በኋላ በቤታቸው አቅራቢያ ያለፈ ሰው አልነበረም።

አንድ ጊዜ፥ ለግማሽ ቀን ትምህርት ባልነበረ ዕለት፥ ሉሲየን ከዚያ ቀደም ባልተለመደ ሁኔታ ራቅ ብሎ ወደ ተራራው በመውጣት ቁጭ ብሎ የእንጨት ቅርጻ ቅርጾችን ይሠራ ጀመር። በጥፍሮቿ መካከል የዛፍ ፍሬ የያዘች ሽኮኮ ቅርጽ በመሥራት ላይ እንደነበረ ነው ኃይለኛ የሰው አተነፋፈስ ከኋላው የሰማው። መለስ ቢል የተራራው ሽማግሌ ከጀርባው ቆመው ይመለከቱታል።

የሰውየው ሁኔታ ያስፈራል። ችፍግ ያለው ጥቁርና ነጭ ፂማቸው እስከ ደረታቸው አድጓል። ወደ ላይ የተቀለበሰው አፍንጫቸው ክፉና አዳኝ አሞራ አስመስሏቸዋል። ሉሲየን ቀና እንዳለ ሰውዬውን በፍርሃት ትኩር ብሉ አያቸው። የሰውየው ዓይኖች ብሩህ፥ ደግነት የሚገለጥባቸውና በትኩረት የሚመለከቱ መሆናቸውን ሉሲየን ተገነዘበ። በመሆኑም ላለመሸሽ ወሰነ። ብቸኝነቱም ከቀድሞው ይልቅ ደፋር አደረገው። ሽማግሌው ሰው የማይጠጋቸውና ክፉ ይሆኑ ይሆናል። ቢሆንም ሉሲየን ስለ አደረጉት ነገር ምንም አያውቅም።

«ጤና ይስጥልኝ፥» አለ ሉሲየን እንደ ምንም እራሱን እያደፋፈረ። ይህን ብሎ የሚሆነውን ነገር በትዕግሥት ይጠብቅ ጀመር።

ሽማግሌው ቡናማ ጥፍር የሚመስል እጃቸውን ዘረጉና ሉሲየን የሠራውን ትንሽ ቅርጽ ከመሬት አነሡ። በተደጋጋሚ እያገለባበጡ ከመረመሩት በኋላ፥ «በዚህ ዕድሜህ ጥሩ ቅርጻ ቅርጽ ሠራተኛ ነህ። ማን ነው አስተማሪህ?» አሉ።

«አስተማሪ የለኝም፤ እራሴን በራሴ ነው ያስተማርኩት።»

«ስለዚህ አንተ እራስህ ጥሩ መምህር ነህ። ተገቢ የመቅረጫ መሣሪያዎች ሊኖርህ ይገባል። ትንሽ ሥልጠና ቢሰጥህ እራስህን ማስተዳደሪያ ገቢ ልታገኝ ትችላለህ። ይህች ሽኮኮ ሕይወት ያላት ነው የምትመስለው።»

«የቅርጻ ቅርጽ መሥሪያ ዕቃ የለኝም፤ የምገዛበት ገንዘብም የለኝም።»

ሽማግሌው በእጃቸው ተከተለኝ የሚል ምልክት አሳዩት። በህልም ዓለም እንደሚንቀሳቀስ ሰው ብድግ ብሎ ወደ ጭጋጋማው ጫካ

ተከተላቸው። ምንም ሳይነጋገሩ ጥቂት እንደ ተጓዙ የሽማግሌው ትንሽ ጎጆ አቅራቢያ ደረሱ።

ዶሮዎቹ ከሚሠፍሩበት ቆጥና ፍየሉ ከሽማግሌው ጋር ከሚጋራው ወጥ ቤት በቀር ሽንት ቤት በጎጆው አቅራቢያ የለም። ፀሐይ እየሞቀች በምራቋ በመታጠብ ላይ ያለችው ድመትም ከፍየሉና ከሽማግሌው ጋር ነው የምትኖረው። መኝታቸው ሣር የተጎዘጎዘበት ቆጥ ነው። ሽማግሌው የሚተኙት ለፍየሉ የክረምት ምግብነት በተዘጋጀው ድርቆሽ ሣር ላይ ጆንያ አንጥፈው ነው።

የወጥ ቤቱ እንዲሁም የሳሎኑ ዕቃዎች መናኛና የተመሰቃቀሉ ናቸው። አንድ ምድጃ፥ ወተት ማለቢያ ባልዲ፥ ከእንጨት ጉማጅ የተዘጋጀ አንድ መቀመጫ፥ አንድ ጠረጴዛ፥ አንድ ወንበርና የአይብ መሥሪያ ናቸው ቤቱ ውስጥ ያሉት። ፍየሉ በማይደርስበት እርቀት ከፍ ብሎ ዙሪያውን ግድግዳው ላይ የተሠራ መደርደሪያ አለ። መደርደሪያው ከእንጨት በተሠሩ ቅርጻ ቅርጾች ተሞልቷል። ቅርጻ ቅርጾቹ ግማሾቹ የሚያምሩ፥ ከፊሎቹ ደስ የማይሉ ቢሆኑም፥ በእውነተኛ ቀራጭ የተሠሩ ናቸው።

በቅርጻ ቅርጾቹ መሀል ድቦች፥ ላሞች፥ ድኩላዎችና ፍየሎች፥ ሽኮኮዎችና ሌሎች እንስሳት እንዲሁም አራዊት ነበሩበት። ትንንሽ ወንዶችና ሴቶች፥ ድንክ ሰዎችና የሚጨፍሩ ሕፃናትም አሉበት። ከዕቃዎች ደግሞ አበባ የተቀረጸባቸው ሳጥኖች እና ሣህኖች ይገኙበታል። ከሁሉም የሚያምረው ብዙ እንስሳት የሚገቡበት የኖኅ መርከብ ቅርጽ ነው። ሉሲየን ዓይኖቹን ከቅርጻ ቅርጾቹ ላይ ሊያነሣ አልቻለም። በዝምታ ይመለከታል።

«በትርፍ ጊዜዬ እየሠራሁ ያጠራቀምኳቸው ናቸው። በክረምት ምሽቶች እንደ ጓደኛ ያጫውቱኛል። በየጊዜው እየመጣህ ከጎበኘኸኝ የመቅረጫ መሣሪያዎቹን አጠቃቀም አስተምርሃለሁ» አሉ ሽማግሌው።

ሉሲየን ቀና ብሎ ሽማግሌውን በጉጉት አስተያየት ተመለከታቸው። ፊቱ ሕይወት የሚታይበት እንጂ እንደ ቀድሞው አስቀያሚ አልነበረም።

«ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለኑሮህ የሚያስፈልግህን ገቢ ልታገኝ ትችላለህ ነው ያሉኝ?» አለ ሉሲየን በማመንታት።

«አዎ፥ ቀስ በቀስ። ቅርጻ ቅርጾችን በደህና ዋጋ የሚሸጥ ጓደኛ አለኝ። ብዙዎቹን ትንንሽ ቅርጻ ቅርጾች ይሸጥልኛል። አንዳንዶቹን ቅርጾች ስለምወዳቸው አልሸጣቸውም። በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥሩ ጥሩ



ሥራዎችህን መሸጥ ይጀምር ይሆናል። በእኔዎቹ የእጅ መሣሪያዎች አማካይነት በሴንጢህ ከምትሠራቸው የተሻሉ ቅርጻ ቅርጾች በቅርቡ ልትሠራ ትችላለህ።»

ሉሲየን አሁንም ሽማግሌውን ትኩር ብሎ አያቸው። ሽማግሌው ለእርሱ የሚያስቡለትና ሊጠቅሙት የሚፈልጉ ሆኖ ስለ አገኛቸው ልቡ በደስታ ዘመረች። ሉሲየን አሁን ሊፈራው የማይገባና መልካም ነገር የሚስብለት ሰው አገኘ። የሽማግሌውን እጅ ጥብቅ አድርጎ ያዘና፥

«በጣም አመሰግንዎታለሁ! ለእኔ በጣም ደግ ሰው ነዎት!» አለ።

«እኔ ብቸኛ ሰው ነኝ! ጓደኞች የሉኝም። ቅርጻ ቅርጾችን አብረን ልንሠራ እንችላለን» አሉ ሽማግሌው።

«እኔም ብቸኛ ነኝ፥ ጓደኞች የሉኝም።»

ሉሲየን ከሽማግሌው ተለይቶ በጫካው ውስጥ ወደ ቤቱ በሚመለስበት ጊዜ አእምሮው በተለያዩ አሳቦች ተሞልቶ ነበር። ከሁሉም ይበልጥ ጠቃሚ የሆነው አንድ አሳብ ግን ለዳኒ የኖኅ መርከብ ያለው ቅርጽ የመሥራት ዕቅድ ነበር። ልክ ሽማግሌው እንደ ሠሩት ብዙ ትንንሽ አራዊት የሚገቡበት መርከብ ለመሥራት አሰበ— አንበሳዎች፥ ዝሆኖች፥ ጥንቸሎች፥ ግመሎችና ላሞች እንዲሁም ኖኅ ከነሚስቱ የሚገቡበት። ቅርጹ በደንብ ተሠርቶ ሲጠናቀቅ ወደ እነ አኔት ቤት በመሄድ እንደ ሰላም በረከት ለዳኒ ይሰጠዋል። ማንም ቢሆን ለዳኒ እንዲህ ያለ በረከት ሊሰጠው አይችልም! ከዚያ በኋላ ምናልባት በትንሹም ቢሆን ከዳኒ ጋር ጓደኛ እንዲሆን እነ አኔት ይፈቅዱለት ይሆናል።

ይህን አሳብ ገና ሲያሰላስለው ልቡ በፍጥነት ይመታ ጀመር። ጫካውን አቋርጦ መንደሩን ከተራራው ግርጌ እስኪያይ ድረስ፥ ለሁለት ሰዓት ያህል ደስተኛ ሆነ። ነገ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ አለበት። እንደገና ብቸኝነትና ፍርሃት ውስጥ ይገባል። ይሁን እንጂ ዛሬ አንድ ጓደኛ አግኝቷል።

ሉሲየን ከትምህርት ቤት መልስ በሳምንት ሦስት ቀን ወደ ሽማግሌው ጎጆ ይሄዳል። ጸጥታ የሰፈነበትን ጫካ አቋርጦ ይጓዝና ሽማግሌው ጎጆ በረንዳ ላይ ቁጭ ብሎ የኖኅ መርከብን ቅርጽ ይሠራል። ስለታምና ለሥራ ምቹ በሆኑ የእጅ መሣሪያዎች መጠቀም በጣም አስደሰተው። ከሉሲየን አሮጌ ሴንጢ በጣም ይለያሉ።

ሽማግሌው በሉሲየን ችሎታ በጣም ተደነቁ። ወደ ኖኅ መርከብ የሚገቡ እንስሳት ዓይነት በየዕለቱ ይጨምራል። ወደ ሽማግሌውው ቤት

በመጣ ቁጥር ስለ አዲስ እንስሳ ቅርጽ ያስባል። በመሆኑም ሥራው እየተራዘመ ሄደ።

በዚህ ወቅት ሉሲየንን ደስ የሚያሰኝ ሌላ ነገር ተፈጠረ። አንድ የትምህርት ቤቶች አስተዳዳሪ መጥቶ የእጅ ሥራ ውድድር ለተማሪዎች አዘጋጀ። ሴቶቹ የሚወዳደሩት በሹራብ፥ በጥልፍና በዳንቴል ሥራ ሲሆን፥ ወንዶቹ ደግሞ ከእንጨት በሚሠሩ ቅርጻ ቅርጾች ነበር። ብዙዎች ወንዶች ልጆች ለውድድር የሚያቀርቧቸውን የእንጨት ሥራዎች የሚያዘጋጁት በስለት በመፋቅ ነበር። አንዳንዶቹ ልጆች ጥሩ ጥሩ ቅርጾችን መሥራት ጀመሩ።

«እንደ እኔ በእንጨት ቅርጻ ቅርጽ ሥራ የሠለጠነ ልጅ የለም» አለ ሉሲየን ለራሱ፥ «በውድድሩ አሸንፋለሁ። ምንም እንኳን በሌሎች ትምህርቶች ደካማ ብሆንና ከእኔ ጋር የሚጫወት ልጅ ባይኖርም፥ ማሽነሬን ሲመለከቱ እኔም አንድ ጥሩ ነገር ልሠራ እንደምችል ያውቃሉ።»

ያን ዕለት ወደ ቤቱ የተጓዘው እየዘመረ ነበር። በተደነቁ ተማሪዎችና የትምህርት ቤቱ ሰዎች መሀል አቋርጦ በመሄድ ሽልማቱን ሲቀበል በአሳቡ ታየው። ከዚያ በኋላ ምናልባት ሁሉም ይወዱት ይሆናል።

ረጅም ጋማውን በአየር ላይ ብትን እያደረገ የሚጋልብ ፈረስ ቅርጽ ለመሥራት አሰበ። ፈረሱ ጭራውን የዘረጋና አየር ለመሳብ ይመቸው ዘንድ የአፍንጫውን ቀዳዳዎች በሰፊው የከፈተ ይሆናል። ሉሲየን ፈረሶችን ይወዳል። ሽማግሌው የሠሩትን የፈረስ ቅርጽ አይቶ ሉሲየን በጣም ነው ያደነቀው። የኖኅ መርከብ ቅርጽ ሥራው በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለሚጠናቀቅ፥ ሉሲየን ያሰበውን ትንሽ የፈረስ ቅርጽ ሥራ ይጀምራል።

ስለሚያሸልመው ውድድር ሊነግራቸው ወደ ሽማግሌው ቤት ሮጠ። ሽማግሌው በሰሙት ዜና በጣም ተደሰቱ። በውድድሩ ሉሲየን እንደሚያሸንፍ እርሳቸውም እርግጠኛ ሆኑ።

«ለምንድን ነው የፈረስ ቅርጽ ለመሥራት ያሰብከው? የኖኅ መርከብ ቅርጽህን ለውድድር ልታቀርብ ትችላለህ። በጣም ጥሩ አድርገህ ነው የሠራኸው» አሉ ሽማግሌው።

«ለስጦታ ነው ያዘጋጀሁት እርሱን» አለ ሉሲየን እራሱን እየነቀነቀ።

«ለስጦታ? ለማን? ለትንሽ ወንድምህ?»

«ጉዳት ለደረሰበትና መራመድ ለማይችል ልጅ።»



«እውነት? እንዴት ነው ጉዳቱ የደረሰበት?»

«ገደል ውስጥ ወደቀ።»

«ያሳዝናል። እንዴት ሊሆን ቻለ?»

ሉሲየን ለጊዜው ዝም ለማለት ቢፈልግም፥ የሽማግሌው ጓደኛነትና ጥሩ ሰው መሆን እውነቱን እንዲነግራቸው አስገደደው። ቀና ብሎ አያቸውና፥ «ገደሉ ውስጥ ለመውደቁ ጥፋተኛው እኔ ነኝ። የድመት ግልገሉን ወደ ገደሉ ስወረውርበት ሊይዛት ሞከረ» አለ።

ይህን እንደ ተናገረ ምላሱን መንከስ ቃጣው። ምክንያቱም ታሪኩን የሰሙት ሽማግሌ ይጠሉትና እንደ ሌሎቹ ሰዎች ያባርሩት ይሆናል።

እርሳቸው ግን ሉሲየን እንደ ፈራው አላደረጉም። «ለዚህ ነዋ ጓደኛ ያጣኸው» አሉ ረጋ ባለ ንግግር።

«አዎ።»

«እና የኖኅ መርከብ ቅርጽ ያለውን መጫወቻ ለልጁ በመስጠት የተበላሹ ነገሮችን አስተካክላለሁ ብለህ ተስፋ ታደርጋለህ?»

«አዎ።»

«ጥሩ አሳብ ነው። የጠፋ ፍቅርን እንደገና ለማግኘት ከባድ ልፋትን ይጠይቃል። ቢሆንም ተስፋ አትቁረጥ። ጽኑ ሰዎች ከሚያገኙት ይልቅ በጥረታቸው በሚፈጥሩት ፍቅር የበለጠ ደስተኞች ይሆናሉ።»

«የሚሉት አይገባኝም» አለ ሉሲየን ትኩር ብሎ እያያቸው።

«ፍቅርን ወዳጆችህ ላልሆኑ ሰዎች በመስጠት ጊዜህን ብታባክን ኀዘንና ተስፋ መቁረጥ ይገጥምህ ይሆናል። በትዕግሥት ብትገፋበት ግን የመፈቀር አፀፋ ብታገኝም ባታገኝም ደስታን የምታገኘው በማፍቀርህ ነው። ይህን ማለቴ ነው። ብቻዬን የምኖርና ማንንም የማላፈቅር ሰው ሆኜ ሳለ ይህን መናገሬ ይገርምህ ይሆናል። ነገር ግን ይህ የማምንበት አሳብ ነው።»

የኖኅ መርከቡ ቅርጽ ሥራ ያን ዕለት ማምሻውን ተጠናቀቀ። ሉሲየን በደስታ ፈገግ እያለና ልቡ በፍጥነት እየመታ እግረ መንገዱን የመርከቡን ስጦታ እነ ዳኒ ቤት ለማድረስ ሄደ።

እስፍራው እንደ ደረሰ ፈራና አንድ ዛፍ ሥር ተደበቀ። የዳኒን ቤተሰቦች ምንድን ነው የሚላቸው? እንዴት ነው ንግግሩን የሚጀምረው? ዳኒን ብቻውን ቢያገኘው ጥሩ ነበር! እኔት ግን ሁል ጊዜ ከትምህርት በኋላ ከእርሱ ጋር ነው የምትሆነው።

የኖኅ መርከቡን ቅርጽ ሲመለከቱ በእርግጥ ይቅርታ ያደርጉለታል! ይቅርታ ቢያደርጉለትና ሌላ ዕድል ቢሰጡት፥ ከእንግዲህ ያለ ሕይወቱን ላለፈው ጥፋቱ ማካካሻ የሚሆን መልካም ሥራ እየሠራ ያሳልፍ ነበር። እንዲህ በተስፋና በፍርሃት መካከል እየታገለ ከተደበቀበት ወጣና ወደ እነ ዳኒ ቤት ሄደ።

አኔት ብቻዋን ውጭ ተቀምጣለች።

ሉሲየን በፍርሃት የደረቀ ጉሮሮውን ለማራስ ምራቁን ጉርጉጭ አድርጎ ወደ እርሷ ቀረበና የሠራውን የኖኅ መርከብ ቅርጽ ወደ እርሷ ዘርግቶ፥

«ለዳኒ ነው ያመጣሁለት» አለ በሹክሹክታ። ቃላቱ ከላንቃው ጋር ተጣብቀው አልወጣ ያሉት ይመስላል። በሀፍረት መሬት መሬቱን እያየ ስጦታ የያዘ እጁን ወደ እርሷ ዘረጋው።

«እንዴት ብትደፍር ነው ወደዚህ የመጣኸው! እንዴት ብትንቀን ነው ለዳኒ ስጦታ ያመጣህለት! ሂድ ከዚህ! ሁለተኛ እንዳትመጣ!» ብላ ጮኸችበት።

እንዲህ በቁጣ እየተናገረች ሉሲየን የያዘውን ቅርጽ ባለ ኃይሏ በእርግጫ መታችና ከበታቿ ካለው የእንጨት ክምር ውስጥ ከተተችው። ከኖኅ መርከብ ጋር የተሠሩት የእንስሳትና የአራዊት ቅርጾች ሁሉ በየግንዱ ላይ ተበታተኑ።

ሉሲየን ለጥቂት ጊዜ አኔትን ትኩር ብሎ ካያት በኋላ፥ መለስ ብሎ ባለው ፍጥነት ሮጠ። ጥረቱ ሁሉ ከንቱ ሆነ። ለዘላለም ይቅር አይባልም። ልፋቱ ሁሉ በከንቱ ጊዜ ማባከን ሆነ።

እንዲህ ባለው ስሜት ውስጥ እያለ ነው የሽማግሌው ምክር ቁጣና መራራነት በሞላበት ልቡ ላይ፥


«ጽኑ ሰዎች ከሚያገኙት ይልቅ በሚፈጥሩት ፍቅር የበለጠ ደስተኞች ይሆናሉ።» እያለ እንደ ቀጭን የብርሃን ጨረር ያበራበት።

ይህ አባባል ምናልባት እውነት ይሆናል። ሉሲየን ምንም ያተረፈው ነገር የለም። ነገር ግን የኖኅ መርከብ ቅርጽን በመሥራቱና ለዳኒ ደስታ በማሰቡ ደስተኛ ነው። በትዕግሥትና በጽናት በርትቶ ፍቅርን በሥራዎቹ ውስጥ መግለጹን ከገፋበት ምናልባት አንድ ሰው፥ አንድ ቀን የፍቅር ስጦታውን ይቀበልና ስለ ስጦታው ይወደው ይሆናል።

ይህ እውን ይሁን አይሁን አያውቅም። ነገር ግን ሙከራውን ላለማቋረጥ ወሰነ።



## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## ወደ ለምለሙ ከፍታ ስፍራ ጉዞ



የዳኒ እግር ቶሎ አልዳነም። ሐኪሙ ብዙ ጊዜ ቤት ድረስ እየመጡ ቢጎበኙትም፥ ስለ ልጁ ጤንነት የስጉና ግራ የተጋቡ ይመስላሉ። ዳኒ ወደ ሆስፒታል ሄዶ ቁስሉ ላይ የታሠረው ፋሻ መፈታቱ አስፈላጊ የሆነበት ጊዜ መጣ። በዚህ ጊዜ ነው ሐኪሙ ዝምታውን ጥሰው ሁልጊዜ ይፈሩት የነበረ ነገር መድረሱን ለዳኒ አባት የነገሯቸው። የልጁ ሰባራ እግር ከጤነኛው በጣም ስለ አጠረ ወደፊት በትክክል ለመራመድ አይችልም።

የዳኒ አባት መርዶ መሰሉን ዜና ከሰሙ በኋላ በጣም እያዘኑ ወደ አንድ አናፂ ቤት ሄደው ምርኩዝ መሰል ሁለት ትንንሽ መደገፊያዎችን ወይም ክራንቾችን እንዲሠራለት ጠየቁት። ቀጥሎም የዳኒን ጥንድ ጫማዎች ወደ ጫማ ሠሪ ቤት ወስደው የአንደኛውን መርገጫ ወይም ሶል ከሌላው በሁለት እጅ አወፍሮ እንዲሠራው ጠየቁት።

አናፂውም ሆነ ጫማ ሠሪው በዳኒ ሁኔታ አዘኑ። ዳኒ በክራንቾቹ በተጠቀመ ቁጥር እያያቸው ፈገግ እንዲል በማሰብ በእጀታዎቹ ላይ የድቦች ራስ ቅርጽ ሠራባቸው። ጫማ ሰፊው ደግሞ የዳኒ አባት በጠየቁት መሠረት ሠርቶ ሲያመጣ ጫማዎቹ ውስጥ ቸኮላት ከረሜላዎች ሞልቶባቸው ነበር። ከዚህም ሌላ ሁለቱም ባለሙያዎች

የተጠየቁትን በጥሩ ሁኔታ ሠርተዋል። ዳኒ ክራንቾቹን እንደ አዲስ መጫወቻዎች ስለ ቆጠራቸው፥ ሊጠቀምባቸው ቸኮለ።

ዳኒ ለአንድና ለሁለት ቀን ያህል ክንራቾቹን ይዞ በቤቱ ደጅ ደስ እንዳለው ፌንጣ ዱብዱብ አለ። በዚያው ሰሞን አባቱ ከብቶቹ ሣር ይግጡ ዘንድ ተራራው ላይ ወደ አለው ለምለም ስፍራ የሚወስዱቸው መሆኑን ተናገሩ። ዳኒ ይህን ሲሰማ ቁጭ በማለት ድምፁን እያሰማ አለቀሰ። ምክንያቱም በአዳዲሶቹ ክራንቾቹና ጫማዎቹ ቢጠቀምም እንኳን፥ ከእንግዲህ ላሞቹን ተከትሎ ወደ ተራራማው ስፍራ ሊወጣ እንደማይችል ተገንዘበ።

ዳኒ በመጠኑ ማድረግ የሚባል ነገር ስለማያውቅ፥ አምርሮ ነበር ያለቀሰው። አኔት፥ አባቱና ሴት አያቱ እንጨት ወደ ተከመረበትና ዳኒ ወደሚያለቅስበት ስፍራ እየተሯሯጡ ደረሱ። ሁሉም እያቀፉና እየሳሙ አባባሉት። ጫጫታ የማትወደው የዳኒ ድመት ጀርባዋን ወደ ላይ አጉብጣ በመቆም መቆጣቷን ለመግለጽ ልዩ ድምፅ አሰማች።

ዳኒ ያለቀሰበትን ምክንያት ቤተሰቦች ሲረዱ፥ የማጽናኛ ዘዴዎች ያቅዱ ጀመር። በመጨረሻም ዳኒ ላሞች እንደ ተሰበሰቡ ያያቸው ዘንድ ከበታቻቸው ወደአለው የገበያ ስፍራ በእንጨት ጋሪ ሊወስዱት ወሰኑ። ከዚያ በኋላ በፈረስ በሚጎተት ጋሪው ላይ እንደሆነ ወደ ላይ የሚወጡ ላሞችን ተከትሎ ይሄዳል። ሴሊቱን ድርቆሹ ሣር ላይ ተኝቶ ያድርና በነጋታው ይመለሳል። ሴት አያቱ እና ክላውስ ቤት ሲቀሩ፥ አኔት አብራው ልትሄድ ትችላለች።

ዕቅዱ የወጣለት ዕለት ደረሰ። ደስ የሚል ቀን ነው። ዳኒ ዕለቱ አንድ ደስ የሚል ነገር የሚከናወንበት መሆኑ እየተሰማው በማለዳ ነበር የነቃው። ለመዘመር ሞክሮ ያልተሳካለት መሆኑን አስታወሰ። ከዚያም አጠገቡ የነበረች ድመቱን ወደ መኝታው በማስገባት ስለ መዝሙሩ ያወራላት ጀመር። ድመቲቱ ወሬው ምንም የጣማት አልመሰለችም። እንደ ምንም ታግላ ከእጆቹ መሀል ወጣችና ጅራቷን ወደ ላይ እንዳቆመች አይጥ ለማደን እንጨቱ ወደ ተከመረበት ስፍራ ሄደች።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ዳኒ በእንጨት ማጓጓዣ ጋሪ ላይ ተሣፈረና አኔት ወደ መንደሪቱ ይዛው ሄደች። ገና ወደ ገበያው ከመቃረባቸው በፊት ነው እነ አኔት ላሞች አንገት ላይ የሚታሰሩ ቃጭሎች ደውል፥



የከብቶች ጩኸት፥ የደስተኛ ልጆች ጫጫታና የገበያተኛው ሁካታ የተሰማቸው። በአንድ ምንጭ አቅራቢያ በሚጠማዘዘው መንገድ እጥፍ ሲሉ የተመለከቱት ገበያ ልዩ ነው!

ገበያው በጣም በተጠጋጉ ላሞችና ጥጃዎቻቸው ተሞልቷል። ሁሉም በአንገታቸው ላይ ቃጭል የታሠረባቸው ሲሆኑ፥ በፍርሃት ራሳቸውን ይነቀንቃሉ። አልፎ አልፎ አንዳንድ ላሞች የታሠሩበትን ገመድ እየፈቱ ወይም እየበጠሱ ሌሎቹ ላሞች ላይ ይዘሉባቸዋል። እልፍ ብሎ ደግሞ ግሮሠሪው በር ላይ የተሰበሰቡ ወጣቶች ቀንዱን በመስኮት ለማስገባት የሚታገል አንድ ወይፈን እየተመለከቱ ይስቃሉ። በዕለቱ ትምህርት ስለሌለም ትንንሽ ሕፃናት ወጣቶች በአካባቢው ይሯሯጣሉ።

ስዊዘርላንድ ውስጥ፥ ሣር በየሜዳው የሚያድገው በበጋ ነው። ያኔ ላሞች ወደ ከፍታ ስፍራ እየሄዱ ለምለሙን ሣር ይግጣሉ። በየሸለቆው ያለው ሣር ግን ለድርቆሽነት ይጠበቃል። ላሞች ሣር ለመጋጥ ራቅ ወዳለ ከፍታ ስፍራ ሲሄዱ ትልቅ ወንዶች አብረዋቸው ይጓዛሉ። ሴቶችና ትንንሽ ልጆች ግን ሠፈር ነው የሚቀሩት። ላሞች ወደ ተራራማ ስፍራዎች በተለያየ አቅጣጫ ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት አንድ ቦታ ይሰበሰባሉ። ጉዞ ሲጀምሩ ልጆች የየራሳቸውን ላሞች ተከትለው ወደሚሄዱበት ያደርሷቸዋል።

ዳኒ ገበያው ስፍራ ሲደርስ ሰዎች ክብብ አደረጉት። የመንደሪቱ ሰዎች ወደ ሆስፒታል ሲሄድ ካዩት ወዲህ ሲያገኙት ዛሬ የመጀመሪያቸው ስለሆነ፥ ሁሉም ሊያዩት ፈልገዋል። ሕፃናት የተቀመጠበትን ጋሪ ፈረስ ለመሳብ ተሽቀዳደሙ፥ ሴቶቹ ደግሞ ሊስሙት ፈለጉ። በላሞቹና በእነርሱ ዙሪያ በተሰበሰበው ሕዝብ ትርምስ ዳኒ ተገፍቶ አለመውደቁ አስገራሚ ነበር።።

ላሞቹና አጃቢዎቻቸው ጉዞ የሚጀምሩበት ጊዜ በመቃረብ ላይ ነው። ገበሬዎቹ ላሞቻቸውን የሚመራውን ከብት መርጠው ወደፊት ይነዱታል። እርሱ ወደፊት ሲሄድ አብረው የሚጓዙት ከብቶች ይከተሉታል። የቡድን መሪ የሚሆነው ከብት አንገቱ ላይ የሚታሠርለት ቃጭል ሌሎቹ ሁሉ ከሚያደርጉት ይበልጣል።

የዳኒ አባት መሪ የሚሆነውን ከብት ከመሀል ወደፊት ለማውጣት በመሳብ ላይ ናቸው። የእርሳቸው የሆኑ ጥቂት ከብቶችም መሪያቸውን እየተከተሉ በፍጥነት በመውጣት ላይ ናቸው። የያዙትን መሪ ከብት

እንደያዙ ዳኒ ወደ ነበረበት ጋሪ ሄዱና፥ «በበቅሎ የሚሳበው ጋሪ ከጫማ ሰፊው ጓሮ ቆሞ ይጠብቃችኋል። ዳኒን ወደዚያ አዛውሪውና ጉዞ እንዲጀምር» አሏት አኔትን።

ይህን ለአኔት ከነገሯት በኋላ ላሞቻቸውን አጅበው ሽቅብ ወደ ተራራው ጉዞ ጀመሩ። የዳኒ አባት ሲጓዙ በላሞቹ ብቻ ሳይሆን በሚወዷቸው የመንደሪቱ ልጆችም ታጅበው ነበር። ዳኒ የተሣፈረበትና በበቅሎ የሚሳበው ጋሪም በልጆቹ ላይ ከኋላ ደረሰባቸው። አኔት የበቅሎውን መሪ ልጓም ይዛ ጋሪውን ትነዳለች። ዳኒ ለመንደሪቱ ሰዎች ሊያሳያቸው ያመጣቸውን ከራንቾች ይዞ ከኋላ በመቀመጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ የደስታ ድምፅ ያሰማል።

ያን ዕለት እስከ ተራራው ያደረገውን ጉዞ ዳኒ ፍጹም አልረሳውም። ናፖሊዮን በሚሰኝ ስም የሚጠራ አንዱ ጥጃ በጉዞው ወቅት ደክሞት ወደ ኋላ ቀርቶ ነበር። ዳኒ ነው ተንጠራርቶ ወይፈኑ አንገት ላይ የነበረውን ማሰሪያ በመያዝ ከጋሪው እኩል ያስኬደው።

አባቱ ዳኒን ወደ ኋላ አየት አድርገው፥ «ደክሞታል! ጋሪው ላይ ብታሣፍረውና ከአንተ ጋር ቢጓዝ ይሻላል» አሉና እግሮቹ በድካም እጥፍ እጥፍ የሚሉበትን ጥጃ ብድግ አድርገው ጋሪው ላይ አስቀመጡት። ዳኒ የጥጃውን ፀጉራማ አንገት በደስታ እቅፍ አደረገ። ጆሮዎቹና ግንባሩ ላይ ያለው ከብ ደስ ይላል። ጥጃውና ዳኒ በዚህ ሁኔታ ጎን ለጎን በመቀመጥ ጫካውን እየተመለከቱና የአበቦችን ጥሩ መዓዛ እያሸተቱ ተጓዙ።

ጫካውን አቋርጠው በወጡ ጊዜ፥ በአረንጓዴ ሣር እተሸፈነው ተራራ ላይ ወጥተው ነበር። እዚያ ሆነው ከበታቻቸው ያሉትን ሸለቆዎችን ተመለከቱ። ሁልጊዜ አናታቸው ላይ የረጋ በረዶ የማያጡት ተራራዎችም ከሩቁ ይታዩዋቸዋል። ዳኒ በጀርባው ተጋድሞ የተራራዎቹን ጫፍ እየቆጠረ፥ እራሱን መንግሥተ ሰማያት ውስጥ እንዳለ ሰው አድርጎ አሰበ። ደስታውንና አሳቡን የተሟላ ለማድረግ በማሰብም ቁጭ ብሎ ከተያዘለት ምግብ በማውጣት ይበላ ጀመር። የረጅም ዳቦውን አንድ ጫፍ እርሱ በጥርሱ ሲሸራርፍ፥ ጥጃው ደግሞ ሌላኛውን ጫፍ ይልስ ነበር።

አኔት ለጥቂት ጊዜ ከተጓዘች በኋላ ዳኒ የተቀመጠበትን ጋሪ የሚጎትተውን በቅሎ ለቀቀችው። እራሱ በትክክል ይጓዝ ጀመር። እርሷ



ከመንገዱ ግራና ቀኝ እሮጥ እሮጥ እያለች አበቦች ትለቅማለች። ስትመለስ ለሴት አያቷ ልትሰጣቸው አስባለች። ዳኒም እንደ አኔት እየተሯሯጠ አበባ ቢለቅም ደስ ይለው ነበር። ነገር ግን ይህ ለረጅም ጊዜ የሚያስበው ነገር አልሆነም። ደስ የሚሰኝበት ብዙ ነገር ነበር። እግሩ ባይጎዳ ኖሮ የድብ ቅርጽ የተሠራባቸው ቆንጆ ከራንቾች አይኖሩትም ነበር። ወይም ጥጃ አቅፎ በጋሪ አይጓዝም ነበር።

ብዙ ከተጓዙ በኋላ ብዙ ሥሮች ካሉት አንድ ትልቅ ዛፍ አጠገብ ደረሱ። ያን አለፍ ብለው መንገዱ ወደ ግራ ከሚታጠፍበት ማዕዘን ላይ ሲደርሱ፥ የአኔት ቤተሰብ በበጋ የሚያርፍበት ቤት በሩቁ ታያቸው። ቤቱ ከከብቶች በረት ጋር የተያያዘ አንድ ሳሎን ብቻ ያለው ሲሆን፥ ቢጫ አበባ በሚበዛበት ሜዳ መሀል ቆሟል። ከቤቱ ቀጥሎ ወደ ተራራው ሲወጣ የመጨረሻው የሆነ ቀጥ ያለ ገደል አለ።

የእነ አኔት የበጋ ቤት እንደገና ተከፍቶ ሰዎች እንዲኖሩበት የጓጓ ይመስላል። ላሞቹም ቤቱን እንደ ተመለከቱ ፍጥነታቸውን ጨመሩ! የአንገታቸው ቃጭልም ድምፅ ጎላ አለ።

ከቤቱ ውጭ ያለው ምንጭ ወደ ጫካው ይወርዳል። በውኃ ጥም የተዳከሙት ከብቶች እራሶቻቸውን ምንጩ ውስጥ እየነከሩ እስኪረኩ ጠጡ። ዳኒና አብሮት የነበረው ጥጃም ከጋሪው ወርደው ከምንጩ ጠጡ። ቤቱ አጠገብ ሲደርሱ ሁሉም በሩ አጠገብ ተሰባሰቡ። የዳኒ አባት የበሩን ቁልፍ ከፍተው ወደ ውስጥ ገቡ።

ቤቱ ክረምቱን በሙሉ በበረዶ ተሸፍኖ ስለነበር ጨለማና ቀዝቃዛ ሆኖ ነበር የቆየው። አኔትና አባቷ ለማገዶ የሚሆን እንጨትና ሌላም ነገር በጋሪው አምጥተው ስለነበር ቤቱ ውስጥ እሳት አቀጣጠሉ። አኔት መጋረጃዎቹን ስትገልጣቸው የፀሐይዋ ብርሃን ወደ ውስጥ ገባ። ያን ጊዜ ቤቱ ውስጥ በየዕቃው ላይ የነበረው አቧራ ወለል ብሎ ታየ።

አኔት መጥረጊያ ይዛ አቧራውን ትጠራርግ ጀመር። ዳኒ ደግሞ እንደ ፌንጣ እየዘለለ ከኋላዋ ይከተላታል። የእነ አኔት አባት ለከብቶቹ ድርቆሽ ሣር ለማውረድ በመሰላል ወደ ቆጥ ወጡ። ወተት የሚታለብበት ሰዓት ሲደርስ ደግሞ ላሞቹ ወደ መታለቢያ ስፍራቸው በተራ ገቡ። ምግብ ከተዘጋጀ በኋላ አኔትና አባቷ ጠረጴዛው አጠገብ ወንበር ላይ ሲቀመጡ፥ ዳኒ ደግሞ ምንጣፍ መሳይ ጨርቅ ተነጠፈለትና ወለሉ ላይ ቁጭ አለ። ወንበር ላይ እንዳይቀመጥ የእግሩ

ሁኔታ አልተመቸውም። ለእራት የተመገቡት ዳቦ በመረቅና በአይብ ሲሆን፥ የጠጡት ደግሞ ቡና ነበር። በጣም ጥሩ እራት ነበር።

ዳኒ መመገቡን እንደ አበቃ ለመቆም እየታገለ እጆቹን ወደ አባቱ ዘረጋ።

«ለመተኛት ትፈልጋለህ?» አሉ አባቱ እጆቹን ይዘው እንዲቆም እየረዱት።

«አይደለም፤ ወደ ተራራው ጫፍ ውሰደኝ» አለ ዳኒ ጠንከር ባለ አነጋገር።

የዳኒ አባት ደነገጡ። ተራራው አናት ላይ ለመድረስ እንደ ግድግዳ ቀጥ ባለው ገደል ላይ እየተንጠላጠሉ ለሀያ አምስት ደቂቃ መጓዝ ያስፈልጋል። በሸክም ለማጓጓዝ ደግሞ ዳኒ ከባድ ልጅ ነው። ያም ቢሆን የዳኒ አባት ትንሽ ልጁ የሚጠይቃቸውን ነገር ሁሉ እምቢ አላደርግም ማለቱ ሁልጊዜ ያስቸግራቸዋል። በመሆኑም በራሳቸው ሞኝነት ከት ብለው እየሣቁ ተነሡና ልጃቸውን በትከሻቸው ተሸክመው ጉዞ ቀጠሉ። ዳኒ በእግሮቹ ተረከዝ የአባቱን ደረት መታ መታ ያደርጋል፤ አኔትም የአባቷን ኮት ጫፍ ይዛ ተከተለቻቸው።

ተራራው ብዙም ባልተለመዱ ውብ አበቦች ተሸፍኗል። የአኔት አባት ዳኒን ተሸክመው በድካም ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ መናገር እስኪያቅታቸው ድረስ ቶሎ ቶሎ ይራመዳሉ። አኔት እየተሯሯጠች አበቦቹን ትቀነጥሳለች። ተራራው አናት ላይ ሲደርሱ ብቻ ነው አባቱ ዳኒን ከትከሻቸው ያወረዱት። ሁሉም ቁጭ ብለው የየራሣቸውን አሳብ እያሰላሰሉ ዙሪያ ገባውን ይመለከቱ ጀመር።

በሚመለከቱበት አቅጣጫ ሁሉ በአበባ የተሸፈኑና ጫፋቸው በበረዶ የተሸፈነ ተራራዎች ይታዩዋቸዋል። ፀሐይዋ በመጥለቅ ላይ በመሆኗ ሸለቆዎች በድንግዝግዝ ጨለማ በመሸፈን ላይ ናቸው። ረጃጅም ተራራዎች ውስጥ በመጥለቅ ላይ ያለችው ፀሐይ የመጨረሻ ጨረር ስለ አረፈባቸው ሀምራዊ ብርሃን ተጎናጽፈዋል። ያን ብርሃን የሚመለከት ሕፃን ተራራዎቹ በመቃጠል ላይ ናቸው ብሎ ሳያስብ አይቀርም። እንዲያ ላሉ ትእይንቶች እንግዳ ያልሆነው ዳኒ ግን በእርካታ ፈገግ አለ። በነበሩበት ተቀምጠው ሲመለከቱ ፀሐይዋ ይበልጥ ስለ ጠለቀች ብርሃንዋ የሚታየው ተራራዎቹ የመጨረሻ ጫፍ ላይ ብቻ ሆነ። ቀስ በቀስ ያም ብርሃን ደበዘዘና በጨለማ ተሸፈነ። ያን



የተኩት፥ ቅዝቃዜ፥ ጥቋቁር ተራራዎችና ከእነርሱ ጀርባ ብቅ የሚሉ ከዋክብት ናቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ጨረቃ ትወጣና ተራራዎቹን በብርማ ብርሃን ታጥለቀልቃቸዋለች።

ወደ ቤት ተመልሶ በር በመዝጋት ትርክክ ካለው ፍም ዙሪያ ተቀምጦ እሳት መሞቁ አስደሳች ነበር። የበረቱ በር ክፍት ስለነበር ጥጃው መጣና ረጃጅም እግሮቹን እጥፍጥፍ አድርጎ ዳኒ አጠገብ ተቀመጠ።


«ጥጃው ከእኔ ጋር እንዲተኛ እፈልጋለሁ» አለ ዳኒ ጠንካራ ውሳኔ በሚመስል ንግግር።

«አይሆንም ዳኒ፥ ቁንጫ ከጥጃው ይተላለፍብሃል» አለች አኔት ፈጠን ብላ።

«ጥጃው ቁንጫ ቢኖርበት ኖሮ፥ ጋሪው ላይ አብረን በነበርን ጊዜ ይተላለፍብኝ ነበር። እባክህ አባዬ ጥጃው አብሮኝ እንዲተኛ በጣም እፈልጋለሁ።»

የዳኒ አባት የልጁን ጥያቄ ለመፈጸም ዘዴ እንደሚፈልጉ ገለጡ። ከዚያም ደረቅ ሣር ጆንያ ውስጥ በመጎስጎስ ፍራሽ ሠሩ። እዚያ ላይ ጨርቅ አንጥፈው ዳኒን አስተኙት። ዳኒ አጠገብ ሣር ጎዝጉዘው ደግሞ ጥጃውን አስተኙት። አኔት የተኛችው ቤቱ ውስጥ በነበረ ብቸኛ አልጋ ላይ ነበር። አባቷ ደግሞ ሣር ማከማቻው ቆጥ ላይ ወጡና ተኙ።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## የአኔት በቀል



ሉሲየን እንደ ሌሎች ልጆች ላሞቹን ይዞ ወደ ተራራማው አካባቢ አልሄደም። ቤተሰቦቹ ያላቸው አራት ላሞች ብቻ ስለሆኑ፣ እነርሱ ከሌሎች ከብቶች ጋር በአቅራቢያው ሣር ይግጣሉ። ስለሆነም በቤቱ አካባቢ ያለው ሣር ለድርቆሽ የሚዘጋጅበት ጊዜ እስኪደርስ ከትምህርት ቤቱ መልስ ረጅም የእረፍት ጊዜ አለው። ይህ ምቹ ሁኔታ ስለ ተፈጠረለት በሳምንቱ አብዛኛውን ቀን ሽማግሌውን ለመጎብኘት ወደ ተራራው ይወጣ ነበር።

የሚሠራው የፈረስ ቅርጽ ሊጠናቀቅ ነው። በሉሲየን ዕድሜ ላለ ልጅ ሥራው በጣም ቆንጆ ነበር። ቅርጹ ከዚህ ቀደም ከሞከራቸው ሥራዎች ሁሉ ትልቅ ነው። ትልቅ ጋማና መሬት ሳይረግጡ በአየር የሚበርሩ የሚመስሉ እግሮች አሉት። ሥራው ብዙ ሰዓት ወስዶበታል። እያንዳንዱን የፈረስ ቅርጽ በትክክል ለመሥራት ይችል ዘንድ በአካባቢው ያሉ ፈረሶችን ትኩር ብሎ እየተመለከተ አጥንቷቸዋል።

ውድድሩ እስከ የድርቆሽ ሣር ዝግጅት በዓል ድረስ ስለሚቆይ፣ የፈረሱን ቅርጽ አሳምሮ የመሥሪያ በቂ ጊዜ አለው። የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ግን ገና ከአሁኑ በውድድሩ የሚያሸንፈው ማን እንደሚሆን በመተንበይ ላይ ናቸው።

ብዙዎቹ ሚካኤል የተባለው የወተት አላቢ ልጅ ያሸንፋል ይላሉ። ልጁ የሠራው አንድ ግንድ ላይ የሚወጡ ሁለት ድቦች ቅርጽ ነው።



በጣም ተግቶ የሠራው ስለሆነ ያምራል። ልጆቹ ቅርጹን እያዩ በጣም በሚያደንቁበት ጊዜ ሉሲየን ቆሞ እያሰላሰለ፣ «ድቦቹ ውሻ ወይም ሌላ እንስሳ በመምሰል ያሳስቱ ይሆናል። የእኔ ፈረስ ግን ምንም አያሳስትም። ፈረስ ነው! ሌላ ምንም አይደለም» አለ በአሳቡ።

የሚካኤልን የድቦች ቅርጽ ሲመለከት፣ በውድድሩ የሚያሸንፈው ራሱ እንደሚሆን ሉሲየን እርግጠኛ ሆነ! ለውድድር ከቀረቡት ሁሉ እንደ እርሱ ሥራ የሚያምር አልነበረም።

ሽልማቱን ሊቀበል ሲሄድ ሰው ሁሉ በአድናቆት የሚመለከተው መሆኑ በአሳቡ ታየው። ሁሉም የሠራውን የፈረስ ቅርጽ ይወዱና በአድናቆት ይመለከቱለት ይሆናል። እርሱንም ይወዱት ይሆናል።

ሴቶች ልጆች የሚያቀርቧቸው የመወዳደሪያ ሥራዎች ብዙ የሚያነጋግሩ ሆነዋል። አኔት ሥልጡን የጥልፍና የሹራብ ሥራ አዋቂ ናት። ወደ ትምህርት ቤት ባልሄደችባቸው ጊዜ ሴት አያቷ አስተምረዋታል። ዳኒን በቅርቧ አድርጋ እየተቆጣጠረችው ቁጭ ብላ ትሠራለች። ሴት አያቷ ደግሞ ባለመደገፊያ ወንበራቸው ላይ ቁጭ ብለው ባስፈለገ ጊዜ ሊረዱት እየተዘጋጁ ይመለከቷታል።

አኔት ለውድድሩ ለማቅረብ ያዘጋጀችው አንድ ጥቁር ሰማያዊ ሹራብ ነው። ዳኒ እሁድ እሁድና በበዓል ቀኖች እንዲለብሰው ነበር የሠራችው። ከአንገቱ ዙሪያና ከግርጌው በብሩህ ቀለም የተሠራ የአበባ ቅርጽ አለበት። ገና ባትጨርሰውም ሥራው በጣም ያምራል። ቁጭ ብላ ስትሠራ ያዩዋት ሁሉ አድንቀውላታል።

«ውድድሩን አሸንፈሽ እንደምትሸለሚ እርግጠኛ የሆንሽ ይመስለኛል። በሹራብሽ ላይ የምትሠሪያቸው ልዩ ልዩ ቅርጾች ለየት ያሉና አስቸጋሪዎች ናቸው። ሰው ሁሉ ነው እንዲህ የሚለው» ይሏታል ብዙዎቹ ጓደኞቿ።

አኔት እራሷም በውድድሩ እንደምታሸንፍ ተስፋ አድርጋለች። ለማሸነፍም ትፈልጋለች። ብታሸንፍ ደካማ ለሆነችበት የሂሳብ ትምህርት ማካካሻ ይሆንላታል። ሴት አያቷ፣ አባቷና ዳኒም በጣም ደስ ይላቸዋል።

ይሁን እንጂ እንደ ሉሲየን ሰፊ የእረፍት ጊዜ የላትም። ከትምህርት በኋላ ሁልጊዜ ቤት ውስጥ ሥራ ይበዛባታል። የድርቆሽ ማዘጋጃው በዓል ስለ ተጀመረ ከማለዳ እስከ ምሽት ልጆች ከትልልቅ ሰዎች ጋር መስክ ላይ ሲሠሩ ነው የሚውሉት።

በዚህ ወቅት የሚከናወነውን ሥራ አስመልክቶ በእነ አኔትና በጎረቤቶቻቸው መካከል አንዳንድ የወዳጅነት መረዳዳት ተደርጓል። ሥራ ለመርዳት የሚችሉ ወንድ ልጆች ያሉት አንድ ጎረቤታቸው የእነአኔትን ላሞች ለመጠበቅ ወደ ተራራማው የግጦሽ አካባቢ ስለ ሄደላቸው፥ የአኔት አባት ድርቆሽ ሣሩን ሊያጭዱና ሊያዘጋጁ መጥተዋል። የራሳቸውን ሥራ ከጨረሱ በኋላ ሁልጊዜ የሉሲየንን እናት ሣርን ያጭዱላቸዋል። ምክንያቱም ሴትዮይቱ ባል የላቸውም! ሉሲየን ደግሞ ሣር ለማጨድ የማይችል ትንሽ ልጅ ነው።

በእነዚያ በጣም ዳገታማ በሆኑ ተራራማ አካባቢዎች የእርሻ ወይም ማጨጃ መኪናዎች ለመንቀሳቀስ ስለማይችሉ፥ ለየት ባለ ማጭድ ነበር ገበሬዎቹ ሣሩን የሚያጭዱት። ወንዶቹ እያጨዱ ከፊት ሲቀድሙ፥ ሴቶችና ልጆች እየተከተሉ ሣሩን በመሰብሰብ ይከምራሉ። ትንንሽ ልጆች እንኳን ሳይቀሩ በመጠናቸው የተሠራላቸውን የሣር መሰብሰቢያ ይዘው በሥራው ላይ ይሠማራሉ።

የሣር መስካቸው በጣም ሰፊ ስለሆነ፥ አኔትና አባቷ በርትተው መሥራት ነበረባቸው። የሚረዱቸው የቀን ሠራተኞች እንዳይቀጥሩ ገንዘብ የላቸውም። ሥራቸውን የሚጀምሩት ገና ማለዳ ቅዝቃዜው ሳይለቅ ነበር። ሞቅ ሲል ረፋዱ ላይ ደግሞ የእነ አኔት ሴት አያትና ዳኒ ይመጣሉ። ሴትዮይቱ ከሕመማቸው ጋር እየታገሉ በቀስታ ይሠራሉ። ዳኒ ግን ስለማይችል ምንም አይሠራም። በዚያ ፋንታ በታጨደው ሣር ላይ እንደ ሚዳቆ ይዘላል! አንዳንዴ ደግሞ ሣር ክምር ውስጥ ይገባና ይደበቃል። ሲደክመው በጀርባው ተንጋልሎ ፀሐይ እየሞቀ ያንቀላፋል።

የዳኒ አባት የራሳቸውን አጭደው ከጨረሱ በኋላ እነ አኔት የታጨደውን እየሰበሰቡ እንዲከምሩ ነገሯቸውና ወደ ሉሲየን እናት መስክ ሄዱ። የሉሲየን እናት ልጃቸው በዳኒ ላይ ባደረሰው አደጋ በመቀየም አባቱ በአጨዳው አይረዱኝ ይሆናል በማለት ፈርተው ነበር። አንድ ቀን ጠዋት ከእንቅልፋቸው በመስኮት ሲመለከቱ ግን የዳኒ አባት ሣራቸውን ሲያጭዱላቸው አዩ። ከወገባቸው በላይ እራቁታቸውን ሆነው የቁም ማጭዳቸውን እያወናጨፉ ሥራውን ያጣድፉታል። ቂመኛና የበቀል ሰው አልነበሩም።

«ፍጠን ሉሲየን ! የዳኒ አባት ሣራችንን እያጨዱልን ነው። እሩጥና የታጨደውን ሣር መከመር ጀምር» አሉ የሉሲየን እናት።



ሉሲየን እያፈረና እየፈራ የዳኒ አባት ወደአሉበት ሮጠ። እዚያ እንደ ደረሰም አቀርቅሮ ሰላምታ ሰጣቸው። ከበደለው ሰው ጋር መሥራቱን ስለአልወደደ፥ ከዳኒ አባት ራቅ ብሎ ነበር የሚሠራው። የዳኒ አባትም ሉሲየንን ሊያናግሩት አልፈለጉም። የጎረቤትን ሣር ማጨድ አንድ ነገር ነው። ትንሽ ልጁን ለከባድ አደጋ ከዳረገ ልጅ ጋር ማውራት ደግሞ ሌላ።

አኔት ለአባቷ ምግብ ይዛ በምሳ ሰዓት መጣች። ሉሲየንን አላየችም። እርሱ ግን አያትና ሹልክ ብሎ ወደ ቤት ገባ።

የእነሉሲየንን ሣር ለማጨድ የአኔት አባት ሦስት ቀን ወሰደባቸው። ሦስተኛው ቀን የድርቆሽ ማዘጋጃው የመጨረሻ ዕለት ነበር። ሉሲየን፥ እናቱና እኅቱ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ሉሲየን ከመሄዱ በፊት ሣሩን ከምረው ለማጠናቀቅ ያለ እረፍት ሠሩ። አንድ ቀን አኔት እንደ ወትሮው ለአባቷ ምሳ ይዛ ስትመጣ ሦስቱም አጨዳው ስፍራ ነበሩ። የሚቀጥለው ዕለት ልጆች የመወዳደሪያ ሥራቸውን የሚያስረክቡበት ስለሆነ በጣም ቸኩላለች። ለውድድር የምታቀርበውን ሹራብ ለመጨረሻ ጊዜ ማስተካከል ነበረባት።

«በውድድሩ አሸንፌ ሽልማት አገኝ ይሆን? ማሸነፍን በጣም እፈልጋለሁ። ካላሸነፍኩም ሹራቡን ዳኒ ይለብሰዋል። በጣም እንደሚያምርበት እርግጠኛ ነኝ» አለች አኔት ለራሷ።

የእነሉሲየን ሣር ያለበት ሜዳ የሚገኘው ከቤታቸው ኋላ ሲሆን፥ አኔት የምትመላለሰው ግን ከፊት ባለው መንገድ ነበር። ቀኑ ሞቃት ነው፥ አኔት ውኃ ጠማት። ከጠባቧ መተላለፊያ ወደ ወጥ ቤት የሚያስገባው በር ክፍት ነው።

«ልግባና ከቧንቧው ውኃ ልጠጣ» አለች አኔት ወጥ ቤቱ ወደ አለበት ፎቅ እያመራች። ውኃ መጠጣት ማንንም አይጎዳም። ዳኒ ላይ ጉዳት ከመድረሱ በፊት አኔት ልክ እንደ ራሷ ቤት ነበር እነሉሲየን ቤት የምትገባውና የምትወጣው። ደረጃዎቹን ጨርሳ መተላለፊያው ላይ ስትደርስ አካባቢውን ትኩር ብላ እያየች በፀጥታ ቆመች።

መተላለፊያው ወይም በረንዳው ላይ አንድ ትንሽ ጠረጴዛ አለ። የእንጨት ፍቅፋቂና የቅርጽ ማውጫ መሣሪያዎች ከብ መቀመጫዎች ላይ ይታያሉ። ፍቅፋቂው መሀል ብትን ያለ ጋማ፥ ለስላሳ ሰኮናዎች ያሉትና የሚጋልብ ፈረስ ቅርጽ ተቀምጧል።

አኔት ይህን ትንሽ ቅርጽ በመመልከት ለአምስት ደቂቃ ያህል ቆመች። ሉሲየን ለቅርጻ ቅርጽ ውድድር ሊያቀርብ የሠራው መሆኑን

ተገንዝባለች። እርሱ ግን በውድድሩ የሚካፈል፥ ወይም ቅርጻ ቅርጾችን ለመሥራት የሚችል መሆኑን ለማንም አልነገረም።

ሥራው ይህ ቀረህ የማይበል ነው። ቅናት የሞላባቸው የአኔት ዓይኖች እንኳን ይህን አረጋግጠዋል። ለውድድር ቢያቀርበው እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ሆነች። እንዲህ የሚያምር ሥራ ማንም ሊያቀርብ አይችልም። ሽልማቱን ቢያሸንፍ ደግሞ፥ ሰው ሁሉ ስለ ሥራው ያደንቀውና ይወደዋል። ዳኒ ላይ ያደረሰውን ጉዳት እንኳን ይረሱለት ይሆናል እያለች አሰበች–አኔት።

ሉሲየን በውድድሩ ቢያሸንፍ ደስ ይለዋል። ሽልማቱን ለመቀበል ራሱን ቀና አድርጎ በኩራት ይሄዳል። ሉሲየን ተደስቶ መመልከቱን ግን አኔት አትፈልገውም። ለምን ይደሰታል? ሁለተኛ ደስተኛ ሊሆን አይገባም። የደስታውን ምክንያት ካሰናከለች ሊደሰት አይችልም። እስፍራው የደረሰችው በትክክለኛው ሰዓት መሆኑ ተሰማት።

ጠረጴዛው የበረንዳውን መደገፊያ ተጠግቶ በትክክል ቆሟል፤ ለስላሳ ንፋስ ፍቅፋቂውን በቀስታ ያርገበግበዋል። ከባድ ንፋስ ቢነሣ ሉሲየን የሠራውን ትንሽ ቅርጽ ይጥለዋል። ቅርጹ ጭቃ ላይ ወድቆና ተረጋግጦ አንድ ሰው ቢያገኘው እንዲያ ያደረገው ነፋስ ነው ይላል እንጂ ሌላ ነገር አይጠረጥርም።

አኔት እጇን ዘረጋችና የፈረሱን ቅርጽ ገፋችው። ድንጋይ ላይ ወደቀና በትንሹ ተሰነጣጠቀ። አኔት በፍጥነት ወደ ደረጃዎቹ ወርዳ ረገጠችው። በመረማመጃ ደረጃ ላይ የወደቀን ነገር ማንም ተላላፊ ይረግጠዋል።

የሉሲየን የፈረስ ቅርጽ በዚህ ሁኔታ በመተላለፊያ መንገድ ድንጋዮች ስንጣቂ ውስጥ ተወሸቀ። አኔትም ቀስ እያለች ወደ ቤቷ ሄደች።

የዕለቱ ብሩህነት ጠፋ፤ ዓለም እንደ ቀድሞው ውብ መሆኗ የቀረ መሰለ።

ገና ወደ ቤቷ ስትቃረብ ነበር ዳኒ ድምፁን ከፍ አድርጎ የእንኳን ደህና መጣሽ ሰላምታ የሰጣት። አንድ ደስ የሚያሰኝ ነገር ተፈጽሟል። ጤነኛ ቢሆን ኖሮ በሩጫ ሄዶ ነበር የሚቀበላት። እንዲያ ማድረጉ ባይቻለውም ክራንቹን ተደግፎ ዘለል ዘለል እያለ ባለው ፍጥነት ወደ እርሷ ሄደ።

«አኔት! አኔት!» አለ ዓይኖቹን እያጭለመለመ፥ «እንጨቱ ክምር ውስጥ በተረት የምንሰማቸውን የመሰሉ ትንንሽ አስማተኞች ሳይኖሩ አይቀሩም። ግንዶቹ አጠገብ ትንሽ ቤት ስሠራ ረጅም ግንድ የተሸከመ



ትንሽ ዝሆን አገኘሁ። እንደገና ስፈልግ ደግሞ ሻኛ ያለው ግመል፥ ረጃጅም ጆሮዎች ያሏት ጥንቸል፥ ላሞች፥ ፍየሎች፥ ነብሮችና በጣም ረጅም አንገት ያለው ቀጭኔ አገኘሁ። ነይና ተመልከቺቻቸው፤ በጣም ያምራሉ። እንጨቱ ክምር አጠገብ ያስቀመጧቸው ትንንሾቹ አስማተኞች ናቸው፥ ሌላ ምን ይሆናል?»

«እኔ እንጃ» አለች አኔት በሻከረ ድምፅ። ዳኒ ቀና ብሎ በመገረም አያት። ከእርሱ በሰማችው ነገር የተደሰተች አትመስልም። ሁኔታው፥ ለዳኒ ድመቱን ነጠላ ጫማ ውስጥ ካገኛት ወዲህ የገጠመው አስደናቂ ነገር ነው።

አኔት ቅርጾቹ ምን ያህል እንደሚያምሩ አላየቻቸውም እንጂ፥ ብታያቸው እንደምትወዳቸው እርግጠኛ ናት። አኔት ከእርሱ ጋር ስትሆን ቀስ ብላ ነበር የምትራመደው፤ ዛሬ ግን አድርጋው በማታውቀው ሁኔታ ስለ ፈጠነች ከእርሷ እኩል ለመሄድ ዳኒ ቶሎ ቶሎ ዘለል ዘለል ይል ጀምር።

ወደ ስፍራው ሲቃረቡ ዳኒ ሳብ አደረጋትና ተከታትለው ከእንጨቱ ክምር ጀርባ ዞሩ። የአራዊት ቅርጻ ቅርጽ አንድ ጠፍጣፋ ግንድ ላይ ተደርድረው ይታያሉ። አስተያየቷን ለማወቅ በጉጉት ተመለከታት። እርሷ ግን ምንም የመደነቅ ወይም የደስታ ስሜት አልታየባትም።

«ቅርጾቹን አንድ ልጅ ጥሏቸው ይሆናል ብዬ አሰባለሁ። ያም ሆነ ይህ ምንም የሚያስገርም ነገር የለም። የሚያስደንቅ ነገር የላቸውም። አንተ ደግሞ ትልቅ ልጅ ነህ፤ በትንንሽ አስማተኞች ማመን የለብህም» አለች በብስጭት።

ከዚያ መለስ ብላ ወደ ክፍሏ ለመግባት በፎቁ መረማመጃ ሽቅብ ወጣች። ከመበሳጨቷ ብዛት እራሷን ጠላችው። ለዳኒ ፍቅርን በመንፈጓ ደስታውን ሁሉ አበላሸችበት። እንዴት እንደዚያ ትናገረዋለች፣ ምን ሆና ይሆን?

የሆነችውን የእርሷ ልብ በሚገባ ይገነዘበዋል። ወራዳ የማታለል ድርጊት ስለ ፈጸመች፥ ያን በማሰብ ልቧ ከባድና ጨለማ ያጠላበት ሆኗል። ፈገግታና ደስታ ከሕይወቷ የጠፉባት መሰላለች።

ከዚህ ሁኔታ ለመላቀቅ ወይም የሆነውን ነገር እንዳልሆነ ለማድረግ አልቻለችም። በሩጫ ፎቁን ወጥታ መኝታ ክፍሏ በመግባት፥ አልጋዋ ላይ ተዘረረችና ስቅስቅ ብላ አለቀሰች።